



@OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ
TEL. 11 27 19

ፖ. ሣ. ቁ
P. O. Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል — ሱቃስ አማረ

@OLDBOOKSPDF

# የትርጉሙ መታሰቢያነት

በኖሩበት አካባቢ ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋና የዕውቀት ብርሃን እንዲበራ ድካቸው ወገኖቻቸውም ሕይወታቸውን እንዲያሻሽሉ ዕድሜ ልካቸውን ለደከሙት ፤

አባ ፍራንሷ ማርቆስ ኬርሳ (1902 — 1981)

@OLDBOOKSPDF

በሕግና በልማድ ስም ምድራዊ ኩነኔ የሚፈጥር የጥርድ ውሳኔ እስ
ካለ ድረስ ፤ ሰዎች በድህነት ምክንያት መዋረዳቸው ፥ ሴቶች በረሃብ ምክ
ንያት ሰብዓዊ ክብራቸውን ማጣታቸው ፣ ሕጻናት ልጆች የዕውቀት ብርሃን
በማጣት ገደሎ ሆነው መቅረታቸው ፡— እነዚህ የምዕተ ዓመቱ ታሳላቅ
ኻጢኻት መፍትሔ እስካላገኙ ድረስ ፤ ሕብረተሰቡ ነጻ አየር እንዳይተነፍስ
የሚያግደው ሁኔታ ለመኖር እስከቻለ ድረስ ፤ ባጭሩ በአለንበት ምድር
ደንቁርናና ድህነት እስከሰፈኑ ድረስ «መከረኞች»ን የመሳሰሉ መጻሕፍት
ተፈላጊነት ሳይኖራቸው ሊቀር አይችልም ።

ደራሲው ።

@OLDBOOKSPDF

# ማ ው ጫ ገጽ

## ክፍል አንድ፡- ፋንቲን


መጽሐፍ አንድ ፡— በጎ ሰው ፡ - - - - - - - - - - - 9
» ሁለት ፡— ውድቀት - - - - - - - - - - - 61
» ሦስት ፡— 1817 ዓ. ም. - - - - - - - - - - 105
» አራት ፡— ሰውን ማመን ፤ ለሰው መገዛት ፡ - - - - 121
» አምስት ፡— አዘቅት - - - - - - - - - - 129
» ስድስት ፡— ጣቪር - - - - - - - - - - 155
» ሰባት ፡— የሻማትየ ጉዳይ - - - - - - - - 165
» ስምንት ፡— አጸፋ - - - - - - - - - - 205


## ክፍል ሁለት፡- ኮዜት


መጽሐፍ አንድ ፡— አሪዮን የተባለው መርከብ - - - - - 219
» ሁለት ፡— የተስፋ ተፈጸሚነት - - - - - - - 223
» ሦስት ፡— የጎርቦ ማረፊያ ቤት - - - - - - - 253
» አራት ፡— አደን ያበረረው - - - - - - - - 261
» አምስት ፡— ፕቲ—ፒክፑ - - - - - - - - 275


## ክፍል ሦስት፡- ማሪዩ


መጽሐፍ አንድ ፡— ፓሪስ የወለደው - - - - - - - - 301
» ሁለት ፡— ታላቁ ከበርቴ - - - - - - - - 305
» ሦስት ፡— የሀሀሂ ወዳጆች - - - - - - - - 319
» አራት ፡— ክፉ ቀን - - - - - - - - - 331
» አምስት ፡— የሁለት ክህቦች መግጠም - - - - - 339
» ስድስት ፡— ድሃና ክፉ ሰው - - - - - - - - 347


## ክፍል አራት፡- የፕሎሜ ጐዳና ትርጢትና የሴን-ዴኒዝ ጐዳና ገድል


መጽሐፍ አንድ ፡— ከታሪክ ጥቂት ገጾች - - - - - - - 407
» ሁለት ፡— ኤፖኒን - - - - - - - - - - 411


@OLDBOOKSPDF

» ሦስት ፡— በፕሎሜ ጐዳና ያለው ቤት - - - - - 421
» አራት ፡— ከታች የተገኘው ዕርዳታ ከላይ የተገኘ
ሊሆን የሚችልበት ጊዜ አለ - - - - - - - - 435
» አምስት ፡— ጅማሬውን የማይመስል ፍጻሜ - - - 441
» ስድስት ፡— ትንሹ ጋቭሮሽ - - - - - - - - 449
» ሰባት ፡— ደስታና ሀዘን - - - - - - - - - 463
» ስምንት ፡— የት ነው የሚሔዱት ? - - - - - - 477
» ዘጠኝ ፡— የአመጽ መንገድ - - - - - - - - 483
» አስር ፡— ኮሪንት - - - - - - - - - - 487
» አሰራ አንድ ፡— የሎም አርሜ ጐዳና - - - - - 507

## ክፍል አምስት፡- ጣና ቫልዣ

መጽሐፍ አንድ ፡— አመጽና ውጊያ - - - - - - - - 515
» ሁለት ፡— የፓሪስ ከርሰ ምድር - - - - - - - 525
» ሦስት ፡— ያዳለጠው ጣቼር - - - - - - - - 539
» አራት ፡— የልጅ ልጅና አያት - - - - - - - - 543
» አምስት ፡— ሠርግ - - - - - - - - - - 549
» ስድስት ፡— የጣን ቫልዣ ኩዘዜ - - - - - - - 553
» ሰባት ፡— ጭልምልምታ - - - - - - - - 559
» ስምንት ፡— ወድቅት ጭለማና ንጋት - - - - - 563

@OLDBOOKSPDF

ከፍል አንድ

ፋብሪካ

@OLDBOOKSPDF

# መጽሐፍ አንድ

## በሳ ሰው

### — 1 —

አባትዬው የኤክስ ከተማ ምክር ቤት አባል ነበሩ ። ልጆቸውም ወደ ፊት የምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ የአባትዬው ምኞት ነበር ። ገና በልጅ ነታቸው ትዳር አስያዝዋቸው ፤ ልጅዬውን ። ቫርል — ፍራንሲ — ቢየን ቨኒው ሚሪዬል ትዳር በያዙበት ጊዜ የአሰራ ስምንት ፤ አስዚያም ግፋ ቢል የሀያ ዓመት ጉብል ነበሩ . . . ቁመታቸው አጠር ያለ ፤ ሰውነታቸው የተዳላደለ ፤ አጭማቸው ያማረ ፤ አእምሮአቸው የበራ ገበል ። ገና በአፍላ ነታቸው ትዳር ቢይዙም ቫርል ሚሪዬል ዓለመኛ ወጣት ነበሩ ይላለ።በዚህ ጉዳይ በጣም ይታሙ ነበር ።

ጊዜው ውለ፡ ክደረ በኋላ የፈረንሳይ አብዮት መጣ ። አስከፊ ሁኔታ ምችም ተደራርበው መጡ ። በምክር ቤቱ አባሎችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ያልታሰበ ጻቡ ዕጻ ወደቀባቸው ። ብዙዎቹ ተገደሉ ። ከተረፉት መሐከል አንጻንዶቹ እንደ አውሬ ታዶኑ ። የተቀሩት ኮብለለው ጠፉ ። ቫርል ሚሪ ዬል አብዮቱ እንደ ኮጀመረ ወዲያውኑ ወደ ኢጣሊያ አገር ሽሹ ። ባለቤ ታቸው የልብ በሽታ ነበረባቸው ። ልጅ እንኳ ወልደው ሳይተኩ እዚያው ኢጣሊያ አገር አረፉ ። ከዚያ በኋላ በቫርል ሚሪዬል ሕይወት ላይ ምን እንደደረሰ በውል አይታወቅም ። ይሁን እንጂ በሕይወታቸው ላይ ታላቅ ለውጥ ስለተፈየ የዚህ ምክንያት ምን ይሆን የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አል ቀረም ። የቅድመ አብዮት የፈረንሳይ ሕብረተሰብ መፍረስ . . . የቫርል ሚሪዬል ቤተሰብ ከሕይወት መፈናቀል . . . የተቀሩትም አስከፊ ሁኔታ ዎች ይሆኑ ሕይወታቸውን የለወጡባቸው ? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ያስቸግራል ። ይሁን እንጂ ቫርል ሚሪዬል ከኢጣሊያ አገር ወደ ትውልድ አገራቸው በተመለሱበት ወቅት አለመኛ የሚባሉ ሰው አልነበሩም ። እንዲያውም ሰውን ሁሉ ያስደንቀው ቫርል ሚሪዬል ወደ ፈረንሳይ አገር በተመለሱበት ጊዜ ተስለው መገኘታቸው ነበር ። በ1804 ዓ. ም. ቫርል ሚሪዬል የብረዎል ዱብር ካህን ሆኑ ። በዚያን ጊዜ በዕድሜ ገፍተዋል ። አንገታቸውንም ቀብረው ነበር የሚኖሩት ።

ናፖሊዎን በናፓርት ዘውድ በጫነበት ዘመን አካባቢ ቫርል ሚሪ ዬል በውል ባልታወቀ ፤ ነገር ግን ደብሩን በሚመለከት ጉዳይ ወደ ፓሪስ ከተማ ሔዱ ። ለደብሩ ዕርዳታ ከሚጠይቋቸው የቤተ ክህነት ባለሥልጣ



@OLDBOOKSPDF

ኖች መሐከል አንዱ ካርዲናል ፌሽ ፤ የናፖሌዎን አጎት ነበሩ ። አንድ ቀን ሻርል ሚሪዬል በዚሁ ካርዲናል እንግዳ መቀበያ ክፍል ሆነው ሲጠ ባበቁ ሳሉ ናፖሌዎን ቦናፓርት በድንገተ ከቸች ይላል ። አጎቱን ለመጠየቅ መምጣቱ ነበር ። ሻርል ሚሪዬል አጥብቀው ሲመለከቱት ነበሩ ። ናፖሌ ዎን ቦናፓርት ወደሳቸው ዞር ብሎ ፤ «አንተ በጎ ሰው ማነህ? ለምንስ አጥ ብቀህ ትመለከተኛለህ ?» ሲል ጠየቃቸው ።

«ሽንሆይ . . . እርስዎ የሚመለከቱት በጎ ሰው . . . እኔም የምመለከ ተው ታላቅ ሰው . . . ለሁሊታችንም በጀን እንጂ ምን ከፋን !» ሲሉ መለሱ ሻርል ሚሪዬል ።

በዚያው ቀን ምሽት ናፖሌዎን ቦናፓርት የካህኑ ስም ማን እንደሆነ አጎቱን ጠይቆ ተረዳ ። ጥቂት ጊዜ ካለፈም በኋላ ሻርል ሚሪዬል የዬ ሰበካ አቡን ሆነው መሰየማቸውን ሰሙ ። ሹመቱ ሳያስገርማቸው አልቀ ረም ።

ይህ የሆነው በ1806 ዓ. ም. ላይ ነበር ።

አቡኑ በሰበካቸው ከደረሱበት ቀን ጀምሮ ስለቀድሞ ሕይወታቸው በሰፊው ተወራ ። ዓለመኛ ነበሩ ተብለው ታሙ ። ይህ ዓይነቱ ሐሜታ ግን የሚያስገርም አይደለም ። በአንድ አነስተኛ ከተማ ውስጥ አዲስ መጥ ሰው ሲታይ የከተማው ነዋሪዎች ስለ አዲስ መጡ ማውራት ልማዳቸው ነው ። ደሞም በትንሽ ከተማ ነዋሪ ከሆኑ ሰዎች መሐከል በአእምሮአቸው የሚገዙ ጥቂት ሰዎች ባይጠፉም አብዛኛዎቹ ጊዜአቸውን የሚያጠፉት በከንቱ ወሬ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም ። ስለሆነም አቡነ ሚሪዬል ዓለመኛ ነበሩ በማለት በሰፊው ታሙ ። እሳቸው አቡን እንደመሆናቸው መጠን አስባልታውንና ሐሜቱን በጸጋ ተቀበሉት ። ቻሉት ።

አቡነ ሚሪዬል ወደ ዬ ሰበካ የመጡት ከእህታቸው ከማድሚዜል ባፕቲስቲን ጋር ነበር ። የአስር ዓመት ታናሻቸው ነች . . . ሴተ ላጤ . . . ረጅም . . . ገርጣ ያሰች . . . ቀጭንና ለዘብተኛ ። ጨዋ ሴት ብትሆንም የእናትነት ወግ ሳይደርሳት በመቅረቷ ልትከበርበት አልቻለችም ። መን ፈሳዊ ነች ማድሚዜል ባፕቲስቲን ። ከልጅነቷ ጀምሮ ቀጭን ነች ። ዕድ ሚዋ እየገፋ በሐዲም ቁጥር ይበልጥ እየቀጠነች ስለሔደች ሰውነቷ ከመ ስተዋት እንደተሠራ ሁሉ በወዲህም በወዲያም የሚያሳይ ይመስል ነበር ። የገጽ ውበት ባይኖራትም የመንፈስ . . . የደግነት ውበት የሚያንሳት አልነበረችም ። በአጠቃላይ መልአካዊ ባህርይ ነበራት ለማለት ይቻላል ።

አቡነ ሚሪዬልና እህታቸው ወደ ዬ ከተማ የመጡት ከሴት ሠራተ ኛቸው ጋር ነበር ። ሠራተኛቸው ማዳም ማሷር ትባላለች ። በዕድሜ የማድ ሚዜል ባፕቲስቲን እቾ ነች ። እጭር . . . ወፍራም . . . በጣም ነጭ ። ሁልጊዜ ትንፋሽ ያጥራታል ። ይኸውም ከወዲያ ወዲህ ፤ ከወዲህ ወዲያ ማለትን ስለምታበዛ ብቻ ሳይሆን የአስማ በሽታ ስላላት ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

አቡነ ሚሪዬል እሀታቸውንና የቤት ሠራተኞቸውን አስክትለው ከተሰየሙበት ከተማ እንደደረሱ ወዲያውኑ በንጉሠ ነግሥቱ ድንጋጌ መሠረት በመንበረ ሥልጣናቸው ተቀመጡ ። መንበረ ሥልጣናቸውም ከሚጀር ጄኔራል ሥልጣን አንድ ደረጃ ብቻ ዝቅ ያለ ነበር ። በመጀመሪያ አቡኑን መጥተው የጠየቋቸው የከተማው ከንቲባና ፕሬዚዳንቱ ሆኑ ። አቡኑም በመጀመሪያ ሐኤው የጠየቋቸው ጄኔራሉንና አገረ ገዥውን ነበር ።

አቡነ ሚሪዬል በመንበረ ሥልጣናቸው ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ የከተማው ሕዝብ ሥራቸውን ለማየት በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር ።



የዴ አቡን የሚኖሩበት ሕንጻ ከሐኪም ቤቱ ጋር ኩታ ገጠም ሆኖ የተሠራ፣ግርማ ሞገስ የተጐናጸፈና ከቤተ መንግሥት ጋር ሊወዳደር የሚችል ፣ በጣም ግዙፍና ያማረ ሕንጻ ነበር ። መኝታ ቤቶች ፣ የእንግዳ መቀበያ ክፍሎች ፣ አዳራሾች ፣ ሰፊ ምድረ ግቢ ፣ በምድረ ግቢው ውስጥ ከለላ ያላቸው መንሸርሸርያ መንገዶች ፣ የሚያማምሩ ዛፎች የበቀሉበት የአት ክልት ቦታ ፣ እነዚህን ሁሉ አቅፎ የያዘ ነበር ። በምድር ቤቱ የነበረው የምግብ አዳራሽም በጣም ረዥም ሆኖ ከአትክልቱ ቦታ ትይዩ ነበር ። ባለፈው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ሕንጻውን በድንጋይ ያሳነጹት ሙሴ ሀንሪ ፒገር ፣ በፓሪስ ሩክልቲ የቲዮሎግ ዶክተር ፣ የሲሞር ካህን ነበሩ ። ሙሴ ሀንሪ ራሳቸው በ1712 ዓ. ም. የዴ አቡን ነበሩ ። በሐምሌ 29 ቀን 1714 ዓ. ም. ሙሴ ሀንሪ ፒገር በታላቁ የምግብ አዳራሽ ውስጥ በርከት ያሉ ታላላቅ ሰዎችን ግብር አብልተውበታል ፣ —እነ ሻርል ብሩ ላር ፤ የጣንሲው ጌታ ፤ ሲቀጳስ . . . የዳምብረ ልዑል .. . እንቷን ደ ሜግሪኟ ፤ ካፑቺን ፤ የግራስ አቡን . . . ፊሊፕ ደቫንዶም ፤ ታላቁ የፊረ ንሳይ ገዳም ቆሞስ ፤ የሴን አኖሬ ደ ሴረ ካህን . . . ፍራንሷ ደ ቦርቦን ደ ከሪየን ፤ አቡን ፤ የቫንስ መስፍን . . . ሴዛር ደ ሳብራን ደ ፎርካልኪዬ ፤ አቡን ፤ የግሳንዬቭ መስፍን . . . እና ጥን ሶነን ፤ የአራቷር ካህን ፤ የንጉሡ ሰባኪ ፤ አቡን ፤ የሴንዝ መስፍን ። የምግብ አዳራሹ በእነዚህ ሁሉ ታላላቅ ሰዎች ምስል ተጊጦ ይታያል ። ታላቁ የግብር ቀንም ፤ ማለት «ሐምሌ 29 ቀን 1714 ዓ. ም.» ከነጭ ዕብነ በረድ በተሠራ ጠረጴዛ ላይ በወርቅ ቀለም ተቀርጾ ይታያል ።

አቡኑ በመጡ በሦስተኛው ቀን ከመኖሪያቸው ሕንጻ ጋር ኩታ ገጠም ሆኖ የተሠራውን ሐኪም ቤት ጐበኙት ። ሐኪም ቤቱ ለዓይን የሚያሞላ አልነበረም ። ካለአንድ ፎቅ የለውም ። ጠባብም ነው ። የአት ክልቱም ቦታ እንዲሁ ጠባብ ሆኖ አገኙት ። ጉብኝታቸውን ሲጨርሱ የሐኪም ቤቱ ዲሬክተር ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲመጣ ጋበዙትና እዚያ እንደደረሰ ቃል ይለዋወጡ ጀመር ።



@OLDBOOKSPDF

«ሙሴ ዲሬክተር . . . በአሁኑ ጊዜ ስንት በሽተኞች አሉህ ?»

«ሀያ ስድስት ናቸው ብጹዕነትዎ ።»

«ሀያ ስድስት . . . ? እኔም የቆጠርኳቸው ሀያ ስድስት ናቸው ።»

«አልጋዎቹ ግን ተጣብበዋል ብዕጹነትዎ ።»

«አሰጉም ተመልክቻለሁ ሙሴ ዲሬክተር ።»

«ክፍሎቹ በጣም አነስተኛ ከመሆናቸው የተነሳ ለንጹህ አየር እንኳ በቂ ቦታ የለም ።»

«አሰጉም ልብ ሳልለው አልቀረሁም ሙሴ ዲሬክተር ።»

«የአትክልቱም ቦታ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሚያገግሙት በሽተኞች ጸሐይ ባለ ጊዜ ጸሐይ ለመሞቅ ሲወጡ ቦታው ያንሳቸዋል ።»

«ሀሰጉም ልብ ብያለሁ ሙሴ ዲሬክተር ።»

«ተስቦ በሽታ ቢነሳ ምን ማድረግ እንደሚገባን እንኳ አናውቅም ብጹዕነትዎ ። በዚህ ዓመት እንኳ ወረርሽኝ በሽታ ገብቶ ነበር ። ከሁለት ዓመታት በፊትም የሚያልብ በሽታ ተነስቶ ነበር ። በዚህ በሽታ ምክንያት አንድ መቶ የሚሆኑ ሰዎች ታምመው ነበር ።»

«በእርግጥም እንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ቢደርስ ምን ማድረግ ይቻላል ብዬ ሳስብ ነበርኩ እኔ ራሴ ።»

«ታዲያ ምን ይሻላል ብጹዕነትዎ ? ጉዳዩ የሚያሳስብ መስሎኛል ።»

ይህንን ቃል የተለዋወጡት አቡኑ በሚኖሩበት ሕንጻ በምድር ቤቱ ባለው ረጅም የምግብ አዳራሽ ውስጥ ነበር ። አቡነ ሚሪዬል ለትንሽ ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሐኪም ቤቱ ዲሬክተር መልሰው፤ «ስመሆኑ ይህ የምግብ አዳራሽ ስንት አልጋ ለመያዝ የሚችል ይመስለ ሃል ?» ሲሉ ጠየቁት ።

«የብጹዕነትዎ የምግብ አዳራሽ ?» አለ ዲሬክተሩ ደንገጥ ብሎ ።

አቡነ ሚሪዬል እንደገና ዝም አሉና አዳራሹን በዓይናቸው ቃኙት ። በዓይነ ገመድ የሚለኩትም መሰሉ ። በሃሳባቸው «ከሀያ ያላነሰ አልጋ ሊይዝ ይችላል» አሉና ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ፤ «ስማኝ ሙሴ ዲሬክ ተር . . .» አሉት ፤ «አንድ የምነግርህ አለኝ ። አየህ . . . አንድ መስተካ ከል ያለበት ነገር እንዳለ ይሰማኛል ። እናንተ በሐኪም ቤቱ ያላችሁት



@OLDBOOKSPDF

በአምስት ወይም በስድስት አነስተኛ ክፍሎች ውስጥ ሠላሳ ስድስት ሆኖ ችሁ ትኖራላችሁ ። እዚህ ያለነው ግን ሦስት ብቻ ነን ። ይሁን እንጂ ለስ ድሳ ሰው የሚሆኑ ክፍሎችን ይዘን ተቀምጠናል ። ይህ ሁኔታ የተዛባ ስለ ሆነ መስተካከል አለበት ። ስለዚህ ቦታ እንድንቀያየር ፈቃዴ ነው ። እና ንተ ወደዚህ ትዛወራላችሁ ፣ እኛም ወደዚያ . . . »

እንዳሉትም በማግሥቱ አቡነ ሚሪዩል ፣ እህታቸውና የቤት ሠራ ተኛቸው ወደሐኪም ቤቱ ፣ በሐኪም ቤቱ የነበሩትም ወደ ማዙፉ ሕንጻ ተዛወሩ ።

አቡነ ሚሪዩል ሀብት ንብረት አልነበራቸውም ። የወላጆቻቸው ሕይ ወት በእብየቱ መከሰት ተፈናቅሎ ስለነበረ ሀብት ንብረት አልወረሱም ። እህታቸውም በጠሪታ መልክ የሚከፈላት የዓመት ገቢዋ አምስት መቶ ፍራንክ ብቻ ነበር ። ሆኖም አቡነ ሚሪዩል አቡን እንደመሆናቸው መጠን ከመንግሥት በየዓመቱ 15,000 ፍራንክ ደመወዝ ይከፈላቸው ነበር ። ወደ ሐኪም ቤቱ ቅጥረ ግቢ ከተዛወሩበት ቀን ጀምሮ ይህንን ደመወዛቸው ቅጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ወጪ ያደርጉት ነበር ። በዛ እጃቸው እንደ ጻፉት ዝርዝሩ እንሆ ፤

የቤት ወጪዬ ዝርዝር ሁኔታ

| | | |
|---|---|---|
| ለትንሹ ዕጩ ካህናት ማሠልጠኛ - - - - - - | 1,500 | ፍራንክ |
| ለሚሲዮን ማህበር - - - - - - - - - - | 100 | » |
| በሞንጻዲዬ ለሚገኙ ላባሬስት ካህናት - - - - | 100 | » |
| በፓሪስ ለሚገኘው የሠጭ ሚሲዮኖች ዕጩ ካህናት ማሠልጠኛ - - - - - - - - - - - - | 200 | » |
| ለመንፈስ ቅዱስ ማህበር - - - - - - - - - | 150 | » |
| በኢየሩሳሌም ለሚገኙ የታይማኖት ተጓሞች - - - | 100 | » |
| ለእናቶች መርጃ ድርጅት - - - - - - - - - | 300 | » |
| በተጨማሪ በአርል ለሚገኘው - - - - - - - - | 50 | » |
| ለእስር ቤቶች ማሻሻያ ሥራ - - - - - - - - | 400 | » |
| ለእስረኞች መርጃ - - - - - - - - - - - | 500 | » |
| በዕዳ ምክንያት ለታሠሩ የቤተሰብ ታላቆዎች ማስፈቻ - | 1,000 | » |
| በሰበካው ውስጥ አነስተኛ ደሞዝ ለሚከፈሉ መም ህራን መደጐሚያ - - - - - - - - - - - | 2,000 | » |
| በሆት—ኦልፕ ለሚገኘው የሕዝብ እህል ማከማቻ | 200 | » |
| በዴ ፣ በማኖስክና በሊስትሮን ለሚገኙና ድሆች የሆኑ ልጃገረዶችን በነጻ ለሚያስተምረው የወይዛዝርት ማህበር - - - - - - - - - - - - | 1,500 | » |
| ለድሆች - - - - - - - - - - - - - | 6,000 | » |
| ለራሴ ወጪ - - - - - - - - - - - - | 1,000 | » |
| ጠቅላላ ድምር - - - - - - - - - - - | 15,000 | » |



@OLDBOOKSPDF

አቡነ ሚሪዮል በደሴ ሰበካ በቆዩበት ዘመን ሁሉ ይህንን የወጪ ዝርዝር አንዳችም ጊዜ አልቀየሩትም ።

ማድሚዘል ባፕቲስቲን በአቡኑ ውሳኔ ምን ጊዜም ቢሆን ስለምትጸና በወጪው ዝርዝር ላይ አንዳችም የተቃውሞ ዝንባሌ አላሳየችም ። በሥጋ ወንድሚ እንደመሆናቸው መጠን ትወዳቸዋለች ። በመንፈሳዊ ሥራቸው ግን አሊታዋ ስለሆኑ ታከብራቸዋለች ። በዚህ ምክንያት ስታነጋግራቸው እንኳ አንገቷን ደፍታ እንኚ ቀና ብላ አታያቸውም ። የቤት ሠራተኛዋ ማዳም ማሏር ግን በወጪው ዝርዝር ሁኔታ ቅሬታ ሳይገባት አልቀረችም ። ይኸውም አቡኑ ለራሳቸው መተዳደሪያ የመደቡት የገንዘብ ወጪ በዓመት አንድ ሺ ፍራንክ ብቻ ስለነበረ ነው ። የእህታቸው የጡረታ አበል ሲታ ከልበት ጠቅላላው ወጪ 1,500 ፍራንክ ነበር ። በዚህ ወጪ የሚተዳደሩት ሦስት ራሳቸውን መሆኑ ሲታወስ የሚያዝናናቸው ነበር ለማለት አያስደፍርም ። እንዲያውም ከእጅ ወደ አፍ ይኖሩ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም ።

ከገጠር አንድ ቄስ ወደ ዴ ሰበካ ሲመጡ እንኳ አቡኑ ከዚሁ አነስተኛ ወጪአቸው አስተናግደው ይሸኟቸው ነበር ። እህታቸው በቤት አያያዝ ባለሙያ ባትሆን ኖሮ ፣ የቤት ሠራተኛቸውም በቁጠባ ረገድ የተመሰገነች ባትሆን ኖሮ ይህንን ሁሉ ሰሚድረግ በጣም ባስቸገራቸው ነበር ።

አንድ ቀን አንድ የገጠር ቄስ ከአቡነ ሚሪዮል ዘንድ መጥተው ሰሦስት ወራት ያህል እዚያው ሲስተናገዱ ሰንብተው ወደ ገጠሩ ከተመለሱ በኋላ አቡኑ ፊታቸውን ወደ ማዳም ማሏር መልሰው ፣ «አሁንስ የወጪው ነገር አሳሰበኝ ! » አሏት ።

«አምን የሚያሳስብ ነው ! » ስትል መለሰችላቸው ፣ «ብጹዕነትዎ በከተማው ውስጥ ለመጓጓዣና በሰበካው ውስጥ ለሚያደርጉት ጉብኝት እንኳ አበል ጠይቀው አያውቁም ። በቀድሞ ጊዜኩ የዚህ ዓይነት አበል ይሰጥ ነበር ! »

«እንኳን አስታወስሺኝ ማዳም ማሏር! በእርግጥም ቀደም ባለው ጊዜ የዚህ ዓይነት አበል ይከፈል ነበር» አሉና ይኸው አበል እንዲከፈላቸው ለሲኖዶሱ አመለከቱ ።

ሲኖዶሱ ጥያቄአቸውን ተቀብሎ ከተነጋገረበት በኋላ በዓመት የሦስት ሺ ፍራንክ አበል እንዲከፈላቸው ወሰነ ። የአበሉም አርእስት ፈለመጓጓዣ ፣ ለደብዳቤ መላላኪያ ፣ እና ለሰበካው ጉብኝት እንዲሆን ለአቡነ ሚሪዮል የተፈቀደ አበል» የሚል ነበር ።

የዚህ አበል መፈቀድ አንዳንድ ባለሥልጣኖችን ሳያስቆጣ አልቀረም ። ከነዚህ መሐከል የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል የነበረ አንድ ባለሥልጣን ነበረበት ። ይህ ባለሥልጣን ከመናደዱ የተነሳ በምሥጢር



@OLDBOOKSPDF

የሚያዝ የቁጣ ደብዳቤ ከመጻፍ አልተግታም ። ሰውዬው ቀደም ብሎም ከባድ ሰው ነበር ። በፈረንሳይ አብዮት ወቅት ከአምስት መቶዎቹ የደርግ አባሎች አንዱ ነበር ። አሁንም በዴ ከተማ አቅራቢያ ከሥልጣኑ ጋር የሚመጣጠን የገዘፈ ቢሮ ተሰጥቶት ይሠራ ነበር ። ይህ ባለሥልጣን በምስጢር የሚያገና ቁጣ የተመላበት ደብዳቤ የጻፈው ሰኃይማኖት ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ለሙሴ ቢጎ ደ ፕራአመኑ ነበር ። በውስጡም እንዲህ የሚል ነበረበት ፤

«የመጓጓጥ ወጪ. . . . ? አራት ሺ የማይሞሉ ነዋሪዎች ባሉበት የገጠር ከተማ በመጓጓጥው ወጪ ምን ሊደረግበት ነው ? የጉብኝት ወጪ. . . . ? ቀድሞ ነገር ጉብኝቱ ለምን አስፈለገ ? ደሞስ ሰፖስታ መላላኪያ የተባለው ወጪ በዚህ ተራራማ አገር ውስጥ በሥራ ላይ ሊውል እንዴት ይቻላል ? በዚህ አካባቢ መግደሎች የሉም ። በፈረስ እንኚ በሌላ ዘዴ ለመጓዝ አይቻልም ፣ በዱራንስና በሻቶ — አርኖ መሐከል ያለው ድልድይ እንኳ ጥግድ በፊ ለማሻገር ያጸግተዋል ። ቁስች ሲባሉ ሁሉም ያው ናቸው ፣ ለገንዘብ ይስገበገባሉ ። ይህ ቁስ [አቡኑ] በመጀመሪያ ወደዚህ ሲመጣ በጎ ሰው መስሎ መጣ ። አሁን ግን እንደሌሎች ሁሉ ለመንደላቀቅ ይፈልጋል ። መጓጓጥና የደብዳቤ ማመላለሻ ሠረገላ እንዲኖረው ይሻል ። እንደ ቀድሞዎቹ አቡኖች በቅንጦት ለመኖር ይፈልጋል ። አዬ ቅስና ! ንጉሥ ነገሥቱ ከእነዚህ ጥቁር ቆብ ሰባኞች ካልገላገሉን በስተቀር ምንም ነገር ሊሳካ አይችልም ። የሮማው ጳጳስ ይውደም ! (ይህንን ያለው ከሮማ ጋር መቃቃር ስለነበረ ነው ።) እኔ በበኩሴ የቁጣርን ሥልጣን ነው የምደግፈው . . . » ወዘተርፈ . . . ወዘተርፈ ።

የአበሉ መፈቀድ እንደዚህ ያሉትን ባለሥልጣኖች ያስቆጣ ቢሆንም ማጸም ማቧርን በጣም አድርጎ አስደስታት ። «እንዴት ጥሩ ሆነ !» አሰኝ ማድሟዜል ባፕቲስቲንን ኢያየች ፤ «በጴዕኔታቸው ለሌሎች ሰዎች ከማ ሰባቸው የተነሳ ራሳቸውን ጥለው ነበር የሚኖሩት ። አሁን ግን ሦስት ሺ ፍራንክ አበል ስለተፈቀደላቸው ለእሳቸውም ለኛም በጀ !»

ለማጸም ማቧር መሰላት እንጂ ምንም የተሻሻለ ነገር አልነበረም ፤ አቡኑ በዚያው ዕለት ማታ ይህ አበል በምን ሁኔታ ወጪ እንደሚሆን ለእህታቸው ማስታወሻ ጽፈው ሰጥተዋት ነበርና ። ማስታወሻው እነሆ ፤

## የመጓጓጥና የደብዳቤ መላላኪያ አበል

| | | |
|---|---|---|
| በሆስፒታል ውስጥ ለሚገኙ በሽተኞች የሥጋ ሾርባ የሚዘጋጅበት - - - - - - - - - - - - - | 1,500 | ፍራንክ |
| በኤክስ ለሚገኘው የእናቶች መርጃ ማህበር - - - | 250 | » |
| በድራጊኛ ለሚገኘው የእናቶች መርጃ ማህበር - - | 250 | » |
| ተጥሎው ለተገኙ ሕጻናት ማሳደጊያ - - - - - - | 500 | » |
| ለሙት ልጆች - - - - - - - - - - - - - | 500 | » |
| ጠቅላላ ድምር - - - - - - - - - - - - - | 3,000 | » |



@OLDBOOKSPDF

ሰበካው አልፎ አልፎ ሌላ ገቢም ነበረው ። ከበርቴዎች አንዳንድ የኃይማኖት አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው በሚጠይቁበት ጊዜ ፣ ለምሳሌ ጋብቻ እንዲፈጸምላቸው ፣ ልጃቸው በግል እንዲጠመቅላቸው ፣ የጸሎት ቤት ወይም ቤተክርስቲያን እንዲባረክላቸው ፣ ሥርዓት እንዲደረግላቸው ፣ ወይም ሌላ አገልግሎት እንዲሰጣቸው በሚጠይቁበት ወቅት አቡኑ የአገልግሎት ዋጋ ያስከፍሏቸው ነበር ። የሚያስከፍሉትም ዋጋ ቀላል አልነበረም ። ምክንያቱም ከእነዚህ ከበርቴዎች የሚያገኙት ገቢ ችግረኞችን ለመርዳት ያስችላቸው ነበርና ።

ከጊዜ በኋላ ስጦታም ይገርፍ ጀመር ። አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አቡነ ሚሪዮል ከፍ ያለ ሀብት በስጦታ መልክ ገባላቸው ። ይሁን እንጂ ምንም ያህል ሀብት ቢገባላቸው አንዳችም ፍራንክ በእጃቸው አይቆይም ነበር ። ምክንያቱም ከከበርቴዎች ያገኙትን ገንዘብ ወዲያውኑ ለችግረኞች ያከፋፍሉት ነበርና ። ምን ጊዜም ቢሆን ከላይ ካሉት ከበርቴዎች ከታች ያሉት መከረኞች በቁጥር አይለው እንደሚገኙ የታወቀ ነው ። ስለሆነም በአቡነ ሚሪዮል እጅ የሚተላለፈው ሀብት አሸዋ ውስጥ ገብቶ እንደሚጠፋ ውሃ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን አቡነ ሚሪዮል የግል ሕይወታቸውን ለማሻሻል ሙከራ ያደረጉበት ቀን አልነበረም ። በመጀመሪያ በወሰኑት አነስተኛ በጀት እንደቀድሞው ከእጅ ወደ አፍ ይኖሩ ነበር ።

በአቡነ ሚሪዮል ችሮታ ይተዳደሩ የነበሩት ችግረኞች አቡነ ሚሪዮልን «እንኳን ደህና መጡ» ብለው ይጠሯቸው ጀመር ። በተለምዶ አንድ አቡን ከተሾመበት ሰበካ ሲደርስ ሙሉ ስሙን ለምዕመናኑ ይገልጻል ። በሚጽፋቸውም ኃይማኖት ነክ ደብዳቤዎች ላይ ይህንኑ ስም ያሰፍራል ። በልማዱ መሠረት አቡነ ሚሪዮል ሙሉ ስማቸው ኤም ቫርል—ፍራንቧ ቢየንቨኒው ሚሪዮል መሆኑን ገልጸው ነበር ። የአካባቢያቸው ችግረኞች ግን ለአቡናቸው ያላቸውን ፍቅር ለመግለጽ ያህል «ቢየንቨኒው» (እንኳን ደህና መጡ) የሚለውን መርጠው በዚህ ስም ብቻ ይጠሯቸው ነበር ። አቡነ ሚሪዮል የችግረኞቹን ምርጫ አልጠሉትም ። «ይህን አጠራራቸውን እወደዋለሁ» አሉ አንድ ቀን ፣ ብጹዕነትዎ «ከሚሉኝ እንኳን ደህና መጡ ቢሉኝ እመርጣለሁ ።»

— 3 —

አቡነ ሚሪዮል ለጉብኝትና ለመጓጓዣ የተሰጣቸውን አበል ለሌላ ጉዳይ ፣ ማለት ለበጎ ተግባር ያውሉት እንጂ ጉብኝት ከማድረግ አልተገቱም ። የዴ ሰበካ ለወሬ የሚበቃ ሚዳማ ሥፍራ የሌለው ፣ መንገድ ያልተሠራለት 1 ተራራማ አገር በመሆኑ ለጉዞ ፈጽሞ የማያመች ነበር ። ሆኖም ሳለ አቡነ ሚሪዮል በሰበካው ውስጥ በየጊዜው መጎብኘት የሚገባቸው ሠላሳ ሦስት ደብሮች ፣ አርባ አንድ ምክትል ሰበካዎችና ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት የጸሎት ቤቶች ነበሩ ። በቅርብ ያሉትን በእግር ፣ በሩቅ ያሉት



@OLDBOOKSPDF

ንና ጋሪ የሚያስገቡትን በጋሪ ፤ እና በተራራማ ሥፍራ ያሉትን በአህያ እየተጓዙ ይገበኟቸው ነበር ። አመቺ በሚሆንበት ጊዜ ማድሚዜል ባጥቂ ስቲንና ማዳም ማ኷ር ያጅቧቸዋል ። አመቺ በማይሆንበት ጊዜ ግን ብቻ ቸውን ይጓዛሉ ።

አንድ ቀን አህያቸውን አስጭነው ጥንታዊና የኃይማኖት መናኸርያ ወዲ ሆነው ሰኔዝ ከተማ ገቡ ተነሱ ። ኪሳቸው ተራቁቶ ኖሮ ባዶ እጃቸውን ነው የተጓዙት ። ከዚያ ሲደርሱ የሰኔዝ ከንቲባ እስከ ከተማው መግቢያ ድረስ ወጥቶ ተቀበላቸው ። በአህያ ተጓዘው መምጣታቸውን ሲያይ ሀፍ ረት ተሰማው ። ከአህያቸው ሲወርዱ ያዩዋቸውም የከተማው ነዋሪዎች ይስቁባቸው ጀመር ። አቡነ ሚሪዬል ግን በአህያ በመጓዛቸው አላፈሩበ ትም ። እንዲያውም በዚያን ወቅት የተናገሩት ቃል የሚረሳ አይደለም ። «ሙሴ ከንቲባ . . . እናንተም የተከበራችሁ የከተማው ነዋሪዎች . . . » አሉ አቡነ ሚሪዬል ፤ በዚያ ያሉትን ሁሉ በዓይናቸው እየቃኙ ፤ «በአህያ ተጉዤ በመምጣቴ በጣም እንደተገረማችሁ ገብቶኛል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ እንደተጓዘ አስታውሳችሁ እኔም እሱ እንዳደረገው በአ ህያ በመጓዜ እንደትዕቢተኛ ቆጥራችሁኝ ይሆናል ። ነገር ግን ሁኔታው አስገድዶኝ እንጂ በትዕቢት መንፈስ ተነሳስቼ ያደረግሁት አለመሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ።»

አባባላቸው የተለምዶ ነበር ። ገብኝት በሚያደርጉበት ጊዜ በመስ በክ ፈንታ ከሰዎች ጋር መጨዋወት ይመርጡ ነበር ። ጨዋታም በቀላሉ ይመጣላቸው ነበር ። ከአንድ ወረዳ ሕዝብ ጋር ተግናኙተው በሚነጋገሩ በት ጊዜ በሌላ ወረዳ የተደረገውን እንስተው ያወጉ ነበር ። ለምሳሌ ለች ግረኞች ደንታ በሌላቸው ሰዎች መሐከል ሲገኙ እንዲህ ይሏቸዋል ፤ «የብሪያንሶን ሕዝቦች ተመልከቱ . . . የራሳቸውን ሣር ከማጨዳቸው በፊት ፤ የሙት ሊጆችን ፤ ባል አልባ የሆኑ ሴቶችንና የኰስቋሎችን ሣር ሦስት ቀን አስቀድመው ያጭዱላቸዋል ። ያለእንጸቶች ክፍያ መኖርያ ቤታ ቸውን ያድስላቸዋል ። ብሪያንሶ እግዚአብሔር የባረከው አገር ነው ። በአለፉት መቶ ዓመታት በዚህ አገር ውስጥ አንድ ሰው እንኳ በግፍ ተገደለ ሲባል ተሰምቶ አይታወቅም . . . »

ለትርፍና ለግል ጥቅም ብቻ በሚሯሯጡ ሰዎች መሐከል ሲገኙ እን ዲህ ይሏቸዋል ፤ «ለለአንበረ አካባቢ ነዋሪዎች ላውራላችሁ . . . በዚያ አካባቢ አባወራ የሆነ ሰው ብቸኛ የሚሆንበት ጊዜ አለ ። ለምሳሌ ወንድ ልጁ ለበሐራዊ ውትድርና አገልግሎት ይመለመላል ። ወይም ሴት ልጅቹ ከተማውን ለማገልገል ይመረጣሉ ። ወይም ደሞ አባወራው ታምሞ ፥ ድኩም ሆኖ አገመራውን ለመስበሰብ ሳይችል ይቀራል ። እንዲህ ያለ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ የአካባቢው ካህን በዕለተ አሁድ እንዲጸልዩለት ምዕመናኑን ይማጸናል ። ከቅዳሴ በኋላም የአካባቢው ነዋሪዎች በሙሉ ፤ ወንዶች ፥ ሴቶች ፥ ሕጻናት እንኳ ሳይቀሩ ወደ አባወራው ማሳ ወጥተው በወቅቱ መከሩን አጭደው ፥ ወቅተው ይሰበስቡለታል ። እህሉንና ገለባ



@OLDBOOKSPDF

ውን ተሸክመው ይወስዱለታል ። እህሉንም ገለባው ውስጥ ያጨምሩ ለታል ።»

በውርስ ፤ በገንዘብና በንብረት ፣ ሳቢያ የተጣሉ ቤተሰቦቻቸው ያጋጥሟ ቸው እንዲህ ይሏቸዋል ፤ «በደቦልኒ ተራራ ስለሚኖሩት ሰዎች ብነግራ ችሁ ምናልባት አታምኑኝ ይሆናል . . . የደቦልኒ አካባቢ ያልተገሪ አገር በመሆኑ ድምጸ መልካሟ ወፍ «ናይቲንጌል» በአምሳ ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳ ብቅ ብላ ስትዘፍን አትሰማም ። ታዲያ በዚህ አገር አንድ አባት በሞት ሲለይ ከወራሾቹ መሐከል ወንዶቹ የአባታቸውን ንብረት ለእህቶቻቸው ትተውላቸው ሥራ ፍለጋ ወደ ሌላ አገር ይሰደዱ ። ይህንን የሚያደርጉት ለእህቶቻቸው አዛኞች በመሆናቸውና ጥሩ ጥሩ ባል እንዲ መጣላቸው በማሰብ ነው ።»

ጉልበታቸውንና ንብረታቸውን በፍርድ ቤት ክርክር የሚጨርሱትን ባላገሮች ሲያገኙ እንዲህ ይሏቸዋል ፤ «ለምን አታስተውሉም? በኬይራ ሸለቆ የሚኖሩት ባላገሮች አብነት ሊሆኗችሁ ይችላሉ ። ሦስት ሺ የሚሆ ኑት የኬይራ ሸለቆ ነዋሪዎች ራሳቸውን ችለው ይተዳደራሉ እንጂ ለሙ ግዝ አደባባይ አይወጡም ። ዳኛም ሆነ ሕግ አስከባሪ አያሻቸውም ። ማን ኛውንም የአስተዳደር ሥሪ የሚሠራላቸው ከንቲባቸው ነው ። የግምሩክ ቀረጥ ይወስንላቸዋል ። የገቢም ቀረጥ በትክክል ይወስንላቸዋል ። የዳኝ ነት አበል ሳያስከፍል ይዳኛቸዋል ። እንዳችም ዋጋ ሳይጠይቅ ውርስ የሚያ ከፋፍሎውም እሱ ነው ። ለነዋሪዎቹ ደግ ስለሆነ እነሱም ይታዘዙለታል ።»

የአስተማሪ እጥረት ባለበት ቀበሌ ሲገኙ አሁንም የኬይራን አገር ነዋሪዎች በምሳሌነት በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ ፤ «የኬይራ ነዋሪዎች ምን እንደሚያደርጉ ልንገራችሁ . . . ? በዚያ አገር ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት በሚደርሱ ጎጆዎች በአንድ አነስተኛ ቀበሌ የሚኖሩ አርሶ አደሮች አስተማሪ ለመቅጠር አቅም የላቸውም ። ስለዚህ በርከት ያሉ ቀበሌዎች በእንድነት ተባብረው አስተማሪ ይቀጥራሉ ። አስተማሪዎቹም ከአንዱ ቀበሌ ወደ ሌላው ቀበሌ እየተዘዋወሩ ያስተምራሉ ። አንደኛው ዘንድ ሰባት ቀን ፤ ሌላው ዘንድ አስር ቀን እያስተማሩና እንዲሁ እንዲሁ እያሉ ቀበሌዎቹን በሙሉ በየተራቸው ያዳርሷቸዋል ።

«አስተማሪዎቹ በእየገበያውም ይታያሉ ። በአንድ ገበያ ውስጥ እኔ ራሴ አይቻቸዋለሁ ። ምልክት አላቸው ። በባርኔጣቸው ላይ ከላባ የተበጀ ብዕር ይሰካሉ ። ንባብ ብቻ የሚያስተምሩት አንድ ብዕር ይሰካሉ ። ንባብና ስሌት የሚያስተምሩት ሁለት ብዕር ይሰካሉ ። ንባብ ፣ ስሌትና የላቲን ቋንቋ የሚያስተምሩት ደሞ ሦስት ብዕር ይሰካሉ ። እነሱ የሚጠሉት አንድ ነገር ብቻ አለ . . . ማይምነት ! እናንተም እንደ ኬይራ አገር ሰዎች አድርጉ ።»

አቡነ ሚሪዬል ከላይ ባለው መልክ ፤ አብነት የሚሆን ነገር እየጠቃ ቀሱ ይመክራሉ እንጂ ጥሬ ስብከት እጅግም አይሰብኩም ። አብነት የሚ



@OLDBOOKSPDF

ሆን ነገር ከሌላቸው አጠር ያለ ምሳሌ ፈጥረው እንዴ ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ያወጉ ነበር ። በልበ ሙሉነት ስለሚናገሩም አድማጫቸውን ማሳመን አይቸግራቸውም ነበር ።

— 4 —

አነጋገራቸው ደስ ይላል ። አጥንት ዘልቆ የሚገባ በመሆኑም የሰውን መንፈስ ይስባል ። አቡነ ሚሪዬል ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ያያሉ ። ራሳቸውን ከእህታቸውና ከቤት ሠራተኞቸው ደረጃ ይመድባሉ እንጂ የበላያቸው ለመምሰል አይከጅሉም ። ሲስቁም እንደ ታዳጊ ሕጻን ይፍለቀለቃሉ ።

አቡነ ሚሪዬል ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ቢያዩም ሠራተኞቸው ማዳም ማኅር «ታላቅነትም» ብላ የምትጠራቸው ጊዜ ነበራት ። አንድ ቀን ከምቹ ወንበራቸው ተነስተው መጽሐፍ ሰማውረድ ወደ መጽሐፍ መደር ደርያው ሐድ አሉ ። አጭር ስለሆኑ በላይኛው ረድፍ የነበረውን መጽሐፍ ማውረድ ተሳናቸውና ወደ ሠራተኞቸው ዞር ብለው በራሳቸው ላይ እየቀለዱ «ማዳም ማኅር» አሏት ፤ «አስቲ ወንበር አቅርቢልኝ ማዳም ማኅር . . . ታላቅነታቸው የላይኛውን ረድፍ ለመድረስ አልቻሉም ፤»

ማዳም ላኮንቴስ ደሎ የተባለች የሩቅ ዘመድ ነበረቻቸው አቡኑ ። ይህች ሴትዮ ከአቡኑ ጋር በተገናኘች ቁጥር ስለልጆቿ ሳታወራላቸው አታልፍም ። ልጆቿ ሦስት ናቸው ። ሴትዮዋ ብዙ ዘመዶች አሏት ፤ የገረጅፉና ሞታቸውን የሚጠባበቁ ። እነዚህ ስዎች በሞት ሲለዩ ሦስት ልጆቿ የውርስ መብት ነበራቸው ። ትንሽዬው ልጅ ከአያቱ እህት በመቶ ሺ የሚቆጠር ፍራንክ ለመውረስ ፤ ሁለተኛው ከአጎቱ የመስፍንነትን ማዕረግ ለመውረስ ፤ እንዲሁም ታላቅዬው የመኰንንነትን ማዕረግ ከአያቱ ለመውረስ ታጭተው ነበር ። ሴትዮዋ ስለልጆቿ የወደፊት ዕድል በኩራት መንፈስ ስታወራላቸው አቡኑ ሳይሰለቹ በገሞታ ያደምጧት ነበር ። አንድ ቀን እንደተለመደው ስለዚሁ ጉዳይ አውርታ ስትጨርስ አቡኑ የሰሙትን ሁሉ በሃሳባቸው ሲያወጡና ሲያወርዱ ልብ አለቻቸውና «ስለምንድነው የሚያስቡት ?» ስትል ጠየቀቻቸው ። «አንድ ነገር ትዝ ብሎኛ.....» አሏትና «ማለቴ አንድ አባባል . . . በመጽሐፈ አውጉስጢኖስ ያለ ይመስለኛል ። ታሉም እንዲህ የሚል ነው ፡ 'አውራሽህ ባልሆነው በእሱ ላይ ተስፋህን ጣል'»

በሌላ ጊዜ ደሞ የባላባቶች ወገን የነበረ አንድ ጨዋ ሰው መሞቱን ሰሙ ። ማለቂያ የሌላቸው የማዕረግ ስሞቹ በአንድ ሙሉ ገጽ ወረቀት ሠፍረው አዩና በመገረም ፤ «ይህንን ሁሉ የማዕረግ ስም በሚች ላይ መክመር..... መቃብሩ ችሎ አይሸከመውም ፤» አሉ ።



@OLDBOOKSPDF

አቡነ ሚሪዬል የእንጋገር ተሰጥዎ ስለነበራቸው ብዙ ጊዜ ስውር መልእክት ያለውን ቃል ጣል ያደርጉ ነበር ። አንድ ሰሞን በጾም ወራት አንድ ወጣት ካህን ወደ ዴ ክተማ መጥዶ በካቴድራሉ ውስጥ ሰበከ ። በመጠኑም ቢሆን የስብከት ችሎታ ነበረው ። የዚያን ቀን ስብከቱ በሰጋስ ነት አርእስተ ነገር ያተኰረ ነበር ። ገሀነም እሳት ምን ያህል አስከፊ ቦታ መሆኑን፥መንግሥተ ሰማይ ደሞ ምን ያህል የምኞት ቦታ መሆኑን ገለጸና ሀብታሞች ከገሀነም እሳት ስቃይ እንዲድኑና መንግሥተ ሰማያን እንዲ ወርሱ እጃቸውን ፊታ አድርገው ችግረኞችን እንዲረዱ አሳሰባቸው ። ከምዕመናኑ መሐከል ቀደም ብሎ አራጣ አበዳሪ ነጋዴ የነበረ ፥ መናኛ ጨርቅና የሱፍ ጨርቅ እንዲሁም ለስፊት የሚያገለግል ክር ከፋብሪካ አሠርቶ በማውጣትና በመሸጥ ሀብት ሚሊዮን ፍራንክ ያካበተና ስመ ጌቦሮንድ የተባለ ሰው ነበር ። መሴ ጌቦሮንድ በመላ ሕይወቱ አንድ ቀን እንኳ ለድሆች ምጽዋት ሰጥቶ አያውቅም ነበር።የወጣቱን ካህን ስብከት ከሰማ ቀን ወዲህ ግን በየሳምንቱ እሁድ እሁድ ከካቴድራሉ አካባቢ ለማ ይጠፉ ስድስት ተመጽዋቾ ሴቶች አንድ አንድ ሱ ይቸሯቸው ጀመር ። አንድ ሱ የአንድ ፍራንክ አንድ ሀያኛ ስለሆነ በጣም አነስተኛ ገንዘብ ነው ። ታዲያ አንድ ቀን ይህ ሰው ምጽዋቱን ሲያድል አቡኑ ደርሰው ተመልክተውት ፍሮ ወደ እህታቸው ሀር ብለው ፥ «መሴ ጌቦሮንድ መነግሥተ ሰማያትን በቤሳቤስቲ ሲገዛ አየሽ ....!» አሏት ይባላል ።

የችሮታ ነገር አያሰኙላቸውም ። እምቢ ቢባሉ እንኳ ተስፋ ሳይቆርጡ በድሆች ስም ችሮታ ይለምናሉ ። የሰውንም ሕሊና ጠቅ የሚያደርግ ቃል ጣል ያደርጋሉ ። አንድ ቀን በክተማው ውስጥ እንደተለመደው ችሮታ ሲለምኑ ሳሉ ከሻንተርሲዬ መስፍን ጋር ይገናኛሉ ። ይህ መስፍን ፍቅረ ንዋይ ያደረበት ከበርቴ አዛውንት ነበር ። የዘውድ አገዛዝን ይደግፋል ። የቮልቴርንም ፍልስፍና ይደግፋል ። እንደሱ ያሉ ሌሎች ሰምችም አሉ ። ታዲያ ያን ቀን አቡነ ሚሪዬል ከንዴን ነካ ያደርጉትና «ለድሆች የምሰጣ ቸውን ስጠኝ» ይሉታል ። «ደሃ መች ጠፋ . . . . እኔም የማስተዳደራቸው ድሆች አሉኝ» ሲላቸው «እንግዲያውስ ድሆችህንም ጭምር ለኔ ስጠኝ» አሉት ይባላል ።

አንድ ቀን አቡነ ሚሪዬል በካቴድራሉ ውስጥ ተግኝተው ቀጥሎ ያለውን ስብከት አሰሙ ።

«እጅግ የተወደዳችሁ ወንድሞቼና ወዳጆቼ . . . በፈረንሳይ አገር 1,320,000 የአርሶ አደሮች መኖርያ ቤቶች ይገኛሉ ። እያንዳንዳቸው ከሦ ስት በላይ የአየር መግቢያ የላቸውም ። እንዲሁም 1,817,000 ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶች ይገኛሉ ። እያንዳንዳቸው ከአንድ በርና ከአንድ መስኮት በላይ የላቸውም ። በመጨረሻም 346,000 ደሳሳ ጎጆዎች ይገኛሉ ። እነ ዚህም እያንዳንዳቸው ከአንድ በር በስተቀር መስኮት እንኳ የላቸውም ። ይህ የሆነበት ምክንያት መንግሥት የበርና የመስኮት ታክስ ስለሚ ያስከፍል ነው ። ድሆች ፥ አሮጊቶችና ሕጻናት ልጆች በእንደዚህ ያሉ ጎጆ ዎች ውስጥ ተፈጋጥገው ሲኖሩ በጠናቸው ላይ ምን ዓይነት ጠንቅ ለማስ



@OLDBOOKSPDF

ከተል እንደሚችል ልትገምቱ ትችላላችሁ ። እግዚአብሔር አየርን በነጻ የሰጠ ቢሆንም የመንግሥት ሕግ የመስኮትና የበር ታክስ እያሰ በገንዘብ ይሸጠዋል ። ይህንንም ስል ሕጉን ማውጡ አይደለም ፤ እግዚአብሔርን ማመስገኔ እንጂ ።

ዐየድሆች ሁኔታ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም ። በቫር ክፍለ ሀገር በአዜር ኦውራጃ ፤ እና በአልፕ ክፍለ ሀገር በሆትና በባስ አውራጃዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች የሚገፉ ጋሪ እንኳ የላቸውም ። በዚህ ምክንያት አዛባ የሚያገኙት በጀርባቸው ተሸክመው ነው ። ሻማ ለመግዛት የገን ዘብ አቅም ስለሌላቸው ማታ ማታ ጎጆአቸውን የሚያበሩት በሙራሮ እሳት ወይም በጋዝ በተነከረ ገመድ ነው ። ይህ ሁኔታ በመላው ዶጋ አገር ፤ በዶሬ ያለ እንጂ በትንሽ አካባቢ የተወሰነ አይደለም ። ሌላም የሚያሳዝን ነገር አለ ። የዶጋው አገር ነዋሪዎች ለዘይስት ወር የሚበቃቸ ውን ዳቦ በአንድ ጊዜ ይጋግሩታል ። ግን ጂቸውም ከቡት ነው ። በክረምት ወራት ዳበው በመጥረቢያ ካልተፈለጠ በስተቀር በእጅ ሊቆረስ አይች ልም ። ከተፈለጠም በኋላ ለሀያ አራት ሰዓት ውሃ ውስጥ ካልተዘፈዘፈ በስ ተቀር ሊበሰሳ አይችሉም ፤ ጥርስ ይሰብራል ። ወንድሞቼ ሆይ . . . ለእነ ዚህ ሰዎች እዘኑላቸው ። በአካባቢያችሁ የመከራ ኑሮ የሚኖሩትንም ብዙ ሃን አትርቧቸው ።»

አቡነ ሚሪዬል በደብብ ክፍለ ሀገር ተወልደው ስላደጉ እንደገጠሬው ሕዝብ ይናገራሉ ። በቀበልኛ ቋንቋ ስለሚናገሩም የሕዝቡን ልብ ይማር ካሉ ። ወደዶጋው አገር በሚወጡበት ጊዜም ሆነ በገበሬ ጎጆ በሚገኙበት ወቅት ባይተዋርነት አይሰማቸውም ። ማንኛውንም የረቀቀ ሃሳብ ባልተ ገራ የገጠር ቋንቋ መግለጽ ስለሚሆንላቸው ከማናቸውም ሰው ጋር መግ ባባት ተስኗቸው አያውቅም ።

በተጨማሪም ስደላቸውም ሆነ ለሕግረኞች ያው ናቸው ። በአቀራረ ባቸው ልዩነት አያሳዩም ። አንዳችም ነገር ሳያመነታኑ በችኮላ አያወግ ዙም ። ይህንን በሚመለከት ፤ ጠፋት ከተሠራ የጥፋቱን መስመር ልብ ብላችሁ መርምሩ ይሉ ነበር ።

አቡነ ሚሪዬል በወጣትነታቸው ዘመን አለመኛ ስለነበሩ ጋጠኦት ምን እንደሆነ ያውቃሉ ። በሀጢአተኛ ላይ ለመፍረድም አይፈልጉም ። ጋጠአትን በሚመለከት እምነታቸው ባጭሩ እንዲህ የሚል ነበር ፤

ዐሰው ሥጋ ለባሽ ነው ። ሥጋው ሸክሙም ፈተናውም ነው ። ከሥ ጋው ርቆ ለመኖር አይችልም ። ለሥጋውም ይሸነፋል ። ሥጋውን መቆጣጠ ርና በመንፈሱ ሥር አንዲውል ማድረግ ይገባዋል ። ሌላ አማራጭ አጣ ካልሆነ በስተቀር ለሥጋው መታዘዝ ፈጽሞ አይገባውም ። አማራጭ አጥቶ ለሥጋው ቢታዘዝ እንኳ ስህተት አልሠራም ማለት አይደለም ። ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነት ስህተት ይቅርታ የማያሰጥ አይደለም ። በአርግጥ


@OLDBOOKSPDF

ውድቀት ነው ። ይሁን እንጂ ውድቀቱ ወደ ጸሎት ጉዳና ሊመራው ይችላል ።

«ጻድቅ መሆን በጣም ያስቸግራል ። ትክክለኛ ሰው መሆን ግን እስከ ዚህም አስቸጋሪ አይደለም ። ራስህን መቆጣጠር ካልቻልክ ስህተት ሥራ ፣ ውደቅ ፣ ኃጢአተኛ ሁን ። ነገር ግን ሁልጊዜም ትክክለኛ ሰው ለመሆን ጣር ።

«ኃጢአት መሥራት ከሰው ባህርይ ጋር የተቆራኘ እንደመሆኑ መል አክ ካልሆነ በስተቀር ኃጢአት የማይሠራ ሰው የለም ። ዓለም ከኃጢአት ነጻ ስመሆን አይችልም ። ኃጢአት እንደመሬት ስበት ያለ ኃይል ነውና ።»

ሰዎች ሲንጫጩና ትዕግሥታቸው ተሚጥጦ ሲናደዱ ሲያዩ ፈገግ ብለው እንዲህ ይሉ ነበር ፤ «ይሽኩ ማናቸውም ሰው ሊፈጽመው የሚችል ዓይነት ስህተት ይመስለኛል . . . ግብዝነትን ሰመሸፈን ያህል የሚደረግ ስህተት ።»

የሕበረተሰቡ ዋልታ ስሆኑት ፤ ለድሆችና ለሴቶች አዛኝ ስለነበሩ እንዲህ ይሉ ነበር ፤ «ሴቶችን ፣ ልጆችን ፣ ደካሞችን ፣ ድሆችንና አላዋቂ ዎችን አትውቀሱ ። መውቀስ የሚገባችሁ ባሎችን ፣ አባቶችን ፣ ጌቶችን ፣ ኃይለኞችን ፣ ከበርቴዎችንና አዋቂዎችን ነው ።»

በተጨማሪም እንዲህ ይሉ ነበር ፤ «አውቀት የሌላቸውን በተቻለ መጠን አስተምሯቸው ። ያልተማሩትን በነጻ የሚያስተምር ሕበረተሰብ ጥፋተኛ ከመሆን አይድንም ። የድንቁርና ጨለማ ቢኖር ኃላፊው ሕበረ ተሰቡ ነው ። የአውቀት ብርሃን በሌለበት ኃጢአት ይነግሳል ። ለዚህም ተጠያቂው የድንቁርና ጨለማ ሳያስወግድ የቀረው ሰው እንጂ ኃጢአት የፈጸመው አይደለም ።»

አቡነ ሚሪዬል ከሰው ሁሉ የተለየ አመለካከት ነበራቸው ። የአመ ለካከታቸውም ምንጩ ቃለ ወንጌል ሳይሆን አይቀርም ።

አንድ ቀን ስለአንድ ወንጀል ሲወራ ጆሮአቸውን ጣል አርገው ይሰ ማሉ።አንድ መከረኛ ሰው እጅ ቢያጥረው ሕገ ወጥ ገንዘብ ሠርቶ ያወጣል። ፍቅረኛ አለችው ። አንድ ሕጻን ልጅ ወልዳለታለች ። ለፍቅረኛውና ለሕ ጻን ልጁ በማሰብ ነበር ወንጀሉን የፈጸመው።በዚያን ዘመን ሕገ ወጥ ገንዘብ ሠርቶ ማውጣት በሞት የሚያስቀጣ ከባድ ወንጀል ነበር ። ሰውዬው ሠርቶ ባወጣው ሕገ ወጥ ገንዘብ ፍቅረኛው የሆነችው ሴት ስትገበያይበት ተያዘች ። ክስ ተመሠረተባት ። ገንዘቡን እኔ ሠርቼ አላወጣሁትም ስትል ተከራከረች ። አቃቤ ሕጉ አንቺ ነሽ ሠርተሽ ያወጣሽው ሲል አጥብቆ ወነጀላት ። እሷ ግን መልሳ ካደች ። አቃቤ ሕጉ ሰውዬውን ወንጅሎ ለፍ ርድ እንዳያቀርበው የተጨበጠ ማስረጃ አልነበረውም ። ስለዚህ ሴቲ የሞን ለማወጣጣት ሌላ ብልሃት ፈጠረ ። ሰውዬውንና ሴትዬዋን ለማቃቃር አስቦ



@OLDBOOKSPDF

ሰውዬው ሌላ ፍቅረኛ ያለው ለማስመሰል ሐሰተኛ ደብዳቤዎችን አስጽፎ ለሴትዮዋ አሳያት ። ሴትዬዋ ደብዳቤዎቹን ስታይ ፍቅረኛዋ በእርግጥም ሌላ የሴት ወዳጅ ያለው መስሏት ተናደደች ። በጣም ተናች ። አሳልፋ ልትሰጠውም ወስና እውነቱን ተናዘዛ ማስረጃም አቅርባ ፍቅረኛዋ ሕግ ፊት እንዲቀርብ አደረገች ።

ስለወንጀሉ የሰሙ ሰዎች በጉዳዩ በሞቀ ሁኔታ ሲከራከሩበት ፣ አቃቤ ሕጉም በፈጠረው ብልሃት ሴትዬዋ እውነቱን እንድትናዘዝና ዋናው ወንጀለኛ ተይዞ ለፍርድ እንዲቀርብ በመታዘዙ ሲያደንቁት አቡነ ሚሪዬል በገዘታ ሲያዳምጡ ቆይና በመጨረሻም «ለመሆኑ ሰውዬውና ሴትዬዋ ለፍርድ የሚቀርቡት የት ነው ?» ሲሉ ጠየቁ ።

«ኤክስ ከተማ ውስጥ ነዋ . . . ! ወንጀለኛ ፍርድ ቤት . . . !»

«እሱስ ይሁን . . . ብቻ . . . አቃቤ ሕጉ ራሱ ለፍርድ የሚቀርበው የት ነው ?» ሲሉ መለሱ ይባላል ።

በሌላ ጊዜ በዬ ከተማ ውስጥ አንድ ከባድ ወንጀል መፈጸሙ ተወራ ። አንድ ሰው የሰው ሕይወት አጥፍቶ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ። ወንጀሉ ኛው የተማረም የማይባል ፣ ያልተማረም የማይባል ጥራዝ ነጠቅ ነበር ። የሚተዳደረው ሕዝብ በተሰበሰበበት ሁሉ እየዘረ መናኛ ዕቃ በመሸጥ ፣ አንዳንድ ጊዜም ለሕዝብ ማመልከቻ በመጻፍ ነበር ። ወንጀለኛው በሚሰቀልበት ቀን ዋዜማ እስረኞችን የሚያጽናኑት የወህኒ ቤቱ ቄስ ታመሙ ። በዚህ ምክንያት ወንጀለኛውን የሚያጽናና ሌላ ቄስ እስፈለገና የአንድ ደብር ቄስ ተጠሩ ። የደብሩ ቄስ «ይህንን ዓይነት ወንጀለኛ ለማጽናናት ፍላጎት የለኝም ። ደሞም እኔንም አሞኛል ። ሰመሐድ አልችልም ። በተጨማሪም የወህኒ ቤቱ ሥራ እኔን የሚመለከት አይደለም» ሲሉ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገለጹ ። አቡኑ ይህንን ወሬ ሲሰሙ ቄሱን በመገሰጽ ፈንታ «በእርግጥም እስረኛው ያለበት ሥፍራ የደብሩን ቄስ የሚመለከት አይደለም ። ጉዳዩን ለኔ ተዉልኝ» በማለት ወዲያውኑ ወደ እስር ቤቱ አመሩ ። ወንጀለኛው ወደታሠረበት አነስተኛ ክፍል ገብተው ፣ ስሙን ጠርተው ፣ እጁን በሞቀ ሁኔታ ይዘው አነጋገሩት ። መሉውን ቀን እህል ሳይቀምሱና እንቅልፍም ሳይተኙ ለሰውዬው እግዚአብሔርን ሲማጸኑና ሲጸልዩ ከሉው ጋር ዋሉ ። ሰውዬውም ነፍሱ ትድን ዘንድ እንዲጸልይ ለመኑት ። እውነት ምን እንደሆነ አስረዱት ። ብዙ ነገር አስተማሩት ። ብርታትም እንዲያገኝ መከሩት ። ሰውዬው ቀን ጨለመበት ነበር ። ሞትን እጅግ አድርጎ ፈርቶ ስለነበረ የሞትን ጽዋ መቅመስ ፈጽሞ የማይዋጥለት እጅግ መራራ ነገር ሆኖበት ነበር ። ከሞት ጋር ስለተፋጠጠም ለመኖር የነበረው ፍላጐት እጅግ የበረታ ነበር ። ከዚህ ዓለም ማዶ አሻግሮ ሲመለከት የቃለማ አዘቅት እንጂ ሌላ ነገር አይታየውም ነበር ። አቡኑ ግን አጽናንተው የብርሃን ጮራ እንዲያይ አደረጉት ።



@OLDBOOKSPDF

ወንጀለኛው የሞት ቅጣት በሚፈጸምበት ቀን ሰዎች መጥተው ይዘ
ውት ሲወጡ አቡኑ ተከትለውት ወጡ ። በአንገታቸውና በትከሻቸው ላይ
ሐምራዊ ቀለም ያለው ጨርቅ ለብሰው ፣ የአቡን መስቀል በአንገታቸው
አንጠልጥለው የፊጥኝ የታሠረውን እስረኛ ተከትለው ሲወጡ በዚያ የተ
ሰበሰበው ሕዝብ በመገረም ይመለከታቸው ነበር ። እስረኛው ከማንገጥው
ጋሪ ላይ ሲወጣ አቡኑ አልተለዩትም ። ተከትለውት ጋሪው ላይ ወጡ ።

የእንጉት መቅሊያው ከነበረበት ቦታ ደርሰው እስረኛው ከመቅሊያው
መድረክ ላይ ሲወጣ አቡኑ አሁንም አልተለዩትም ። አብረውት ወጡ ።
በትናንትናው ዕለት ቀን ጨልሞበት የነበረው ይህ መከረኛ ሰው የመጣ
ደያው ሰዓት በተታረበበት በአቡኑ ወቅት ፊቱ በርቶ ይታይ ነበር ። ከእማ
ዚአብሔር ጋር የታረቀ መስሎ ታየው ። ብሩህ ተስፋም አደረበት ። የአ
ንገት መቅሊያው ስለት ወርዶ አንገቱ ላይ ከማረፉ በፊት አቡኑ ሳመትና
እንዲህ አሉት ፣ «ሰው የገደሰውን እግዚአብሔር ከሞት ያስነሳዋል ። ወን
ድሜ የሸሸት ሰው እግዚአብሔርን መልሶ ያገኛል ። ጸልይ ፣ እመን ፣
ወደ ሕይወት ዓለም ግባ ። አባታችን እግዚአብሔር ያለው ከዚያ ነውና ።»

አቡኑ ይህንን ብለው ከመድረኩ ሲወርዱ ሕዝቡ ገለል አሰላቸው ።
በገጻቸው ላይ አንዳች የሚነበብ ነገር ነበረበት ። የመንፈስ ርጋታ ኖሯል
ወይስ ሌላ ? በውል አረጋግጠ ያወቀ ሰው አልነበረም ። ለዓይን ከማይሞላ
ውና አሳቸው ግን «ቤተ መንግሥቱ» ብለው ከሚጠሩት መኖሪያ ቤታ
ቸው ሲመለሱ እህታቸውን አየት አደረጉና «ማዳኜን ፈጽሜ መጣሁ»
አሏት ።

ክቡር ሥራ ምን እንደሆነ ያልተረዱ አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች
የአቡኑን ድርጊት ከተመለከቱ በኋላ ፣ «እሳቸው ሰው ጤና አይደሉም !» ከማ
ለት አልተቆጠቡም ። የተቀደሰ ሥራ ምን እንደሆነ የተገነዘቡት ግን በአ
ቡኑ ድርጊት በጣም ተነኩ ። በየልባቸውም አደነቋቸው ።

አቡኑ በበኩላቸው «ጊለሞቲን» የተባለውን የእንጉት መቀርጠፊያ
መሣርያ በማየታቸው እጅግ በጣም ተሰቀጠጡ ። ለረጅም ጊዜ ከአእምሯ
ቸው አውጥተው ሊጥሉትም ሳይችሉ ቀሩ ።

በእርግጥም መሣሪያው መድረክ ላይ ተተክሎ ሲታይ በሰው ሕሊና
ውስጥ ቅዠት ን የመሰለ ነገር ይፈጥራል ። መሣሪያውን እስካላዩት ድረስ
የሞት ቅጣት ብያኔ እጅግም ላያስደነግጥ ይችላል ። ስለቱን በገዛ ዓይን
ካዩ በኋላ ግን ከመሸበር ለመዳን አይቻልም ። እንደ ዲ ሚስትር ያሉ እን
ዳንድ ሰዎች የእንጉሉ መቀርጠፊያውን መሣሪያ ያደንቁታል ። እንዴ
ቤክርያ ያሉት ሌሎች ሰዎች ግን በልባቸው ያወግዙታል ። አስፈሪውን
መሣሪያ ያየ ማናቸውም ሰው አቋም ሳይወስድ ለመቅረት አይቻለውም ፣
ወይም ያደንቀዋል ፤ ወይም ያወግዘዋል ። መሣሪያው የሕግ ቋሚ ሐው
ልት ነው ለማለት ይቻላል ። ሐውልቱም ቅጣት በሚል ስያሜ ይጠራል ።
ያየው ሰው ሁሉ ይርበደበዳል ። ሕዝቡ ተሰብ ነክ የሆኑ ጉዳዮች የሚሸከ



@OLDBOOKSPDF

ረክሩ። በሱ ዙሪያ ነው። የመቅለያው መድረክ ራሱ በሰው ልቦና ውስጥ ልዩ የሆነ ስሜትን ይፈጥራል። ራሱን የቻለ ግርማት ነው ለማለት ይቻላል። ምንም እንኳ በአናጢ እጅ፤ ከእንጨት፥ ከብረትና ከገመድ ተሠርቶ የተዘጋጀ ቢሆንም እንደተራ ግዑዝ ነገር የሚቆጠር አይደለም።

መድረኩ በአንዳች ከዩሲ ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ሕያው ነገር ይመስላል። እንደሕያውም ፍጡር የሚያይ፥ የሚሰማ፥ የሚያስብ፥ የራሱ የሆነ ፈቃድ ያለው ይመስላል። የሞት ቅጣቱን ከሚያስፈጽመው ሰው ጋር የሚያብር፥ የጭራቅም ባህርይ ያለው ይመስላል። እንደጭራቅ የሰውን ሥጋ ይበላል። እንደ ጭራቅ የሰውን ደም ይጠጣል። የበላው ሥጋና የጠጣው ደም ያሳሳዋል። ጥንካሬና ኃይልም ይሰጠዋል።

በዚህ ሁሉ ምክንያት አቡነ ሚሪዬል «ጊሎቲኑ»ን ካዩበት ዕለት ጀምሮ ለብዙ ቀናት ስቅጥጥ ብለው ሰነበቱ። ቀደም ብሎ የነበራቸው ርጋታ ሁሉ እንዳልነበረ ሆነባቸው። ስብእዊ ፍትህ ምንድነው የሚል ሃሳብ በእምሮአቸው ውስጥ ገቢዮ መንፈሳቸውን ያውከው ጀመር። በተለምዶ፥ በፈጸመት ተግባር ርካታ ይሰማቸው ነበር። አሁን ግን ራሳቸውን ይወቅሱ ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ብቻቸውን ይናገሩም ጀመር። አንድ ቀን ብቻቸውን ሲናገሩ እህታቸው ሰማቻቸው። እንዲህ ሲሉ ነበሩ፤ «መሣርያው እንዲህ ያለ አስቃቂ ነገር አይመስለኝም ነበር። በመንፈሳዊ ሥራ ተውጠው በመኖሬ ነው እስከዛሬ ድረስ ሳላየው የኖርኩት። ነገር ግን የሰውን ፍትህ አስከመርሳት ድረስ በእግዚአብሔር ፍትህ ተውጠ መቅረት ትክክል አይደለም። የሰውን ሕይወት ለመውሰድ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሰው በዚህ ሥልጣን ጣልቃ መግባት አይገባውም . . .»

ጊዜው ወሎ ሲያድር ይህ ሁሉ አስተሳሰባቸው እየተረሳቸው ሔደ። ይሁን እንጂ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው አገዛት ከሚቀላበት አካባቢ መግኘትን አቆሙ።

ሰው ሲታመምና በጣር ላይ ሲገኝ በማናቸውም ሰዓት ይጠሩ ነበር። ግዳጃቸው ስለሆነም ፈጥነው ይሔዱ ነበር። የሙት ቤተሰብ ካለበት አካባቢ ግን እስኪጠሩ ድረስ አይጠብቁም። በገዛ ፈቃዳቸው ሔደው የሚኙን ቤተሰብ ያጽናናሉ። ዝም ማለት በሚገባቸው ወቅት ዝም እንደሚሉ ሁሉ መናገር በሚገባቸውም ወቅት ይናገራሉ። ሐዘንተኞችን በሚያጽናኑበት ሰዓት ሐዘንተኞቹ ሐዘናቸውን እንዲረሱ በመምከር ፈንታ ሐዘኔታው የተሰፋ ምንጭ መሆኑን አጥልተው ያስረዳሉ፤ እንዲህ እያሉ፤ «ስለመታን በምታስበበት ጊዜ አንድ ነገር ልብ በሉ። ጠፊ ስለሆነ ነገር አታስቡ። አርቃችሁ ተመልከቱ። መታን በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ ሕያው ብር ሆን እንደሚገናጸፉ አትርሱ።»



@OLDBOOKSPDF

የአቡነ ሚሪዩል የግል ሕይወት ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ተነጥሎ የሚታይ አልነበረም ። በድህነት ለመኖር ፈቃደኛ ስለነበሩ ኑሮአቸው በእርግጥም ተራ የሆነና የድህነት ኑሮ ነበር ።

ሽማግሌዎችና ፈላስፎች በእንቅልፍ የሚያሳልፉት ጊዜ አጭር እንደ መሆኑ መጠን አቡነ ሚሪዩልም በየቀኑ በእንቅልፍ የሚያሳልፉት ጊዜ በጣም አጭር ነበር ። ከተኙ ግን ጥልቅ የሆነ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል ። በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ከሰው ነጠል ብለው ለአንድ ሰዓት ያህል ጊዜ የሕሊና ምርመራ ያደርጋሉ ። ያስባሉ ፣ ያሰላስላሉም ። ተጥለውም ወደካቴድራሉ ሒደው አለዚያም ወደ ጸሎት ቤታቸው ገብተው ይቀድሳሉ ። ከቅዳሴ በኋላ ቁርሳቸውን ይበላሉ . . . ዳቦና ወተት ። ወተቱ ከገዛ ላሞቻቸው የሚታለብ ነበር ። ከቁርስ በኋላም ሥራ ይጀምራሉ ።

የአቡን ሥራ ዓይነቱ ብዙ ነው ፡— በየቀኑ የሰበካውን ጸሐፊ ተቀብሎ ማነጋገር . . . በየጊዜው የሰበካውን ምክትል አስተዳዳሪዎች ተቀብሎ ማነጋገር . . . አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ምዕመናኑን መምከርና መገሰጽ . . . እንዲሁ አልፎ አልፎ ሌሎች ሰዎችን ተቀብሎ ማስደሰት . . . በቤተ መጻሕፍት ያሉትን መንፈሳዊ መጻሕፍት (ትምህርተ ክርስቲያን ፣ የጸሎት መጻሕፍት ፣ ወዘተርፈ.) ማየትና መመርመር . . . መመሪያዎችን በጽሑፍ ማዘጋጀት . . . በክህናት የተዘጋጀውን ስብከት ማጽደቅ . . . በክንቲባዎችና በካህናት መሐከል አለመግባባት ሲፈጠር እነዚህን ማስታረቅ . . . መንፈሳዊም ሆነ አስተዳደር—ነክ የሆኑ ደብዳቤዎችን ጽፎ ማዘጋጀት . . . ሌሎችም በርካታ ሥራዎች . . .

አቡነ ሚሪዩል እነዚህን ሁሉ ካከናወኑና በየዕለቱ እንደሚያደርጉትም መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ከፍተው ካነበቡ በኋላ ቀሪ ጊዜአቸውን በሽማግሌዎች ፣ በሕመምተኞችና በሀዘንተኞች ጉዳይ ያሳልፉታል ። ተጥሎም በግል ሥራቸው ላይ ያተኩራሉ ። አንዳንድ ጊዜ የአትክልቱን ቦታ ይኖ ጥራሉ ፣ ይኮተኩቱታልም ። አእምሮአቸውንም እንደአትክልት ቦታ ስለሚቆጥሩትና «መኰትኰት ይገባዋል» ስለሚሉ መጽሐፍ ያነብባሉ ፣ ይጽፋሉም ።

አየሩ ጥሩ በሚሆንበት ወቅት እኩለ ቀን ላይ ከዘራቸውን ይዘው ለሽርሽር ይወጣሉ ፣ ወደከተማ ወይም ወደገጠር ። ብቻቸውን ነው የሚን ሽረሸሩት ፣ አንገታቸውን ወደመሬት ደፍተው እያሰቡ ። ሽርሽር በሚወጡበት ጊዜ የሚለብሱት ልብስ ከሐር የተሠራና ሐምራዊ ቀለም ያለው ፣ የተጨማደደ ቢሆንም የሚያሞቅ የካህን ልብስ ነበር ። እንዲሁም ሐምራዊ ቀለም ያለው የእግር ሹራብና ሽካራ ጫማ ያደርጋሉ ። በራሳቸው ላይ ባርኔጣ ይደፋሉ . . . ባለሦስት መርገፍ ባርኔጣ ። መርገፎቹ ወርቃማ ናቸው ።



@OLDBOOKSPDF

በመንገድ ያገኛቸው ሰው ሁሉ በደስታ ይቀበላቸዋል ። ያሉበት አካባቢ ሁሉ የሞቀና ብርሃን የተመላበት ነበር ለማለት ይቻላል ። ሕጻናት ልጆችና ሽማግሌዎች እሳቸውን ሲያዩ ተሽቀዳድመው ወጥተው ይቀበሏቸዋል ። እሳቸውም ይባርኳቸዋል ። አቡነ ሚሪዮል ሕጻናትን አይተው አያልፉም ፤ ቆም ብለው ያነጋግሯቸዋል ። ከእናቶቻቸው ጋር ከሆኑም ወደ እናቶቻቸው እያዩ ፈገግ ይላሉ ። ሽርሽር በሚሔዱበት ወቅት በመንገዳቸው ደሳሳ ጎጆ ካዩ ጐራ ይላሉ ። ገንዘብ ባላቸው ጊዜ ድሆችን ይጐበኛሉ ። ገንዘብ በሌላቸው ጊዜ ግን ሀብታሞችን ይጐበኛሉ ።

ቀሚሳቸው በጣም ያረጀና የነተበ በመሆኑ ሐምራዊ ቀለም ያለውና ጭምድድ ያለው ካባቸውን ሳይደርቡ አይወጡም ነበር ፤ አሮጌውን ቀሚስ ከሰው ዓይን ለመሰወር ያህል ። ስለሆነም በበጋው ወራት ካባ መደረባቸው አያገናናቸውም ነበር ።

ከሽርሽር ሲመለሱ ምሳቸውን ይበላሉ ። አውንም ዳቦና ወተት ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከአህታቸው ጋር ሆነው ራታቸውን ይበላሉ ። የተለምዶ አራታቸው ጎመንና በዘይት የተሠራ ቆርባ ነበር ። ማዳም ማኂር ከበስተኋላቸው ቆማ ታበላቸዋለች ። ምግቡ ሁሉ በቁጠባ የተያዘ ነበር ። አቡነ ሚሪዮል እንግዳ በሚጋብዙበት ጊዜ ግን ማዳም ማኂር ይህንኑ ምክንያት በማድረግ የሐይቅ አሳ ወይም የአደን ሥጋ አዘጋጅታ ታቀርብላቸው ነበር ። አልፎ አልፎ የሚያረግና እንግዶቻቸውንም የሚያስደስት በመሆኑ አይቃወሙትም ነበር አቡኑ ።

ከራት በኋላ ለግማሽ ሰዓት ያህል ጊዜ ከማድሚዜል ባፕቲስቲንና ከማዳም ማኂር ጋር ይጨዋወታሉ ። ጭውውቱ ሲያበቃ ወደ ክፍላቸው ገብተው ብትን ወረቀት አውጥተው በሃሳባቸው ያሰቡን ይጻጽፋሉ ። በጻፉበት ገጽ ላይ ቀለም ባልወደቀበት ሥፍራ ፤ ማለት በዳርቻና በዳርቻው ተጨማሪ ሃሳብ የሚያክሉበት ጊዜም ነበራቸው ። አቡኑ ምሁር ናቸው . . . የቀለም ሰው ። አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ምሁራዊ ድርሰቶች ነበሯቸው ። አንደኛው ድርሰታቸው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስነ ፍጥረት በተሰኘው ክፍል «በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃዎች ፊይ ሰፈፈ» በሚለው ግጥም ላይ ያተኰረ ትንተና ሆኖ ይህንኑ ከሌሎች ምስት ግጥሞች ጋር ያነጻጽሩታል ፤ ማለት «የእግዚአብሔር ነፋሱ ነፈሱ» ከሚለው ከአረብኛው ግጥም ጋር ፤ «ከላይ የመጣው ነፋስ በምድር ላይ ፈጣኖ ነፈሰ» ከሚለው ከፍላቪዩስ ጆዜፉስ ግጥም ጋር እና «ከእግዚአብሔር የመጣው ነፋስ በውሃዎች ላይ ነፈሰ» ከሚለው በካልዲያ ቋንቋ አንኬሎስ ከቀረበው ግጥም ጋር ። በሌላ ምሁራዊ ድርሰታቸው ውስጥ የኢጎን የቴዎሎጊ ሥራዎች ይመረምራሉ ። ኢጎ የቶማይ አቡንና የ«መከረኞች» ደራሲ ቅድመ አያት ናቸው ። አቡነ ሚሪዮል ስለአቡነ ኢጎ ሥራዎች በሚተነትኑበት ጊዜ ባለፈው ምዕተ ዓመት አቡነ ኢጎ «ባርሴኪር» በሚል የብዕር ስም በርከት ያሉ ጽሑፎች አሳትመው እንዳወጡ ይናገራሉ ።

መጽሐፍ በሚያነብቡበት ወቅት ሳይታወቃቸው ከሃሳብ ባሕር ውስጥ ሰጥመው የሚቀሩበት ጊዜ ነበራቸው ። ከስጠመቡት የሃሳብ ባህር



@OLDBOOKSPDF

ሲወጡም በያዘት መጽሐፍ ዳርቻና ጸርቻ ፤ ማስት ቅስም ባልወደቀበት ሥፍራ በሃሳባቸው የመጣላቸውን ያሠፍሩበት ነበር ። ይህንን የሚያደር ጉት በማንኛውም መጽሐፍ ገጽ ላይ ነበር ። የሚያሠፍሩትም ጽሑፍ አብዛ ኛውን ጊዜ ከሚያነብቡት መጽሐፍ ይዘት ጋር አንዳችም ግንኙነት አልነ በረውም ። ለምሳሌ ያህል በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ቀጥሎ ያለውን አሠ ፈሩበት ፤

«ጌታ ሆይ !

መጽሐፈ መክብብ 'ሁሉን የሚችል' ብሎ ይጠራሃል ። የማኳቤ ሰዎች 'ፈጣሪ' ብለው ይጠሩሃል ። ለኤፌሶን ሰዎች የተጻፈው መልእ ክት 'ነጸነት' ብሎ ይጠራሃል ። ባሩክ 'ወሰን የሌለው' ብሎ ይጠራሃል ። መጽሐፈ መዝሙር 'ጥበብና እውነት' ብሎ ይጠራሃል ። የሐንስ 'ብርሃን' ብሎ ይጠራሃል ። መጽሐፈ ነገሥታት 'ጌታ' ብሎ ይጠራሃል ። መጽሐፈ ምጽአት 'የሰማዩ ጌታ' ብሎ ይጠራሃል ። ሴቭቲክስ 'ቅድስና' ብሎ ይጠራ ሃል ። ኤስድራስ 'ፍትሃ' ብሎ ይጠራሃል ። ስነ ፍጥረት 'እግዚአብሔር' ብሎ ይጠራሃል ። ሰው 'አባት' ብሎ ይጠራሃል ። ሰለሞን 'አባኻ' ብሎ ይጠ ራሃል ። ከመጠሪያምችህ ሁሉ የተዋበው ይኸው 'አባኻ' የሚለው ነው ።»

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ግድም ሲሆን ሚድሚዚል ባፕቲስቲንና ማዳም ማሏር ወደ ቦቱ ሲወጡ አቡነ በምድር ቤቱ ባለው ክፍላቸው ውስጥ እስክ ንኃቱ ይቆዩ ነበር ።

እዚህ ላይ የአቡነ ሚሪዬል መኖሪያ ቤት ምን እንደሚመስል በዝር ዝር መግለጽ ይገባል ፡

— 6 —

ሕንጻው ከታች ሦስት ክፍሎች ከላይ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሆኖ በተጨማሪም ከፎቱ ጣራ ጥግ ለዕቃ ማከማቻ የሚያገለግል ፡ «አቲክ» ተብሎ የሚጠራ አንድ አነስተኛ ክፍል አለው ።

በፎቱ ላይ ያሉት ሦስት ክፍሎች የሚድሚዚል ባፕቲስቲንና የማ ዳም ማሏር መኖሪያ ቤቶች ሲሆኑ በምድር ቤት ያሉት የአቡነ ሚሪዬል መኖሪያ ናቸው ። አንደኛው ምግብ ቤታቸው ፡ ሁለተኛው መኝታ ቤታ ቸው ፡ ሦስተኛው የጸሎት ቤታቸው ። መኝታ ቤታቸውንና የጸሎት ቤታ ቸውን የሚያገናኝ በር አለ ። ነገር ግን ወደ ውጭ ፡ ወደ ምድረ ግቢው የሚያስወጣ በር ሁለቱም የላቸውም ። ወደ ውጭ የሚያስወጣ በር ያለው ምግብ ቤቱ ብቻ ነው ። ስለዚህ ከመኝታ ቤቱና ከጸሎት ቤቱ ወደ ምድረ ግቢው ለመውጣት ቢያስፈልግ በምግብ ቤቱ በኩል ማለፍ ግዴታ ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

በጸሎት ቤቱ ውስጥ ነጠል ያለና አንድ አልጋ ሊያስዘረጋ የሚችል ባዶ ሥፍራ አለ ። አቡነ ሚሪዬል እንግዳ ሲኖራቸው ለምሳሌ አንድ የገጠር ቄስ በሥራ ምክንያት ወደ ደ/ ከ/ማ መጥተው እሳቸው ዘንድ ማረፍ ቢኖርባቸው መኝታ የሚዘጋጅላቸው ከዚያ ነበር ። ከዚሁ ከመኝታ ቦታ አጠገብ አንድ ወንበር አለ ፤ መቀመጫው ግር የተሰነሰገበት ። ለዚሁም የተሰነሰገው ግር በከፊል ወጥቶ የተቡተነ ስለሆነ ምቹነቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ በምናብ ማየት አያስችግርም ። በተጨማሪም ከወንበሩ እግሮች አንዱ ተሰብሮ ስለወደቀ ግድግዳውን ካላስያዣት በስተቀር ወንበሩ ለመቆም አይችልም ። ከሰባራው ወንበር ሌላ በጸሎት ቤቱ ውስጥ ከግር የተሠሩ ሁለት መንበርከኪያዎችና አንድ ጠረጴዛ አለበት ። ጠረጴዛው በጨርቅ ተሸፍኗል ። ጨርቁም ጥልፍ ቢጤ አለበት ። የጸሎት ቤቱ መቅደስ መሆኑ ነው ።

የደ/ ከ/ማ መንፈሳዊ ሴቶችና አንዳንድ ከበርቴ ምዕመናን ለአቡኑ ጸሎት ቤት የሚሆን መቅደስ ማሠርያ ገንዘብ ከአንድ ሁለቴም አዋጥተው ለአቡኑ አስረክበዋቸው ነበር ። አቡኑ ግን የተቀበሉትን ገንዘብ ለታሰበለት ሥራ በማዋል ፈንታ ለችግረኞች አደሉት ። ስለዚህ ጉዳይ ሲያነሱባቸው ፤ «ከሁሉም የተዋበው መቅደስ ከህዘኑ የሚጸናናና እግዚአብሔርን የሚያመሰግን የሰው ልብ ነው» ይሉ ነበር ።

የምግብ ቤቱ ዕቃዎች አንድ ጠረጴዛ ፡ አንድ «ቡፌ» እና አራት ወንበሮች ብቻ ናቸው ።

የአቡኑ መኝታ ቤት ሰፋ ያለ ሆኖ በውስጡ አንድ አልጋ አለበት ። ከላይ ከአረንጓዴ ጨርቅ የተሠራ ከለላ ተደርጎለታል ። ከአልጋው በስተጀርባ መጋረጃ ፡ ከመጋረጃው በስተጀርባ ለፊት እንከብካቤ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ይገኛሉ ። አቡነ ሚሪዬል በወጣትነት ዘመናቸው ዓለመኛ ስለነበሩ እነዚህ የፊት እንክብካቤ መሣሪያዎች የዚያን ጊዜ ማስታወሻ ዎታቸው ሳይሆኑ አይቀሩም ።

በመኝታ ቤቱ ውስጥ ሁለት በሮች አሉ ። አንደኛው ወደ ጸሎት ቤቱ ሁለተኛው ወደ ምግብ ቤቱ ያመራሉ ።

በመኝታ ቤቱ ውስጥ የሚታዩ ሌሎች ቁሳቁሶችም አሉ ፡— በመጻሕፍት የታጨቀ የመጻሕፍት መደርደሪያ ፡ ከእሳት ማንደጃው ላይ የተቀመጠ የመዳብ መስቀል ፡ ወረቀትና የቀለም ብልቃጥ ያለበት ጠረጴዛ ፡ የክንድ ማሣረፊያ ያለው ወንበር ፡ ወዘተርፈ ።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ በመኝታ ቤቱ ውስጥ ከአልጋው ራስጌ አንድ አነስተኛ ቁም ሳጥን አለ ፤ ብርቅ የሆኑ ዕቃዎች የሚቀመጡበት ። አቡነ ሚሪዬል ከጥንት ጉበረታቸው የተረፏቸው ስድስት የብር ቢላዎችና ሹካዎች እንዲሁም አንድ የሾርባ ጭልፋ ነበሯቸው ። በምግብ ጠረጴዛ ጨርቅ



@OLDBOOKSPDF

ላይ ሲያኖሯቸው ስለሚያንጸባርቁ ግዳም ማኗር በጣም ትወዳቸዋለች። ግዳም ማኗር እነዚህን የብር ዕቃዎች በቁም ሳጥን ውስጥ ትቆልፍባቸዋለች ። ቁልፉን ግን ከቁም ሳጥኑ አውጥታው አታውቅም ።

አቡነ ሚሪዱል ከአያታቸው እህት የወረሷቸው ከበድበድ ያሉ ሁለት የሻማ መቅረዞችም ነበሯቸው ። እነዚህም ከብር የተሠሩ ናቸው ። አብነ ኛውን ጊዜ ከእሳት ማንደኛው ላይ ባለው መደርደሪያ ላይ ሆነው ይታ ያሉ ። እራት የተጋበዘ እንግዳ ሲኖር ግን ሻማ ተሰክቶባቸው በምግብ ጠረጴዛው ላይ ይቀመጡ ነበር ።

ከዋናው ሕንጻ ሴላ በምድረ ግቢው ውስጥ ሌሎች ቤቶች አሉ ። እነ ዚህ ቤቶች ምድረ ግቢውን በማስዋብ ፈንታ መልኩን አበላሽተውበታል ለማለት ይቻላል ። ሆኖም ጥቅም አላቸው ። ከአትክልት ቦታው አጠገብ ያለው የቀድሞው መድኃኒት ቤት በከፊል እንደ ወጥ ቤት ፣ በከፊል እንደ ዕቃ ቤት ያገለግላል ። በተጨማሪም በአትክልት ቦታው ውስጥ አንድ በረት አለ ። በቀድሞ ጊዜ የሐኪም ቤቱ ወጥ መሥሪያ ቤት ነበር ። አሁን ግን የአቡኑ ሁለት ላሞች ያድሩበታል ። የሚታለቡት ወተት ይብዛም ይነሱ እኩሌታውን ጠዋት ጠዋት በሐኪም ቤቱ ሳሉት በሽተኞች ይልኩ ታል ። በቀልድ ዘይቤም «ይህ ሊሐኪም ቤቱ የምከፍለው አስራት ነው» ይላሉ ።

የአቡኑ መኝታ ቤት ሰፋ ያለ በመሆኑ በብርድ ወራት ስለማይሞቅ ፣ እሳት እንዳያነዱበት ማገዶ ውድ ስለሆነ አቡኑ አንድ አዲስ ሃሳብ መጥቶ ላቸው በበረቱ ውስጥ አንድ ክፍል እንዲሠራላቸው አደረጉ ። ብርድ በሚከፋበት ወራት በዚያ ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ ። ክፍሉንም «የክረ ምት አልፍኜ» ብለው ይጠሩታል ። በክረምት አልፍኛቸው ውስጥ አንድ ጠረጴዛና ከሣር የተሠሩ አራት ወንበሮች አሉበት ።

አቡኑ ሰባት ወይም ስምንት እንግዳ በአንድ ጊዜ የሚቀበሉበት ጊዜ ነበራቸው ። ለምሳሌ አገረ ገዥ ፣ ጄኔራል ፣ የምድር ጦር ባልደረቦች ወይም የክህነት ትምህርት የሚማሩ ወጣቶች እንደ አጋጣሚ ሆኖ በአንድ ጊዜ ይመጡ ነበር ። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር በየክፍሉ ያሉትን ወንበሮች ማስመጣት ግዴታ ነበር ። በየክፍሉ ያሉትም ወንበሮች እስከ አስራ አንድ ይደርሱ ነበር ።

ይህም ሆኖ ሳለ አንድ ተጨማሪ ወንበር በማድሚዘል ባጥቲስቲን ክፍል ውስጥ ነበር ፤ በጣም ሰፊና ከእንጨት የተሠራ ወንበር ። ይሁን እንጂ ከቦታው ተንቀሳቀስ አያውቅም ። ከርቱ ወደ ምድር ቤቱ ፣ ከምድር ቤቱ ወደ ፎቁ የሚወስደው ደረጃ በጣም ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ እን ግዳ በመጣ ቁጥር ሰፊውን ወንበር ማውረድ ፊጽሞ የማያመች ነበር ።

ሳይሚላላት ቀረ እንጂ ማድሚዘል ባጥቲስቲን በቤት ዕቃ መሚላት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ሕልም ነበራት ። ቢጫ ክፈፍ ያለውና የጽጌረዳ ቅርጽ የታተመበት እንዲሁም በልዩ ልዩ ሁኔታ የተጌጠ ሙሉ የእንግዳ መቀበያ



@OLDBOOKSPDF

ክፍል ዕቃ ለመግዛት ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች ። ለዚሁ ብላ በአምስት ዓመታት ውስጥ አርባ ሁለት ፍራንክ ተኩል አጠራቅማ ነበር ። ዳሩ ግን እሷ ያለመችው ዓይነት የሳሎን ቤት ዕቃ ለመግዛት ቢያንስ አምስት መቶ ፍራንክ ያሻው ስለነበረ ገንዘቡ አልጠራቀም ሲላት ርግጥ አድርጋ ተወችው ። የተመኘውን ሁሉ ያሟላ ማን አለ ፤

ስለ ዋናው ሕንጻና በምድረ ግቢው ስላሉት አስተያየ ቤቶች እንዲሁም በየክፍሎቹ ስላሉት ቁሳቁሶች ከተወራ ዘንዳ ስለአነስተኛው አትክልት ቦታም መጥቀስ ያሻል ። የአትክልቱ ቦታ መስቀልያ የሆኑ አራት የእግር መንገዶች አሉት ። መነሻቸው የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ነው ። በአትክልቱ ዙሪያ ሌላ የእግር መንገድ አለ ። ይህ መንገድ በዙሪያው ያለው ንና ነጭ ኖራ የተቀባውን የግምብ አጥር ተከትሎ ይሔዳል ። በመንገዶቹ የተከበቡ አራት የአትክልት መደቦች አሉ ። የእያንዳንዳቸው ወርድና ርዝማኔ እኩል ነው ። በሦስቱ መደቦች ማዳም ማሷር ቅጠላ ቅጠል ተክላባቸዋለች ። በአራተኛው መደብ አቡነ ሚሪዬል አበባ ተክለውበታል ። ጥቂት የፍራፍሬ ተክሎችም አልፎ አልፎ ይታያሉ ።

አንድ ቀን ማዳም ማሷር አቡኑ ምን መልስ ይሰጡኝ ይሆን በማለት «በጸዕነትዎ» አለቻቸው ፤ «በተሰምዶ ማንኛውም ነገር ጥቅም ሳይ እንዲውል ቢሹም አንድ ዋጋ የሌለው ነገር የሠሩ መሰለኝ ። በዚያ መደብ ላይ አበባ በመትከል ፈንታ ሰላጣ ቢተክሉበት አይሻልም ኖሯል?»

«ተሳስተሻል ማዳም ማሷር..... የተዋበ ነገር ከጠቃሚ ነገር አያንስም ። እንዲያውም የተዋበ ነገር ከጠቃሚ ነገር አይበልጥም ይሆን?» ሲሉ መለሱላት ።

አቡኑ የሚያለሙት የአበባ መደብ ሦስት ወይም አራት ንዑስ መደቦች ነበሩት ። በአበባቸው እንክብካቤ የሚያሳልፉት ጊዜ መጽሐፍ በማንበብ ከሚያሳልፉት ጊዜ እጅግም አያንስም ። ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ያህል ጊዜ አበቦቹን ይገርዛሉ ፥ መሬቱን ይኮተኩታሉ ፥ ጉድጓድ ይቆፍራሉ ፥ አትክልትም ይተክላሉ ። በበጋ ወራት ከሦስትም በምሽት ሰዓት በየቀኑ የአበቦቹን ንዑስ መደቦች ውሃ ያጠጣሉ ፤ ከቆርቆሮ በተሠራ ማጠጫ ። ተባይ በማጥፋት ረገድ ግን እንደ ሌሎች አትክልተኞች ጨካኝ አልነበሩም ። ደሞም አበባ ማልማት ደስ ቢላቸውም ስለ ስነዕፅዋት በቂ እውቀት አልነበራቸውም ። ስምሌ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው አበቦች መኖራቸውንና አንድ ተክል ከመሬት ሲያገነቁል የሚያወጣው ቅጠል ከተከሉ አንጓ በምን እንደሚለይ አያውቁም ። ስለ ዕፅዋትም ጥናት አድርገው አያውቁም ።

የአቡነ ማሪዬል መኖርያ ቦታ ጠቅላላ ገጽታው ከላይ እንደተዘረዘረው ሆኖ ሳለ በተጨማሪ መግለጽ የሚገባው አንድ ነገር አለ ። ይኸውም የቤቱ በሮች አይቆለፉ እንደነበረ ነው ። ከካቴድራሉ አደባባይ ትይዩ የሆነው የምግብ ቤቱ በር ቀደም ብሎ እንደእስር ቤት በር መቀርቀሪያ



@OLDBOOKSPDF

ነበረው ። አቡኑ ግን መወርወሪያው እንዲነቀል አደረጉ ። በዚህ ምክንያት ቀንም ሆነ ሌሊት ሊቀረቀር አይችልም ነበር ። መዝጊያው በመንጠቆ ብቻ ስለሚያዝ ማንኛውም ሰው ገፋ አድርጎ ሊከፍተው የሚችግረው አል ነበረም ። ማድሚዘል ባፕቲስቲንና ማዳም ማኋር በዚህ ጉዳይ ቅር ሳይ ሰኙ አልቀሩም ። ቅሬታቸውንም ሲገልጹ አቡኑ «እስቲ የራሳችሁን በሮች ቆልፉ!» ይሏቸዋል ። በሩ እንዲቆለፍ ፈጽሞ አይፈልጉም ። በዚህ ረገድ ስለነበራቸው አስተሳሰብ ስመረጻት በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ በአንድ ገጽ ላይ በጽሑፍ ያሰፈሩትን ማስታወስ ሳይረዳ አይቀርም ። ጽሑፉ እንዲህ ይላል ፤ «የሐኪም በር ምንጊዜም ቢሆን መቆለፍ አይገባውም ። የካህን በር ደሞ ሁልጊዜም ክፍት መሆን ይገባዋል ።

«የሕክምና ሳይንስ» በተሰኘ በሌላ መጽሐፍም ላይ ቀጥሎ ያለውን አስፍረውበት ተገኝቷል ፤ «እኔ ብሆን ሐኪም አይደለሁም? እኔምክ የማክማቸው አሎኝ.... ያልታደሉ መክረኞች.....»

ሌላው ጽሑፋቸውም እንዲህ የሚል ነበር ፤ «መጠግያ የጠየቀህን ሰው ስም ማን ነው ብለህ አትጠይቅ ። ከሁሉ ይበልጥ መጠግያ የሚያሻው በስሙ የማይኮራ ሰው ነውና ።»

አንድ ቀን አንድ ይካህን መጡና አቡኑ ለምን ብለው በሩን ሳይቆልፉ እንደሚተውት ይጠይቋቸዋል ። ጥያቄውን ያቀረቡላቸው በማዳም ማኋር ግፊትነት ሳይሆን አይቀርም ። «ቤቴን እግዚአብሔር ካልጠበቀው በስ ተቀር ከሌባም ሆነ ከአደጋ ሊጠበቅ አይችልም» አሏቸውና ጨዋታ ቀየሩ ።

አቡኑ ሌላም አባባል ነበራቸው ፤ እንዲህ የሚል ፤ «የጦረኛ ጀግና እንዶሰ ሁሉ የካህንም ጀግና አለ ። የኛው ጀግንነት ግን በእርጋታ የሚፈ ጸም ዓይነት ነው ።»

— 7 —

ጋስፓር ቤ. የተባለው አመጸኛ ሽፍታ ኦልዩል የተባለውን አገር ሲያ ስሸብር ከኖረ በኋላ የመንግሥት ወታደሮች ተከታትለው ወጉት ። ከተሸ ነፈም በኋላ ተከታየቹ ተበታተኑ ። የሱ ምክትል ከነበሩት አንዱ ፤ ክራ ሻት የተባለው ወንበዴ ወደ ያጋው አገር ወጥቶ ተሸሸገ ። ከጋስፓር ቤ ተከታዮች አንዳንዶቹ ከዚሁ ከክራሻት ጋር ሔደው በኢስ አገር ቆዩ ። ቀጥሎም ወደ ፒዬድሞ ተጓዙ ። ፒዬድሞንም ሲቅለው ወደ ባርሴሎኔት መሐዳቸው ተወረ ። ወንበዴዎቹ በዚህም አላበቁ ። በገቦዜና በትዊስት ታዩ ተባለ ። ቀጥሎም በገቦ ደሞግል ። በዚሁ ቦታ ዋሻ ውስጥ እየኖሩ ፣ ከዚ ያም ወጥተው በአባይና በአባዬት ሸለቆ አልፈው ወደ ገበሬዎች ሠፈር ወርደው መታየታቸው ተሰማ ።



@OLDBOOKSPDF

ክራቫትና ሰዎቹ አንድ ቀን ሌሊት ከአምበረ ዘልቀው ፣ ከአምብረ ካቴድራል ውስጥ ገብተው ፣ መቅደሱን አርክሰው ፣ የካቴድራሱን ሀብት ንብረት ዘርፈው ሸሹ ። መቼም ቢሆን የክራቫት እግር የረገጠው ምድር ጥሉት እንጂ ልማት አያውቅም ። ፖሊሶች ተከታትለው እንዲይዙት ትዕዛዝ ተላለፈ ። ፖሊሶቹ ግን ሊያገኙት ሳይችሉ ቀሩ ። ቢያገኙት ኖሮ እንኳ ወጊያ ይገጥማቸው ነበር እንጂ እጁን አይሰጥም ነበር ። ደፋርና ምንም የማይበግረው ወንበዴ ነበርና ። ክራቫትና ሰዎቹ እንዲሁ አገር ሲያሸብሩ በነበሩበት ወቅት አቡነ ሚሪዬል ከዚያው አገር ደረሱ ። አመጣጣቸው ሻስተላር የተባለው ንክተማ ለመገመብኘት ነበር ፣ ማድሚዜል ባፕቲስቲንና ማዳም ማሏርን አስከትለው ። የክተማው ከንቲባ ካረፉበት መጥቶ ጠየቃቸውና በመጠበት እግር እንዲመለሱ ተማጸናቸው ። ይሽውም ክራቫት እስከ አርሽና ከዚያም አልፎ ያለውን ደጋ አገር በቁጥጥሩ ሥር አውሎት ስለነበረና አቡኑም ጉዞአቸውን ቢቀጥሉ አደገኛ እንደሚሆንባቸው በመ ግንዘብ ነበር ። ሦስት ወይም አራት ፖሊስ አስከትለው ቢሔዱ እንኳ አስጊ እንደሚሆን ሲገልጽላቸው «የፖሊስ እጅብ አልፈልግም» አሉት አቡኑ ፣ «ብቻዬን ነው የምሔደው ።»

«ብቻዬን.....? የማይታሰብ ነው ብጹዕነትዎ ።»

«ብቻዬን ነው የምሔደው ብየሃለሁ ። ከአንድ ሰዓት በላይ ከዚህ አል ቆይም ። »

«እንዴት?»

«እሔዳለሁ!»

«በቻምንን?»

«አምን ፤ ብቻዬን ።»

«ፈጽሞ የማይታሰብ ነው ብጹዕነትዎ ።»

«ስማኝ ሙሴ ክንቲባ..... ከጋራው ማዶ የሚኖሩትን ገጠሬዎች ከገ በኘኋቸው ሦስት ዓመት ሆኖኛል ። ፍየል ጠባቂዎች ናቸውና የተባረኩ ሰዎች ። እያንዳንዳቸው ከሚያሟሏቸው ሠላሳ ጥየሎች አንዱ ብቻ የራሳ ቸው ንብረት ነው ። የሱፍ ገመድም ይገምዳሉ..... ብዙ ዓይነት ቀለም ያላቸው ። ዋሽንት መጫወትም ይችሉበታል..... በባለ ስድስት ቀዳዳ ዋሽንት ። ሰዎቹ ወዳጆቼ ናቸው ። አልፎ አልፎ ቡራኬ ማግኘት ይገባቸ ዋል ። ታዲያ እዚህ መጥቼ እነሱ ዘንድ ሳልደርስ ብመለስ ወይም መጥቶ እንዳይጠይቃችሁ ፈርቶ ተመለሰ የሚል ወሬ ቢነገራቸው ምን ይሉኛል?»

«ወንበዴዎቹ የሚያስኬዱዎት ቢሆንማ.....?»



@OLDBOOKSPDF

«እረግ.....! እንዲያውም ሌላ ነገር አስታወስከኝ ። እነሱም ስለደኅ እግዚአብሔር ማወቅና መስማት አለባቸው ። እነሱም በራሴ ማግኘት ይገባቸዋል ።»

«በርከት ያሉት ናቸው ብጹዕነትም ። የተኩላ መንጋ.....?»
«ማን ያውቃል! እግዚአብሔር የላከኝ ይህንን የተኩላ መንጋ ለመጠበቅ ይሆናል ። የቸሩ እግዚአብሔርን ሃሳብ ማን ያውቃል!»

«ይዘርፉዎታል ብጹዕነትዎ ።»

«እኔስ ምንም የለኝም ሙሴ ከንቲባ ። ምኔን ነው የሚዘርፉት?»

«ሰውን ከመግደል እንኳ ወደ ኋላ የማይሉት ናቸው ብጹዕነትዎ ።»

«እረዲያ.....! እየጸለየ የሚያልፍ አንድ አዛውንት ካህን ሊገሉ? ምን ይጠቅመናል ብለው ይገድሉኛል?»

«ድንገት ቢያገኙዎት..... ፈጽሞ አላማረኝም!»

«ቢያገኙኝማ ለድሆች የሚሆን ገንዘብ እንዲሰጡኝ እለምናቸዋለሁ!»

«አባክዎን አይሒዱ ብጹዕነትዎ ። ይቅመኑኝ..... ስለእግዚአብሔር ብለው ሃሳብዎን ይቀይሩ ። ለምን ብለው ሕይወትዎን አደጋ ላይ ይጥላሉ?»

«ሙሴ ከንቲባ..... እውነት አስከዚህ ገመትከኝ? እኔስ በዚህ ዓለም የምኖረው የሰዎችን ነፍስ ደህንነት ለመጠበቅ እንጂ የራሴን ሕይወት ለመጠበቅ አይደለም ።»

ከዚያ በላይ ሊከራከራቸው አልፈቀደም ። አቡነም መንገድ የሚያሳያቸው አንድ ወጣት ልጅ ብቻ አስከትለው ጉዞ ተነሱ ። በበቅሎ ነበር የሚጓዙት ። ተጉዘው ተጉዘው ፣ ጋራውን አቋርጠው ፣ ያለአንዳች አደጋ ከፍየል ጠባቂዎቹ መንደር ደረሱ ። መንደርተኞቹን ሲሰብኩ ፣ ክርስቲያናዊ ሥራ ሲሠሩ ፣ ሲያስተምሩ ፣ ሲመክሩ ለአስራ አምስት ቀኖች ያህል አዚያው ቆዩ ። የመመለሻቸው ቀን ሲቃረብ «ንሴብሆ ለእግዚአብሔር» የሚለውን መንፈሳዊ መዝሙር በአቡን ሥርዓትና ወግ ለመዘመር ወሰኑ ። ውሳኔአቸውንም ለመንደሩ ቄስ ገለጹላቸው ። ይሁን እንጂ መዝሙሩን በአቡን ሥርዓትና ወግ ለመዘመር አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች አልነበሩም ። ልብስ ተክህኖ ከሚ ተመጥበት ሥፍራ ካለአንድ የቅዳሴ ልብስ በስተቀር ሌላ ምንም የለም ። ለዚህም አርጌና ጥልፍ ብጤ የተጠለፈበት ነበር ።

ቄሱ ይህንኑ ሲነግሯቸው «ግድ የለም . . . እግዚአብሔር ያበጀዋል» አሏቸው ። ከዚያም በኋላ ቁሳቁሶቹ በአካባቢው በነበሩ በሌሎች ደብሮች



@OLDBOOKSPDF

ይገኙ ይሆናል በሚል ተስፋ ፍለጋ ተደረገ ። ምንም ውጤት አልተገኘም ።

ነገሩ አሳፍሯቸው የሚያደርጉትንም አጥተው እንደተቀመጡ ሁለት ያልታወቁ ፈረሰኞች በድንገት መጥተው በአቡኑ ማረፊያ ቤት ትልቅ ሳጥን አጉረው በመጡበት እግራቸው ተመልሰው ሔዱ ። ሳጥኑ ተከፍቶ ቢታይ በውስጡ የወርቅ ካባ ፣ በዕንቁ የተንቆጠቆጠ የአቡን ቆብ ፣ የሊቀ ጳጳስ መስቀል ፣ እና በጣም ያማረ በትረ አቡን አለበት ። እነዚህ ሁሉ ከአንድ ወር በፊት በአምብረ ከሚገኘው ማርያም ቤተክርስቲያን የተዘረፉ ነበሩ ። በሳጥኑ ውስጥ እንዲህ የሚል ጽሑፍም ተገኘ ፤ «ለአቡነ አንባን ይህና መጡ . . . ከከራቫት የተላከ ።»

«የተቀረውን እግዚአብሔር ያበጀዋል አላልኩም ነበር . . . ! የካህን ካባ ይበቃኛል ስሚል እግዚአብሔር የሊቀ ጳጳስ ካባ ይለክለታል» ብሰው ፈገጉ አቡነ ሚሪዬል ።

ቂሱም እየሳቁ ፤ «ከእግዚአብሔር ነው የተላከ ወይንስ ከሰይጣን ?» ሲሉ ጠየቋቸው ።

አቡኑ ፊታቸውን አኩብደው ፤ «ከእግዚአብሔር ነው የተላከው ብያለሁ» አሏቸው ።

አቡኑ ወደ ሻስትላር ሲመለሱ የዚያ ነዋሪዎች ወደ መንገድ ወጥተው እንደ ጉድ ያይዋቸው ጀመር ። ማድሚዘል ባጥቲስቲንና ማዳም ማሏር በሻስትላር ካህን ቤት ሆነው ሲጠብቋቸው ነበሩ ። አቡኑም ከዚያ ሲደርሱ «አያችሁ . . » አሏቸው ፤ «ደንቁን የፍየል ጠባቂዎች ለማየት መሐይሙ ስህተት አልነበረም ። እምነቴን ብቻ ይገኔ ባዶ እጄን ሐድኩ ። ስመለስ ግን የአንድ ካቴድራል ሀብት ንበረት ይገቡ ተመለስኩ ፡ »

ያን ቀን ማታ ወደ መኝታቸው ከመሔዳቸውም በፊት እንዲህ ሲሉ ተናገሩ ፤ «ቀጣሮችንና ነፍስ ገዳዮችን አንፍራቸው ። እስከዚህም አደገኛ አይደሉምና ። ይልቁንስ ራሳችንን እንፍራ ። እውነተኛ ቀናኛ በሰውኛ ላይ ያለን የተዛባ ስሜት ነውና ። እውነተኛም ነፍሰ ገዳይ ክፉ ሥራ ነውና ። የሚያስፈራው አደገኛነት ያለው ከኛው ልብ ውስጥ ነው ። አእምሮአችንንና ገንዘባችንን ከአደጋ የሚያደርስ ማንኛውም ነገር ሊያስጨንቀን አይገባም ። ሊያስጨንቀን የሚችል ነፍሳችንን ከአደጋ የሚያደርስ ነገር ብቻ ነው ።»

ቀጥሎም ፊታቸውን ወደእህታቸው አዙረው እንዲህ አሉ ፤ «ካህን የሆነ ሰው እገሌ እንዲህ ያደርገኛል ብሎ መስጋት አይገባውም ። እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ሰው አያደርገውምና ። አደጋ ሊያደርስብን መቻሉን ስናውቅ መጨነቅ ይገባናል ። የምንጨነቀው አደጋ እንዳይደርስብን ሳያሆን አደጋ የሚያደርሰው ሰው አደጋውን በመጣል ኃጢአት እንዳይሠራ ነው ።»



@OLDBOOKSPDF

ክራሻት የተባለው ወንጀዴ የፈጠረው ዓይነት ሁኔታ በአቡነ ሚሪ ዬል ሕይወት ውስጥ አልፎ አልፎ የሚደርስ እንጂ የተለምዶ አልነበረም ። ይሁንና ከአምበረ ካቴድራል ተዘርፎ በአቡኑ እጅ የወደቀው ሀብት ንብ ረት ከምን ደረሰ ? ይህንን ጥያቄ መጠየቅ ምናልባት ባልተገባ ! ከወርቅና ከእንቁ የተሠራ ዕቃ ምን ጊዜም ቢሆን ያጓጓልና ። ለማንኛውም አቡነ ሚሪዬል ሀብት ንብረቱን ከምን እንዳደረሱት በውል አልታወቀም ። በማስታወሻ ደብተራቸው ውስጥ ግን እንዲህ የሚል ጽሑፍ ተገኘ ፤ «ይህ ንብረት ወደ ካቴድራሉ ይመለስ ወይንስ ለሆስፒታሉ ይሰጥ ? ሃሳቤን መቁረጥ አዳግቶኛል . . . »

— 8 —

በአንድ በዓል ቀን አቡነ ሚሪዬልና በእሳቸው ሳይ ቁጣ የተመላበት ሰውር ደብዳቤ የጻፈባቸው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል በአገረ ገዥ ቤት ራት ተጋበዙ ።

የምክር ቤቱ አባል ተጨባጭ ጥቅም በሚያስገኙ ነገሮች እንጂ ተጨ ባጭነት በሌላቸው ነገሮች አያምንም ። ሰምሳሉ ሕሊና ፥ እምነት ፥ ፍትህ ፥ ግዳጅ እና የመሳሰሉት ሁሉ ሰሉ ቅርጉም የላቸውም ። ከአለበት ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ለመድረስ የበቃውም መሰናክል የሚሆኑበትን ሁሉ ደፍ ጭቆ በማለፍ ነበር ። ከዓላማውና ከግል ጥቅሙ ንቅንቅ የሚያደርገው አንዳችም ነገር አልነበረም ። ሰራሱም ሆነ ለልጆቹ ፥ ለአማኞቹ ፥ ለዘመዶ ቹና ለወዳጆቹ ጥቅም የሚያስገኝ ነገር ልብ ካለ ያንን ጥቅም በእጁ ለማድ ረግ የማይፈጥረው ዘዴ ፥ የማይፈጽመው ተግባር አልነበረም ። ተጨባጭ ጥቅም ለሌላው ነገር መድከም ግን ደደብነት መስሎ ይታየው ነበር ።

የኤፒኩር ደቀ መዝሙር ነኝ ባይ ነው የምክር ቤቱ አባል ። በእውነቱ ከሆነ ግን እሱ የሚከተለው ፍልስፍና የፒት— ሰብረ ፍልስፍና ነበር ። ዘለዓለማዊ ቦሆኑ ነገሮች አያምንም ። አቡነ ሚሪዬል አማኝ በመሆናቸውም በልቡ ይስቅባቸዋል ። አንድ አንድ ጊዜም አቡኑ ራሳቸው በተገኙበት በገ ሃድ ያፌዝባቸው ነበር ።

ይህ ሆኖ ሳለ በበዓሉ ቀን ሁሉቱም አገረ ገዥ ዘንድ ጥሪውን አክብ ረው መጡ ። ግብግዋ ተሟሙቆ ወደ ፍጻሜ በሚቃረብበት ሰዓት የምክር ቤቱ አባል ሞቅ ሞቅ አለው ። በእርግጥ ክብሩን እስከሚዋረድ ድረስ አል ስከረም ። ሞቅታው ግን በግልጽ የሚታይ ነበር ።

«ጎንሽ ብንወያይ አይከፋም መሰለኝ . . . » አላቸው አቡነ ሚሪዬ ልን ፤ «እርስዎ አቡን ፥ እኔ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነን ሳለ እንደ ተራ ሰዎች እንዲሁ ተፋጥጠን መቀመጥ አያምርብንም ። እኔ በበ ኩሌ የራሴ የሆነ ፍልስፍና ስላለኝ ይህንኑ ልናዘዝልዎ ፈቃደኛ ነኝ ።»



@OLDBOOKSPDF

«ደግ ነው እስማማለሁ . . . » አሉት አቡኑ ፤ «መቼም እያንዳንዱ ሰው የሚመራው በፍልስፍናው መስመር ነው ። ያንተም ፍልስፍና በከፍተኛ ደረጃ የሚመደብ እንደሚሆን አምናለሁ ።»

«የዳርዣ መስፍን ፣ ፒሮ ፣ ሆብ ፣ እና ኤም ኔጎ ክፉ ሰዎች ናቸው አል ልም ። ዲኤሮን ግን ከእንጀቱ እጠለዋለሁ ። ሃሳባዊ ፣ ባዶ ለፍላፊና እመ ጸኛ ሰው ነው ። በልቡ ግን በእግዚአብሔር ያምናል ። ደሞም ከቮልቴር የባሰ ግብዝ ሰው ነው ። ቮልቴር በኢጾም ይቀልድ ነበር ። ይህ ግን ስህተት ነው ። ምክንያቱም ኢጾም እግዚአብሔር ዋጋ ቢስ መሆኑን ያረጋግጣል ። በበኩሌም ስለእግዚአብሔር የሚወራው መላ ምት አስተሳሰብ ሰልችቶ ኛል ። ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር የሚባለው ይውደም ! የሰቃዬ ምንጭ እሱ ነውና ። የሱ አለመኖር ግን ይለምልም ! ሰላም የሚሰጠኝ እሱ ነውና ። መናዘዝ ስላለብኝ ስሰራሁ እውነቱን መናገር ይገባኛል ። እኔ ጅል ሰው አይ ደለሁም ። የእውቀት ብርሃን አርፎብኛል ። ኢየሱስ ክርስቶስን አጠላዋ ለሁ ፤ ሁሉንም ነገር ተው ፣ ራሳችሁንም መስዋዕት አድርጉ ስለሚል ። ሁሉንም ተው . . . ? ለምን ? መስዋዕት ሁኑ . . . ? ለምን ? አንድ ተኩላ ለሌላ ተኩላ ራሱን ሲሰዋ አላየሁም ! ሰውም ቢሆን ያው ነው ። ሁላችንም በተፈጥሮ ሕግ መሠረት መኖር ይገባናል ። ሰዎች ከፍጥረታት ሁሉ የበላዮች ነን ። ፍልስፍናችንም የበላይ መሆን ይገባዋል ። አርቀን ለማ የት ካልቻልን ግን ከፍጡራን ሁሉ የበላይ ብንሆን ምን ዋጋ አለው ? እኔ በበኩሌ ተደስቱን እንኑር ባይ ነኝ ። ከአለንበት ሕይወት ውጪ ሌላ ሕይወት የለም ። ሰው ከዚህ ዓለም ሕይወት ውጪ ሌላ ሕይወት አለው የሚባለውን ፈጽሞ አላምንበትም ። ሊሆንም አይችልም . . .

«አዎ . . . ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገህ ተው . . . ራስህንም ሰዋ ተብሎ ይነገረኛል ። ስለምታደርገው ነገር ሁሉ መጠንቀቅ አለብህ . . . በሳውንና ክፉውን ጠንቅቀህ እወቅ . . . ትክክለኛ ሁን . . . ሀሰተኛ አት ሁን ተብሎም ይነገረኛል ። ነገር ግን ስምን . . . ? በዚህ ዓለም ስላደረግ ሁት ሁሉ ከመቃብር ማዶ ባለው ሕይወት ስልምጠየቅበት ! ምን ዓይነት ቅዠት ነው አባካችሁ ! እኔ ከሞትሁ በኋላ ስለሥራዬ የሚጠይቀኝ ማነው ? ጉም መጨበጥ ይሏል ይህ ነው ! ይልቁንስ የዕውቀት ጮራ ያረፈብን እኛ ፤ ሁላችንም እውነቱን ብንናገር ይሻላል ። ከፉና በጎ የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም ። ያለው ተጨባጭ የሆነው ነገር ብቻ ነው ። ስለዚህ ተጨባጭ የሆ ነውን ነው መሻት የሚገባን ። ቁም ነገሩ ከዚህ ላይ ነው ። ተጨባጩን እውነት አሸትተን ማግኘት አለብን ፤ ካለበት ጠልቀን ገብተን ። ያኔ ነው ፍጹም ደስታ የምናገኘው ። ይህ ሲሆን ብርታት ይሰማናል ። እንስቃ ለንም . . .

«እኔ በበኩሌ መኖሬን አውቃለሁ ። ዘለዓለማዊነት ግን ከሕልም ያልተሻለ ሃሳብ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም ። የፈለገ ሰው በዘለዓለማዊ ነት ሊያምን ይችላል ። የራሱ ጉዳይ . . . ! ዘለዓለማዊነት የሚያጓጓ ተስፋ መሆኑንም አልክድም . . .



@OLDBOOKSPDF

«አዎ . . . ! እንደሚነገረን ሰዎች ነፍስ አላቸው ። መላእክትም ይሆናሉ ። ስማያዊ ክንፍ ያበቅላሉ ። ይሽሽ ይሁን ። ብቻ... ብቻ ... ጓደ ታን ከከዋክብት ወደ ከዋክብት ይበርራሉ' ያለው ቴርቱልየንም አይ ደል ! በጣም ጥሩ አባባል ! አንድ ቀን እንዲ ፈንጣ ከከዋክብት ወደ ከዋ ክብት መዝለሳችን አይቀርም ! እግዚአብሔርንም እናያለን ። ይገርማ ልኮ እባክችሁ ! ይህ ሁሉ እንቶ ፈንቶ . . . !

«እኔ በበኩሌ እንደማስበው እግዚአብሔር ችርነም የሌለው ጭራቅ እንጂ ከዚህ የተሰየ አይደለም ። ይህንን በማሰቴ ይቅርታ ! በወዳጆቼ መሐ ከል ስላለሁ እውነቱን ተናዘዝሁ እንጂ በሌላ ቦታ ቢሆን ደፍሬ እንዲህ አልናገርም ።

«ወየ ጉድ ! ጎሳ ሰገና ሙንግሥት ስማይ አገባለሁ ፣ ምድረ ነነን እወርሳለሁ ብሎ የዚህን ዓለም ደስታ መስዋዕት ሚድረግ ምን ዓይነት የዋህነት ነው! የለም ጊታዬ ... ! ከሞት በኋላ ሕይወት ፣ ዘለዓለማዊነተ የለም ።

«ከመወለዴ በፊት ሕያው አልነበርኩም ። ከሞትኩ በኋላም ሕያው አልሆንም ። እና አሁን ምንድነኝ ? ሕይወት ያለው ፣ ተንቀሳቃሽ ትቢያ ነኝ ። በዚህ ዓለም እስክለሁ ድረስ ምን ማድረግ ይገባኛል ? ምርጫው የኔ ነው ። ብፈልግ ተደስቼ እኖራለሁ ። ብፈልግ ተሰቃይቼ እኖራለሁ ። የስቃይ ኑሮ ትርፉ ምንድነው ? ስቃይ ! የደስታ ኑሮ ትርፉ ምንድነው ? ደስታ !

«እኔ ያለኝ ምርጫ መብላት ወይም መበላት እንደሆነ ከተገነዘብሁ ቆይቻለሁ ። ከመበላትም መብላትን መርጫለሁ ። ለምን ተብሎ ! ግር ሆኖ ከመበላት ጥርስ ሆኖ መብላት ይበልጣል ። የኔ ፍልስፍና ይህ ነው ። ከዚህ ዓለም ሕይወት በኋላ ሁሉም ነገር በመቃብር ይከተታል ። አለቀ ። ደቀቀ ። መጨረሻው ኢምንትነት ነው ። ከመቃብር ማዶ ምንም የለም ፣ ከባዶነት በስተቀር ። ከዚህ የተሰየ አስተሳሰብ ሁሉ ያስቀኛል ፣ ቅዠት ወይም ለልጆች የሚነገር ዓይነት ተረት ነውና ። ኃጢአተኛው ሳርዳናፖ ልም ሆነ ቅዱሱ ዊንሳ ዶ ፖል መጨረሻቸው አንድ ነው ፣ ከመቃብር ማዶ ያለው ጭለማ !

«አምን . ሕይወት ያልተሳካላቸው ሰዎች ፡— ባዶ አማሪቸውን የሚሉዱ ሊማኞች ፣ ቀጥቃጮች ፣ እና መከረኞች ያለከንቱ ተስፋ ለመ ኖር አይችሉም ። ስለዚህ የዘለዓለማዊነት ፣ በመንግሥተ ሰማይ ፣ በነፍስና በመሳሰሉት ማመን አለባቸው ። አፊ ታሪክ . . . ! ቅዠት . . . ! ምንም የሌለው መናጢ ድሃ እግዚአብሔር አለው ። ይህንን የሚነሳው ስው የለም ። መናጢ ድሃ የሆነ ስው ለምን በእግዚአብሔር ያምናል ብዬ አልከራከርም ። አልታወመውም ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰተራ ሕዝብ እንጂ ለኔ ትርጉም የለውም ።»



@OLDBOOKSPDF

ይህንን ብሎ ሲጨርስ አቡነ ሚሪዮል አጨበጨቡለት ። ቀጥለውም እንዲህ አሉ ፤

«ንግግር ማለት እንዲህ ነው ! ይህ ቀረው የማይባል ! መንፈሳዊ የሆነውን ሁሉ ንቆ ሥጋዊ የሆነውን ብቻ መያዝ ። እንዴት ያለ ግሩም ፍልስፍና ነው ! በሥጋዊ ነገር ብቻ ካመኑ በምንም ነገር ለመታለል አይ ቻልም ። እንደ ካቶ አይሰደዱም ።እንደ እስጢፋኖስ በድንጋይ አይወገሩም ። እንደ ጎን ዳርክ በሕይወት እያሉ በእሳት አይጋዩም ። በሥጋዊ ፍልስፍና ብቻ የሚያምኑ ሁሉ ለምንም ነገር ኃላፊነት የለባቸውም ። እነሱ እስካል ቀዋጡ ድረስ ሌላውን ሁሉ ቢወጡ ቀጠያቂነት የለባቸውም ። በትክክለ ኛም ሆነ በሐሰተኛ መንገድ ሥልጣን ቢይዙ ፣ ቢበለጽጉ ፣ ቢሾሙና ቢሸለሙ ፣ ለጥቅም ቢገዙ ፣ ክፋት ቢሠሩ ፣ ሕሊናቸውን ቢሸጡ ፣ ለነሱ ይህ ፁሉ ተፈቅዷል ! ይህንንም ሁሉ አድርገው ዐመጨረሻ ወደ መቃብ ራቸው ሲወርዱ ተጠያቂነት የለባቸውም ! ከዚህ የቦሰጠ ምን ይፈለጋል ሴናተር ! ይህንንም ስል በመሐከላችን አለመግባባት እንዳይኖር ! ከሳይ የዘረዘርካቸውን ሁሉ ሠርተሃል ማለቱ አይደለም ። ሆኖም ስለፍልስፍናህ እንኳን ደስ ያለህ ሳልልህ አላልፍም ። እናንት ምርጥ መኳንንት የራሳች ሁ የሆነ ፍልስፍና እንዳላችሁ ታወራላችሁ ። ይህ ፍልስፍና እናንተን ምር ጡቹን እንጂ ሌላውን ስው ፣ ተራውን ሕዝብ እንደማይመለከትም ታረጋ ግጣላችሁ ። በጣም የረቀቀና ደስ የሚል ነው ፍልስፍናችሁ ! በጣም የረቀቀ ከመሆኑም የተነሳ እናንተ ምርጦቹ እንጂ ተራው ሕዝብ ሊደርስበት አይችልም ፣ ከዚህም በላይ ደግነት አያሳችሁም ፣ እናንተ ምርጥ መጻን ንት ! ተራው ሕዝብ በእግዚአብሔር ቢያምን አንቃወምም ትላላችሁና ።»

— 9 —

ስለአቡነ ሚሪዮል ባህርይና ስለግል ኑሮአቸው በይበልጥ ለመረዳት እህታቸው ማድሚዘል ባፕቲስቲን ለአብሮ አደጓ ፣ ለጊቨሮ እመቤት የጻፈችውን ደብዳቤ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል ። ደብዳቤው እነሆ ፤

ዴ ክተማ 1 ታህሳስ 16 ቀን 18—ዓ. ም.

ለተወዳድሽው የጊቨሮ እመቤት ፣—

ስምሽን ሳናነሳ ውለን ያደርግበት ጊዜ ባይኖርም ዛሬ ደብዳቤ የም ጽፍልሽ አንቺን ለማስታወስ ያህል ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የምነግርሽ ስላለኝ ነው ። ማዳም ማኧር ቤታችንን ስታጸዳዳ ምን ያገኘች መሰለሽ ! እንደምታውቂው ሁለቱ መኝታ ቤቶቻችን በአርጌ መረቀቶች የተሸፈኑና መረቀቶቹም ኖሪ የተቀቡ ናቸው ። የኔው እንግዳ መቀበያ ክፍል እንዳችም ቅራቅምቦ የሌለበት ባዶ ክፍል ነው ። ልብሶቻችንን ካጣጠብን በኋላ የምናስጣቸውም ከዚህ ክፍል ውስጥ ነው ። ወደላይ ርዝመቱ ከአስራ አምስት ጫማ ፣ ጉኑና ወርዱ ከአስራ ስምንት ጫማ አይበልጥም አያንስ



@OLDBOOKSPDF

ምም ። ቀደም ባለው ጊዜ ጣራው ስዕል የተሳለበት ሆኖ ቀለሙ ወርቃማ ነበር ። እንዳቺው ቤት ወጋግራም ነበረበት ። ሕንጻው ሐኪም ቤት በነበረበት ጊዜ ጣራው በጨርቅ የተሸፈነ ነበር ። የእንጨት ሥራዎቹም በአያቶቻችን ዘመን የታነጹ ናቸው ። ታዲያ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁልሽ ማዳም ማኟር ቤታችንን ስታጸዳዳ ምን ያገኘች መሰለሽ ! ግድግዳውን የሸፈነውን የወረቀት ልባስ ልጣ ስታነሳው በእጅ የተሳለ ስዕል አግኝታለች ። ሥዕሉ ውብ ነው ባይባልም እስከዚህም የሚያስከፋ አይደለም ። ከግሪኮች አማልክት አንዱ የሆነው ቲሌማክ ከሮማ አማልክት አንዷ ከሆነችው ከሚኔርቭ እጅ የጦር መኮንንነትን ማዕረግ ሲቀዳጅ ያሳያል ። ማዕረጉን የምትሰጠው በአንድ መሩፈሻ ሥፍራ ነው ። ስሙን እንዳልነግርሽ ረስቼ ዋለሁ ። ታዲያ ምን ልበልሽ ! ሮማውያን ወንዶችና ሮማውያን ወይዛዝርት እስከነጭፍሮቻቸው ፣ እስከነአሽቢዎቻቸው የሚታዩበት ነው ስዕሉ ። በስዕሉ ላይ ትንሽ የተበላሸ ነገር ስላለበት ማዳም ማኟር በበጋው ወራት ልታሳድሰው አስባለች ። ከዚያ በኋላ የኔ ክፍል ቋሚ ‹መዚያም» እንደሚሆን አልጠረጥርም ! እንዲሁም በጣራው ጥግ ከሚገኘው አነስተኛ ክፍል ፣ ከ «አቲክ» ማዳም ማኟር ጥንታዊ የሆኑ ሁለት ጠረጴዛዎች አግኝታለች ። ጥንት የነበራቸውን ዓይነት ወርቃማ ቀለም ልናስቀባቸው አስበን ነበር ። ነገር ግን ቀለሙን ለማስቀባት አስራ ሁለት ፍራንክ ስለጠየቁን ግንዘቡን ለድሆች ብንሰጥ ይሻላል ብለን ወስነናል ። ደሞም ጠረጴዛዎቹ አስቀያሚ ስለሆኑ እኔ በበኩሌ ከጥቁር እንጨት የተሠራ ክብ ጠረጴዛ ቢኖረኝ እመርጣለሁ ።

በተረፈ በጣም ተቆጥበን ነው የምንኖረው ። ብጹዕነታቸው በጣም ደግ ከመሆናቸው የተነሳ ያላቸውን ሁሉ ለድሆችና ለበሽተኞች አገልግሎት ያውሉታል ። በክረምት ወራት አገሩ በጣም ይበርዳል ቤታችን ግን በመጠኑም ቢሆን ብርሃንና ሙቀት ስላለው ታድሰናል ለማለት እችላለሁ ።

መቼም ወንድሚ የራሳቸው የሆነ ልዩ አመለካከትና አኗኗር አላቸው ። አቡን የሆነ ሰው ልዩ አመለካከትና አኗኗር እንዲኖረውም ያሻል ይላሉ ። እስቲ አስቢው ! የቤታችን በር ተቆልፎ አያውቅም ። የፈለገ ሰው በፈለገው ሰዓት ከወንድሚ ክፍል ሰተት ብሎ እንዳይገባ የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም ። እሳቸው እንደሆኑ በሴሊት እንኳ ምንም ነገር አያስፈራቸውም ። ‹‹የኔ ድፍረት ከዚህ ላይ ነው» ይላሉ ።

ማዳም ማኟርና እኔ ምን ይደርስባቸው ይሆን እያልን በጣም እንጨነቃለን ። እሳቸው ግን እንድንጨነቅላቸው አይፈልጉም ። ራሳቸውን ለብዙ ዓይነት አደጋ ያጋልጣሉ ። ዝናብና ጉርፍ ባለበት ወራት እቤት እንደመቀመጥ ወጥተው ይሄዳሉ ። የክረምት ወራት ለጉብ የማያመች ቢሆንም እሳቸው እቤት አይውሉም ። አደገኛ በሆነና በሚያስፈራ መንገድ ይጓዛሉ። በሌሊት እንኳ የሚጓዙበት ጊዜ አለ ።

ባለፈው ዓመት ሳያፈሩ ብቻቸውን ወንበዴዎች ካሉበት አገር ሔደው ነበር ። እዚያም ሁለት ሳምንት ያህል ቆይተው ቦደሀና ተመለሱ ። እኛ



@OLDBOOKSPDF

ግን በሕይወት ይመለሳሉ የሚል ተስፋ አልነበረንም ። ከቪታ አንደተመለሱ ምን አሉ መሰለሽ !ወንበዴዎች እንዳይዘርፉኝ ፈርታችሁልኝ ነበር ። ነገር ግን ተመልከቱ» ብለው አንድ ትልቅ ሳጥን ከፍተው በውስጡ የነበረውን እንቁ አሳዩን ። «ይህ ሁሉ ከአምበረ ካቴድራል ተዘርፎ የነበረ ሀብት ንብረት ነው ። ዘራፊዎቹ ግን ለኔ አምጥተው ሰጡኝ» አሉን ። ታዲያ አይገርምሽም ! እኔ ግን ሳልወስዳቸው አላሰፍኩም . ማለቴ ሰው በሉ ለበት ሰዓት . . .

ወንድሚ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ሁል ጊዜ እጸልይላቸዋለሁ ። ማዳም ማሏርም እንዲሁ ። በእሳቸው ላይ አንዳች አደጋ ቢደርስ ምን ይውጠኛል ! እሳቸው ቢሞቱ እኔም መሞቴ አይቀርም ። ቀደም ብሎ ማዳም ማሏር ከኔ ይበልጥ ሳ ሲጋሳቸው ነበር አሁን ግን ሁለታችንም ከሁኔታቸው ጋር ተላም ደናል ። ከመጸለይ በስተቀር ምን ለማድረግ እንችላለን ! ጸልዮን ወደመኝ ታችን ሐዲን እንተኛለን ። ዲዮበስሎ ከቤታችን ሊገባ ቢሻ የሚከለክለው ነገር የለም ። ይሁን እንጂ ምን የሚያስፈራን ነገር አሰ ! ጎያሉ አማዚአብ ሔር እያለ የሚያስፈራን አንዳችም ነገር አይኖርም ።

ወንድሚ አንዳችም ቃል ሳይናገሩ ምን እንደሚፈልጉ አውቃለሁ ። እና ተስፋችንን በእማዚአብሔር ላይ ጥለን እንኖራለን ።

ወዳጄ የፀሸሸሮ አመቤት ፡—

ዘመድሽ የሆኑትና የተቀደሱት ሙሴ ካርዲናል እንዲደልዩልን አደራ በይልን ። ውድ የሆነቺ ሲልቫኔ አንቺ ዘንድ የምትቆየው ሳጭር ጊዜ ስለሆነ እንኳን ደብዳቤ ያልጸፈችልኝ ! ጊዜዋን ለኔ ደብዳቤ በመጸፍ ማባከን የለባትም ። ሽጋ ልጅ ነች ። ከሷ የምትጠብቂውን ሁሉ ታደርጋለች ። ደሞም ትወደኛለች ። ከዚህ በላይ የምመኘውም የለኝ ። በአንቺ በኩል የላከችልኝ ስጦታ ደርሶኛል ። በጣምም አስደስቶኛል ። ጤናዬ ክፋ አይደለም ። ሆኖም በዋሰ ባደረ ሰውነቴ እየቀጠነ ይሔዳል ። በይ ደህና ሁኝልኝ ። የምጽፍበት ወረቀት አልቆብኛል ። ስለዚህ ከዚህ ላይ ማቆም አለብኝ ። መልካም ምኞቴን እየገለጽሁ . . .

ባፕቲስቲን ።

ተጨማሪ ፡—

የወንድምሽ የልጅ ልጅ በጣም ደስ የሚል ልጅ ወጥቶታል ። ትናን ትና አንድ ሰውዬ ኮርቻ ላይ ተቀምጦ ሲያልፍ አየና ወበጉልበቱ ላይ ያለው ምንድነው ?» ሲል ጠየቀኝ ። ፈረሰኛው በእርግጥም የአደጋ መከላከያ በጉልበቱ ላይ አድርጎ ነበር ። ለመሆኑ ዕድሜው አምስት ዓመት ሊሞላው መቃረቡን አውቀሻል ? በጣም ደስ የሚል ልጅ ነው ። ታናሽ ወንድሙም አሮጌ መጥረጊያ እየጐተተ እንደጋሪ ነጂ ሆኖ ! ሆዋ ! ሆዋ ! ይለዋል ።



@OLDBOOKSPDF

ከዚህ ደብዳቤ ለመረዳት እንደሚቻል ማድሚዜል ባፕቲስቲንና ማሪም ማሏር የአቡኑን ጠባይ ደህና አድርገው ያውቁ ነበር ። እንደጠባያ ቸውም ይይዟቸው ይታዘዙዋቸውም ነበር ። አዲጋ ሊያደርስባቸው የሚችል ውኔታ ሲፈጠርም አደጋው ከመድረሱ በፊት ይተዉ ይሏቸው እንደሆነ እንጂ ድርጊቱ ካለፈ በኋላ እንዳችም ቃል አይተነፍሱም ነበር ።



ከዴ ከተማ አቅራቢያ ከሰው ተገልሎ የሚኖር አንድ ሰውዬ ነበር ፤ ገፍ የሚባል ። በፈረንሳይ አብዮት ዘመን የንጉሥ ነገሥቱ መንግሥት ፈርሶ የሬፑብሊክ መንግሥት እንዲመሠረት ይታገል የነበረውና በወቅቱ ሽብር ሲያካሒድ የነበረው ብሔራዊ ምክር ቤት አባል ነበር ።

በዴ ከተማ አካባቢ የዚህ ሰውዬ ስም ሲነሳ የሚይረበሽና ስቅጥጥ የማይል አልነበረም ። በጣም ግፈኛ ነበር ይሉት ። ብዙ ሰዎች እንደጀፈ አሞራ ይቆጥሩት ነበር ። እንደ ጅፈ አሞራም ገለል ብሎ ብቻውን ይኖራል። ከአብዮቱ በኋላ ንጉሣዊ አገዛዝ እንደገና አንስራርቶ ሥልጣን በያዘበት ወቅት ንጉሡ የሞት ቅጣት እንዲበየንበት ድምጽ ሰጥተው የነበሩት የቀድሞው ብሔራዊ ምክር ቤት አባሎች ከአገር እንዲሰደዱ ሲበየንባቸው ይህ ሰው ግን ንጉሡ በሞት እንዲቀጣ ድምጽ ሳይሰጥ ቀርቶ ስለነበረ እንደሌሎቹ አልተሰደደም ። እንዲያውም ከወታደር ፍርድ ቤት እንኳ አል ቀረበም ። ከሞት ቅጣት ባይሠን ከሰደት በመትረፉም ብዙዎቹን ሳያስገር ምና ሳያስቆጣ አልቀረም ።

ከዴ ከተማ አርባ አምስት ደቂቃ ያህል ከሚያስኬድ ሥፍራ ፡ ከገ በሬዎች መንደርና ከአውራ ጎዳና ራቅ ብሎ ከአንድ ከአልተገራ ሸለቆ ውስጥ እንደአውሬ ብቻውን ዋሻ ውስጥ ይኖራል ፤ ይህ ገፍ በሚል ስም የሚጠራው የቀድሞው ብሔራዊ ምክር ቤት አባል ። እሱ በዚያ ዋሻ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አስቀድሞ ወደዚያ ሥፍራ የሚወስድ የእግር መንገድ ነበር ። ከጊዜ በኋላ ግን የግር መንገዱን ሣር በላው ።

አቡነ ሚሪዬል ስለዚህ ሰውዬ ብዙ ጊዜ ያስባሉ ። ወደሚኖርበት ሸለቆ አሻግረው እየተመለከቱ፤ «ከዚያ ሥፍራ አንዲት ብቸኛ ነፍስ አለች» ይላሉ ። ሰውዬውን ለመገብኘት አስበው ከቤታቸው ወጥተው ራመድ ካሉ በኋላ ሃሳባቸውን ቀይረው ወደቤታቸው የሚመለሱበት ጊዜም ነበ ራቸው ። ይኸውም አቡነ ሚሪዬል እንደሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ሰውዬው ክፉና አደገኛ ሰው ነው ብለው ያምኑ ስለነበረ ነው ። ሆኖም ሳለ መንፈሳቸው አያርፍም ። «የበግ እረኛ በጉ ቢታመምበት በጉ አስጠላኝ ብሎ አይተወ ውም ። እኔም የዚህን ሰው ነፍስ ማዳን አለብኝ» እያሉ እንደገና ከሕሊና ቸው ጋር ይታገላሉ ።



@OLDBOOKSPDF

አቡነ ሚሪዬል ሃሳባቸውን መቁረጥ አቅቷቸው እንዲሁ ሲያመሩምኑ ሳሉ በከተማው ውስጥ አንድ ወሬ ተነዛ ። «ሰውዬው ታሚል . . . ሽባ የሚያደርግ ደዌ አድርበታል . . . የሚያገለግለው ወጣት ልጅ ሐኪም ፍለጋ ወደከተማው መጥቷል . . . ሰውዬው እስከ ነገ ድረስ ባሕይወት የሚቆይ አይመስልም» የሚል ነበር ወሬው ። ዜናውን ከሰሙት መሐከል «እግዚኦብሐር አይማረው !» ያሉም አሊጠሩም ።

ስለሰውዬው መታመም እንደሰሙ አቡነ ሚሪዬል ዘንጋቸውን ይዘው፣ ካባቸውን ደርበው ሲጠይቁት ሰመሐዴ ጉዞ ተነሱ ። ካባቸውን የደረቡት አሮጌ ቀሚሳቸውን እንዲሸፍንላቸው ብቻ ሳይሆን መሸት ሲል ብርድ ሳያወርድ አይቀርም በማለትም ጭምር ነበር ።

ተገዘው ተጉዘው ጀምበር ልትጠልቅ በተቃረበችበት ሰዓት ከሸለቆው ደረሱ ። አንድ ጉድባ ዘልለው ፣ አንድ ጥሻ አለፈው ፣ የጭራሮ አጥር ያለበትንም አልፈው ገለጥ ካለ ሥፍራ ደረሱ ። ልባቸው በፍርሃት ድው ድው ቢሉባቸውም ፍርሃታቸውን አሸንፈው ሬመድ ሬመድ ብለው ሔዱ። ከአሾማ ቁጥቋጦ በስተጀርባ ዋሻውን አገኙት ።

ዋሻው ደሳሳ ጎጆ የመሰለ ፣ ጣራው ገቅ ያለ ፣ አንስተኛና ንጹህ ነበር ። ከበስተውጭ በምስማር የተያዘ ሐረግ አለበት ።

ሽበቶው አዛውንት ፣ ገር ፣ ከመግቢያው በር በስተውጭ አሮጌ ወንበር ላይ ተቀምጠ በመጥለቅ ላይ ያለችውን ጀንበር ያስተውሳል . . . ፊገግ ብሎ ። ከወንበሩ አጠገብ አንድ ወጣት ልጅ ቆሟል ። እረኛ ነው ወጣቱ . . . የሽበቶው አዛውንት አገልጋይ ። አቡኑ በደረሱበት ወቅት ልጁ ለአዛውንቱ ጣሳ ወተት ሲያቀርብለት ነበር ። «ኪያስፈልግኝም . . . አመሰግናለሁ» አለው አዛውንቱ ለወጣቱ እረኛ ።

አቡኑ ጠጋ አሉት ። ሽበቶው አዛውንት የእግራቸውን ኩቲ ሰምቶ ፊቱን ወደ እሳቸው አዞረ ። በጣምም የተገረመ መሰለ ። «እዚህ መኖር ከጀመርህበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ አንድም ሰው ይህንን ቦታ ረግጦት አያውቅም . . . ማን ነምት ጌታዬ ?» አሳቸው ።

«እንኳን ደህና መጡ አባታችሁ» አሉት ።

«እንኳን ደህና መጡ . . . ? ይህንን ስም ከዚህ ቀደም የሰማሁት ይመስለኛል . . . ሰምት ፣ብጹዕ እንኳን ደህና መጡ› ብለው የሚጠሩምት እርስዎን ነው ?»

«አምን . . . ልክ ነህ ።»

ሽበቶው አዛውንት ትንሽ ፊገግ አሉና ፣ «እንዲህ ከሆነ የኔም አቡን ነምት ማለት ነው ?» አላቸው ።



@OLDBOOKSPDF

«ሳልሆን አልቀርም ።»

«ወደ ውስጥ ይግቡ ጌታዬ» ብሎ ሊጨብጣቸው እጁን ዘረጋ ። እሳ ቸው ግን እጁን በመጨበጥ ፈንታ ፤ «ታምመሃል ብለው ነግረውኝ ነበር ። ነገር ግን አልታመምክም ። ወሬው ውሸት በመሆኑም ደስ ይለኛል» አሉት ።

«እየተሻለኝ ሔዷል» አሳቸውና ለአጭር ጊዜ ዝም ብሎ ቆየ ። ቀጠል አድርጎም «በቻ ምን ያረጋል . . . ከሦስት ሰዓት በኋላ እንደምሞት አው ቃለሁ . . . ዶክተር ቢጤ ነኝ ጌታዬ . . . የመጨረሻዋ ሰዓት ስትቃረብ ይሰማኛል ። ሰውነቱ እየቀዘቀዘ ሔዷል ። ትናንትና እግሮቼ ብቻ ቀዝቅ ዘው ነበር ። ዛሬ ግን ቅዝቃዜው እስከጉልበቱ ድረስ ወጥቶ ይሰማኛል ። አሁን ወደ ወገቤ በመውጣት ላይ ነው ። ቅዝቃዜው ከልቤ ሲደርስ አለቀ ልኝ ማለት ነው» ብሎ ጀምበሯን መልከት አሰና «ውብ ነች . . . አይደለ ችም እንዴ ? በውጭ የተቀመጥሁ አካባቢዬን ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ነበር» ብሎ ዓይኑን ወደ አቡኑ መልሶ «ለሞት የተቃረበን ሰው ለመጠየቅ መምጣትዎ ደግ ነው . . . ሲያነጋግሩኝ ከፊለጉም ይደክመዋል ብለው አይስጉ . . . በእንዲህ ያለ ሰዓት ከሰው ጋር መሆን ጥሩ ነው» ብሎ ንግግ ሩን በመቀጠል «አሰከነባ ጠዋት ፣ አሰከነጋቱ ድረስ ብቆይ ደስ ይለኝ ነበር ። ነገር ግን ከሦስት ሰዓት በላይ በሕይወት እንደማልቆይ አውቃለሁ ። ከሦት ሰዓት በኋላ ጭለማ ይሆናል ። ብቻ... ቢሆንስ ምን አለበት ! ለሞት ብርሃን አያሻውም ። ቢያሻውም በክዋክብት ብርሃን እሞታለሁ» አላቸ ውና ዓይኑን ወደ ወጣቱ ልጅ አዙሮ «ሐዲሀ ተኛ ። ትናንትና ሌሊት ሳት ተኛ ስላደርህ ደክሞሃል» አለው ።

ልጁ ወደ ውስጥ ገባ ። ሲገባም ሳለ ሽበቶው አዛውንት በዓይኑ ተከ ተለው ። «አሱ በተኛበት ሰዓት እሞታለሁ» ሲል አሰበ ፤ «እንቅልፍና ሞት መልካም ጐረቤቶች ናቸው !»

አቡነ ሚሪዬል በሽበቶው አዛውንት አነጋገር እጅግም አልተደሰቱም። ለሞት ተቃረብሁ የሚል ሰው የሚናገረው ዓይነት አልሆነ አላቸው ። እሳቸውንም «ብጹዕነትዎ» ባይሳቸውም እንኳ እንደ ካህን «አባ» ብሎ በመጥራት ፋንታ «ጌታዬ» እያለ መናገሩን አልወደዱለትም ። ሽበቶው አዛውንት አብዮተኛ ስለነበረና በአብዮቱ ወቅት እያንዳንዱ ሰው «አንቱ» የሚለውን ትቶ «አንተ» ወይም «ዜጋ» ብሎ ይጣራ እንደነበረ አስታው ሰው «ጌታዬ» ብሎ ስለጠራቸው አደፋውን ለመመለስ ያህል «ዜጋ» ሊሉት ቃጣቸው ። በጊዜው አብዮታዊ ባለሥልጣን ስለነበረም የዚያን ጊዜ ድርጊቱን አንስተው ሊወቅሱትም ዳዳቸው ። እሳቸው ይህንኑ በሃሳ ባቸው ሲያስላስሉ ሳሉ ሽበቶው አዛውንት በትህትና ሲያስተውላቸው ነበር . . . ለሞት የተቃረበ ሰው የሚያሳየው ዓይነት ትህትና ።

በሁለቱ መሐከል የሚታየው አመለካከት ቅራኔ የተመላበት አመለ ካከት ነበር ። አቡነ ሚሪዬል ከሌላ ሰው ጋር በሚሆኑበት ጊዜ አመለካከታ



@OLDBOOKSPDF

ቸው ሰውን የሚስብና የሚያቀርብ እንዲሁም ደስ የሚል ሆኖ ሳለ የአሁኑ አመለካከታቸው ግን ወቀሳ ያዘለ ነበር ። ሽበቶው አሳውንት የቀድሞው ምክር ቤት አባል በመሆኑ እንደ ሕገወጥ ሰው ቆጠሩት ። ሰብአዊ በጎነትም የራቀው መስሎ ታያቸው ።

ከወገቡ በላይ ቀጥ ያለ ሰው ነው ገሬ ። ድምጹ ግን ይንቀጠቀጣል ። ዕድሜው ከሰማንያ ዓመት በላይ ቢሆንም የአካል ጥንካሬ ይታይበታል ። በመኑ የፈጠራቸው የዚህ ዓይነት ሰዎች በብዛት ነበሩ ። ጊዜ የፈተነው መሆኑ ከአቋመ-ና ከአነጋገሩ ያስታውቃል ። ለሞት የተቃረበ ቢሆንም የጤነኛ ሰው ሁኔታ ይታይበታል ። ብሩህ አመለካከቱ ፣ ብርቱ አነጋገሩ ፣ እና ጠቅላላ አቋመ- ሞትን የሚፈታተን ይመስላል ። አዝራኤል ፣ የአስላ ሞች መልአክ ሞት ቢያየው ኖሮ በሸሸው ነበር ! ለሞት ቢተቃረበበት በዚያ ሰዓት እንኳ ፈቱ ላይ የነጻነት መንፈስ ይነበብበት ነበር ። አግሮቹ ግን አይንቀሳቀሱም ። ሞት አጥብቆ የያዘው እግሮቹን ነበርና ። ጭንቅላቱ ግን ሕያው ነው ። ብርሃን የተገናጸፈም ይመስላል ። በምስራታውያን አፈ ታሪክ ከታች ዕብን በረድ ፣ ከላይ ሥጋ ለባሽ የሆነ ንጉሥ አለ ይባላል ። ገሬ የሱ ብጤ ነበር ።

አቡነ ሚሪዬል በአጠገባቸው በነበረ ድንጋይ ላይ ወርደው ቁጭ አሉና «እንኳን ደስ ያለህ» አሉት ።

«ለምኑ ?»

«ንጉሡ ይገደል ብለህ ድምጽ ሳትሰጥበት በመቅረትህ ነዋ !» አሉት ወቀሳ ባዘለ አነጋገር ። ሽበቶው አሳውንት ግን የአቡኑ አነጋገር ወቀሳ አዘል መሆኑን ልብ አላለውም ።

«እምበዛም 'እንኳን ደስ ያለህ' ባያቋርጥ ጌታዬ . . . !» አላቸውና በከረረ ድምጽ ፤ «የጭቆና አገዛዝ እንዲገረሰስ ድምጽ ሰጥቻለሁ» አሳቸው።

«ምን ማለትህ ነው ?»

«የጭቆና አገዛዝ ምንጩ ድንቁርና ነው ። የንጉሥን አገዛዝ ያመጣውም ድንቁርና እንጂ ሌላ አይደለም ። የሰው ልጅ መጣት ያለበት በነ ጉሥ ሳይሆን በሳይንስ ብቻ መሆን ይገባዋል ።»

«ሕሊናስ ?»

«ሳይንስና ሕሊና ምን ሊያቸው ? አንድ ናቸው ። ሕሊና በእያንዳንዱ ጭን ውስጥ ያለ ሳይንስ ነው ። ከዚህ የተለየ ነገር የለውም ።»

የገሬ አነጋገር ከጠበቁት ውጭ ስለሆነባቸው አቡነ ሚሪዬል በጥሞና አዳመጡት ። አሱም ንግግሩን ቀጠለ ፤ «ሉዊ 16ኛ ይገደል በተባሪ ጊዜ


@OLDBOOKSPDF

በእርግጥም አልተስማማሁም ። የሰውን ሕይወት እንዳጠፋ መብት አለኝ ያልኩበት ጊዜም የለም ። ነገር ግን ሽርሙጥና ፣ ባርነት ፣ የድንቁርና ጭለማ ፣ በአጠቃላይም ጭቆና እንዲጠፋ ድምጽ ሰጥቻለሁ ። የሬፑብሊክ መንግሥት እንዲመሠረት ታግያለሁ ። ለሰው ልጅ ወንድማማችነት ፣ ለሰው ልጅ ስምምነት ፣ ለነፃ መቅደድ ድጋፍ ሰጥቻለሁ ። አድልዎና ጥፋት ከምድረ ገጽ እንዲጠፉ የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ ። የኔ ነዚህ ሁሉ መጥፋት ለብርሃን መፈንጠቅ አስፈላጊ ነውና ። ለለውጥ የቆምነው ሁላችንም አሮጌው ሥርዓት እንዲፈርስ አድርገናል ። የመከሬ ምንጭ የነበረው አሮጌው ሥርዓት መፍረሱም የደስታ ምንጭ ሆኗል ።»

«ሁለንተና ደስታ አልሆነማ !» አሉት አቡኑ ።

«አዎን ሁለንተና ደስታ አልሆነም . . . ችግር የተቀላቀለበት ነበርና ። እና በ1814 ዓ.ም. የቀድሞው ሥርዓት እንደገና ሲመለስ ያ ደስታ አዘነመ። ያሳዝናል ! ሥራችን የሚተላ አልሆነም ። የቀድሞው ሥርዓት መፍረስ እውን ሆኖ ቢታይም የቀድሞ አስተሳሰብ በጥዱም ሊጠፋ አልቻለም ። ቀድሞ የነበረውን አለአግባብ መበልጸግ ፣ በሥልጣን መባለግና የመሳሰሉ ትን ማጥፋት በቂ አይደለም ። ነባር ልምዶችም መቀየር አለባቸው ። አለ ዚያ 'አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ ?' እንደሚባለው ነው ።»

«ያፈረሳችሁትን አፈረሳችሁ ። ማፍረስ አሰፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ የለም ለማለትም አይቻልም ። ጸሩ ግን በማፍረስ ድርጊት ላይ ቁጣ ሲታከ ልበት ድርጊቱን አጠራጠረዋለሁ !» አሉት

«የመብት ጉዳይ ቁጣን ያስከትላል ጌታዬ . . . በመብት ምክንያት የሚነሳውም ቁጣ የዕድገት አንዱ ገጽታ ነው ። ለማንኛውም ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከታዩት ድርጊቶች በሙሉ የፈረን ሳይ አብዮት ታሳቂ እንደሆነ አይጠራጠሩ በእርግጥ የተሟላ አብዮት አልነበረም ። ነገር ግን በጣም ከፍተኛ አብዮት ስለመሆኑ የሚጠራጠር ሊኖር አይችልም ። የፈረንሳይ አብዮት ያልታወቁትንና ሕበረተሰብ ነክ የሆኑትን ኃይሎች ነጻ አውጥቷል ። ለሰዎች ርኃታ ፣ ርካታና ጮራ ፈንጥ ቋል ። በአለንበት ዓለም ላይ የሥልጣኔ አየር እንዲነፍስ አድርጓል ። ለሰው ልጅ ቅዱስናን አጐናጽፏል ። ጥሩ ነገር ነው ።»

«ነው ? 1793 ዓ. ም. !» አሉት ።

«አዎ . . . ! 1793 ዓ. ም . . . . ! ይህንንም እንደሚያነሰብኝ አውቅ ነበር ። ለአንድ ሺ አምስት መቶ ዓመታት የአብዮት ደመና ሲዳምን ኖረ ። በመጨረሻም አብዮቱ ፈነዳ ። መብረቅ . . . ነጐድጓድ . . . !»

አቡኑ ባይናዘዙም ከውስጣቸው አንዳች ነገር የሞተ መስሎ ተሰማ ቸው ። ሆኖም ስሚታቸውን ደብተው እንዲህ አሉት ፤ «ዳኛ የሆኑ ሰው በፍትህ ስም ይናገራል ። ካህን የሆነም ሰው በአብያኝነት ስም ይናገራል ።


@OLDBOOKSPDF

አዛኝነትም በከፍተኛ ደረጃ ያለ ፍትህ ነው ። በመብረቅና በነጐድጓድ ስም ጥፋት መሥራት አይገባም» አሉትና አተኩረው አዩት ። «ሕጻኑ ሉዊ 17ኛስ ?» ሲሉ ጠየቁት ተጠል አድርገው ።

በዚህ ጊዜ ሽበቶው ገዢ እጁን ዘርግቶ የአቡኑን ክንድ ያዝ አደረገና «አምን . . . ሕጻኑ ሉዊ 17ኛ በታምፕል ግምብ ውስጥ ተሰውቷል ። ደህንና ለማን ነው ያዘኑት ? ሉዊ 17ኛ ሕጻን ስለነበረ ነው ያዘኑት ወይንስ ንጉሥ ስለነበረ ? ያዘኑት ሕጻን ስለነበረ ከሆነ ከእርስዎ ጋር እኔም አዝናለሁ ። ያዘኑት ንጉሥ ስለነበረ ከሆነ ግን ስለዚህ ጉዳይ አስተያየት ሰመስጠት ጊዜ ያስፈልገኛል» አላቸውና ንግግሩን በመቀጠል ፤ «የወንበዴው ካርቱሽ ወንድም ሌላው ምንም ጥፋት ያልሠራ ሕጻን ልጅ በግሬቪ አደባባይ በብጥቱ ተሰቅሎ ተገድሏል ። የወንበዴው ካርቱሽ ወንድም ከመሆኑ በስተቀር አንዳችም ጥፋት ያላጠፋ ሕጻን ልጅ ነበር ። ሉዊ 17ኛም የሉዊ 15ኛ የልጅ ልጅ ከመሆኑ በስተቀር አንዳችም ጥፋት ያላጠፋ ሕጻን ልጅ ነበር ። አንደኛው ሕጻን ልጅ በግፍ በመገደሉ እንደግዝን ሁሉ ሁለተኛውም በግፍ በመገደሉ አዝናለሁ» አላቸው ።

«ሁሉቱን ስሞች ማገናኘትህ ትክክል አይመስለኝም ።»

«ካርቱሽንና ሉዊ 15ኛን ? የተኛውን ስም ነው የሚታወሙት ?»

ለአጭር ጊዜ ዝምታ ሆነ ። አቡኑ በመምጣታቸው ሳይጸጸቱ አልቀሩም ። ውስጣዊ ፍርሃትም ተሰማቸው ።

የፀሉቱ ክርክር ቀጠለ ።

«የእውነትን ጥሬ ገጽታ ለማየት አይወዱም ጌታዬ» አላቸው ሸበቶው ገዢ ፤ «ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእውነትን ጥሬ ገጽታ ለማየት አይፈሩም ነበር ። በትር ይዞ ገብቶ ቤተ መቅደሱን እንዳጸዳው ላስታውስዎት ይገባኝ ይሆን ? ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለቱ ሕጻናት መሐከል ልዩነት ባላደረገም ነበር ። የወንበዴውን ባርናባስ ልጅና የንጉሥ ሔሮድን ልጅ በአንድ ዓይን መመልከት አያሳፍረውም ነበር ። ዋናው ቁም ነገር የሕጻናቱ ንጽሕና ነው ። ንጹህ ለመሆን የንጉሥ ልጅ መሆን አያሻም ። የቡኮቶ ለባሽም ልጅ ንጹህ ሊሆን ይችላል ።»

«እሱስ እውነት ነው» አሉት አቡነ ሚሪዬል ዝቅ ባለ ድምጽ ።

«የሉዊ 17ኛን ስም ካነሱባኝ ዘንዳ ለመግባባት እንሞክር ጌታዬ . . . ከታላቅ ቤተሰብም ይወለዱ ከብዙሃኑ ለንጹሐን ፥ ለሰማዕታት ፥ ለሕጻናት ማዘን ይገባናል ። በዚህ ከተስማሙልኝ ከ1973 ዓ. ም. በፊት የነበረውንም ሁኔታ ማስታወስ ይገባናል ። ለሉዊ 17ኛ ማልቀስ ካሉብን ከዚያ በፊት ለነበሩትም ማልቀስ ይገባናል ።»



@OLDBOOKSPDF

«ለሁሉም ነው የማለቅሰው» አሉት አቡኑ ።

«በእኩል ደረጃ . . . ! በእኩል ደረጃ ካላሉ ለንጦስት ልጅች ከማ ልቀስ ይልቅ ለብዙሃኑ ልጆች ይበልጥ ማልቀስ ይገባናል ። ለረጅም ዘመ ናት የተሰቃዩት እነሱ ናቸውና !»

አሁንም ዝምታ ሆነ ። ሽበቶው ገፀ አንድ እጁን ተደግፎ ቀና አለ ። በአውራ ጣቱና በአመልካች ጣቱ ጉንጩን ያዝ አድርጎ አቡኑን አተኩሮ አያቸው ፤ «ይስሙኝ» እንደማለት ። ቀጥሎም በኃይለ ቃል ተናገራቸው ፤ «አዎን ጌታዬ . . . ! ሕዝቡ ለረጅም ዘመናት ሲሰቃይ ኖሯል ። ይህ ብቻም አይደል . . . » አሰና ፤ «ኧረ ለመሆኑ ስለሌዊ 17ኛ የጠየቁኝና ጉዳዩን ያነሱብኝ ለምንድነው ? እኔኮ አላውቅትም ። ከዚህ በፊ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ብቻዬን ነው የኖርኩት ። ከዚህ ወጥቼ አላውቅም ። አሁን ካዩት ትንሽ ልጅ በስተቀር ከሰው ጋር ተገናኝቼም አላውቅ ። በእርግጥ ስለእርስዎ ስም የተምታታ ወሬ ሰምቻለሁ ። የስምዎም አጠራር የተም ታታ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ግን ስለሱ ግድ የለም . . . ምንም ለውጥ ሊያ መጣ አይችልም» አለና «በነገራችን ላይ ሠረገላም ወደኋት አለ ? ድምጹን አልሰማሁም ። መንታ መንገድ ካለበት ሥፍራ ፣ ከጥሻው ማዶ አቁመ ውት ይሆን የመጡት ? ለማንሻውም አላውቅትም ብያለሁ ። በእርግጥ አቡን መሆንዎን ገልጸውልኛል ። ነገር ግን አቡን መሆንዎ ስለምግባርዎ ስለሥራዎ ፣ ስለውስጣዊ ባህርይዎ ምንም ነገር አይነግረኝም ። ስለሆነም እንደገና ልደግመውና እርስዎ ማን ነዎት . . . ?

«አቡን ማለት በቤተክህነት ሠንድ እንደልዑል እንደሚቆጠር ይገ ባኛል ። የኔ አቡን መሆን ቀላል ነገር አይደለም ። ክብሩም ገቢ ውም ከፍተኛ መሆኑን አውቃለሁ ። በዓመት ቋሚ የሆነ 15ሺ ፍራንክ . . . ተጨማሪ ገቢ 10ሺ ፍራንክ . . . በጠቅላላው በዓመት 25ሺ ፍራንክ ። አሽከሮችና ገረዶች አሉት ። አቡን የሆነ ሰው ተንደላቅቆ እንደሚኖር ፣ በዕለተ አርብ የዶሮ ሥጋ እንደሚበላ ፣ በሠረገላ እንደሚንዘ ፣ አንድ አሽ ከር ከፊት አንድ አሽከር ከኋላ ሆነው እንደሚያጅቡት ፣ መኖርያ ቤቱ ከቤተ መንግሥት እንደማያንስ . . . ይህንን ሁሉ አውቃለሁ ጌታዬ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ጫማ እንኳ አልነበረውም ! የሆነ ሆኖ ምናልባት ጥቦቦ ሊያስተምሩኝ አስበው ከሆነ የመጡት በቅድሚያ ስለእርስዎ ውስጣ ዊ ባህርይ ለማወቅ አሻለሁ ። እኖ ማን ነዎት ? ከማን ጋር እነጋገራለሁ ልበል?»

አቡኑ አንገታቸውን ሰብረው ፡ «ከትል የማልበልጥ ሰው ነኝ» አሉት ።

«በሰረገላ የሚንዘ ትል ?» ሲል ጮኸባቸው ።

«የፈለግኸውን በል ። እንደዘረዘርከውም በሠረገላ መጣሁ ልበል ። ሠረገላውም ከጥሻው ማዶ አለ ልበል ። በዕለተ አርብ የዶሮ ሥጋ ይቀር



@OLDBOOKSPDF

ብልኛልም ልበል ። የዓመት ገቢዬም ሀያ አምስት ሺ ፍራንክ ነው ልበል ። የገዘፈ መኖሪያ ቤትና አሽከሮችም አሉኝ ልበል ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ የአቡን ግዳጁን ለመፈጸም እንደማያስችሉኝ ምን ማስረጃ አለህ ? የ1793 ዓ. ም. ድርጊትም ሊወገድ የሚቻል አልነበረም የሚያሰኝ ማስረጃስ የት አለ ?» አሉት ።

ሽበቶው ገፅ ግንባሩን በእጁ ጠራረገው ፤ ከፊቱ ጉም ጠርጎ ለማንሳት እንደፈለገ ሁሉ ። «መልስ ከመስጠቴ በፊት ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምንዎታለሁ . . . ስሀተት መሥራቴን ተገንዝቤአለሁ ጌታዬ ። እንግዳዬ እንደመሆንዎ መጠን ላከብሮት ይገባኝ ነበር ። ምሁራዊ ክርክር ይዘንም ሳለን ስለስነዘሩት ሃሳብ ምሁራዊ መልስ በመስጠት ፈንታ ስለሀብትዎና ተንደላቅቀው ስለመኖርዎ በክርክራችን ውስጥ ጣልቃ ማስገባት አይገባኝም ነበር ። ከአሁን ወዲያ እንዲህ ያለውን ሁሉ ከክርክራችን መሐል ጣልቃ እንዳላስገባ ቃል ገብቼልዎታለሁ ።»

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ» አሉት ።

«አሁን . . . ለጠየቁኝ ጥያቄ መልስ ልስጥት ። ብቻ . . . ከምን ላይ ነበርን ? ምን ነበር የሚሉኝ ? የ1793 ዓ. ም. ድርጊት አስከፊ ነበር ነው የሚሉት ?»

«አዎን በጣም አስከፊ ነበር ። የሰውን አንገት ቆርጠ የሚጥለው መሣሪያ ፤ ጊሎቲን የሰዎችን አንገት ቀርጥፎ ሲጥል ማራት በደስታ ያጨበጭብ ነበር ። ስለሱ ምን አስተያየት አለህ ?»

«የሉዊ 14ኛ ወታደሮች የፈረንሳይ ፕሮቴስታንቶችን ይጨፈጭፉ በነበሩበት ወቅት ቦሱዌ ንሴበሆ ለእግዚአብሔር ብሎ ይዘምር ነበር ። እርስዎስ ስለሱ ምን አስተያየት አሉት ?»

ጥያቄውን በጥያቄ መመለሱ አቡኑን አሩጠጣቸው ። እንደ ወስፈም ከልባቸው ገብቶ ጠቅ አደረጋቸው ። መልስ አጥተው ለተወሰነ ጊዜ ዝም አሉት ። ስለቦሱዌ እንዲህ መናገሩም አበሳጫቸው ። እንደሳቸው ያለ ታላቅ ሰው እንኳ የሚያከብረውን ሰ,ያዋርዱበት ልቡ ይቆስላልና ።

ሽበቶው ገፍ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ቢልበትም ክርክሩን ቀጠለ ፤

«የፈረንሳይ አብዮት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከታዩት ድርጊቶች በጣም ክፍተኛው ከመሆኑም በላይ 1793 ዓ. ም. በዘመኑ ለነበረ ጥያቄ ምላሽ ሰጥቷል» አላቸው ፤ «የፈረንሳይ አብዮት በጣም አስከፊ ነበር ይላሉ ጌታዬ ። ነገር ግን ለመላው ንጉሣዊ አገዛዝ ምን ቅጽል እንስጠው ? ካርዬ ወንበዴ ነበር እንበል ። ነገር ግን ሞንትረቪልን ምን ብለን እንጥራው ? ራሲዬ ቴንቢል መሠሪ ነበር እንበል ። ነገር ግን ላሚኞ—ባቪልን ምን ብለን እንጥራው ? ሚይላር ክፉ ሰው ነበር እንበል ። ነገር ግን ሶል



@OLDBOOKSPDF

ታሻንን ምን ብለን እንጥራው ? ታላቅዬው ዱሼን አውሬ ነበር እንበል ። ነገር ግን ሌተሲዬን ምን ብለን እንጥራው ? ዠርዳን—ኩፐ—ቲት ጭራት ነበር እንበል ። ነገር ግን የሉሽዋን መስፍን ምን ብለን እንጥራው ነ» ብሎ ንግግሩን በመቀጠል ፤ «ለንግሥት ማሪ አንቷኔት አዝናለሁ ጌታዬ ። ነገር ግን ለምስኪኗ ሁጓዌኖት ሴትም አዝንላታለሁ ። ይህች ምስኪን ሴት በ1685 ዓ. ም. ፤ በታላቁ ሉዊ ዘመነ መንግሥት ፤ እስከወገቧ ድረስ እንድ ትራቆት ተደርጎ ታሠረች ። ሕጻን ልጇ ከእቅፏ ተወሰደባት ። ጡቷ ወተት ከብዶት ይታይ ነበር ። የተራበው ሕጻን ልጇ ጡቷን እያየ ምርር ብሎ የደም እምባ አለቀሰ ። ይህች ሴትዮ ፕሮቴስታንት ከመሆን በስተቀር ያጠፋችው ጥፋት አልነበረም ። እና ሕግ አስፈጻሚው 'ጥፋትሽን እመኚ' አላት ። ሴትዮዋ ከሁለት አንድ መምረጥ ነበረባት ፡— ጥፋተኛ አይደለ ሁም በማለት ሕጻን ልጇ በረሃብ እንዲሞት ምክንያት መሆን ወይም ጥፋ ተኛ ነኝ በማለት ሕሊናዋን መሸጥ ። ታዲያ ስለዚህች ሴትዮ ምን አስተያ የት አለዎት ጌታዬ ?» ብሎ አሁንም ንግግሩን ቀጠለ ፤ «የፈረንሳይ አብ ዮት እንዲከሰት ምክንያት ነበረው ጌታዬ ። የአብዮቱ አስከፊነት ወደ ፊት ይከሳል ። በአብዮቱ ምክንያት ዓለም የተሻለ ቦታ ይሆናል ። የሰውም ልጅ የተሻለ ሕይወት ይኖራል ። ነገሩን ከዚህ ላይ ማቆም ይገባኛል ጌታዬ ። በሞት አፋፍ ላይ ነው ያለሁት» ብሎ የመጨረሻ ታላ አከለበት ፤ «አዎ . . . ለዕድገት ታስቦ የሚፈጸመው አስከፊ ድርጊት አብዮት ተብሎ ይጠራል ። ነገር ግን ምንም ያህል አስከፊ ቢሆን በዚህ ድርጊት ምክንያት የሰው ልጅ ወደ ዕድገት ደረጃ እንደሚሸጋገር አያጠራጥርም ።»

ሸበቶው ገፀ አቡነ ሚሪዬልን እንዳሰመናቸው አልተጠራጠረም ። አሳቸውም በክርክሩ እንዲተሸነፉ ልባቸው አውቆታል ። ይሁን እንጂ ያላሰመናቸው አንድ ነጥብ ብቻ ነበር ። ይህንን በሚመለከት እንዲህ አሉት ፤ «ዕድገትና እምነት አይነጣጠሉም ። ክፉ ነገር በሳን ነገር ሊያገ ለግል አይችልም ።»

ሸበቶው ገፀ መልስ አልሰጣቸውም ። ሲንቀጠቀጥ ነበር ። ወደሰማይ አንጋጦ ተመለከተና ዓይኖቹ እምባ ቋጠሩ ። ቀጥሎም እምባው በጉንጩ ኮለል ብሎ ወረደ ። ገቾ ባለም ድምጽ እንዲህ አለ ፤ «አ አንተ ! የሰው ልጅ የመጨረሻው ዓላማና ግብ የሆንከው አንተ ! አንተ ብቻ አለህ . . . ትኖ ራለህም ።»

አቡነ ተደናገጡ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሸበቶው ገፀ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ ፤ «መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ሕያውነት አለ ። ከዚያ ይገኛል» ጣቱን ወደ ሰማይ ሰቅሎ እያመለከተ ፤ «ይህ ሕያውነት ሰብአዊነት ባይኖረው ኖሮ ሰብአዊነትም መጀመሪያና መጨረሻ ባልኖረው ነበር ። ይህ መጀመ ሪያና መጨረሻ የሌለው ሕያውነት እግዚአብሔር ነው ።»

ሸበቶው ገፀ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ መንፈሱ በደስታ ተመልቶ ነበር ። ተናግሮም ሲጨርስ ዓይኖቹ ተዘጉ ፤ ደክሞት ነበርና ።



@OLDBOOKSPDF

አቡኑ የሰውየውን ሁኔታ ተረዱ ። በሕይወት የሚቆይበት ጊዜ እያ
ከተመ በመሐድ ላይ ነበር ። የእሳቸውም አመጣጥ በዚህ ሰዓት ከሱ ጋር
ለመሆንና መንፈሳዊ ግዳጃቸውን ለመፈጸም ነበር ። ሰውዬው በተናገረው
ቃል ልባቸው ሞቶ ፤ የተሸበሸበ ፥ ያረጀና የቀዘቀዘ እጁን በእጃቸው ሰቀም
አድርገው ይዘው ፤ የተዘጉትን ዓይኖቹን አተኩረው እየተመለከቱ ጐንበስ
ብለው እንዲህ አሉት ፤ «ይህች ቅጽበት የእግዚአብሔር ናት ። ለመሆኑ
መገናኘታችን ከንቱ ሆኖ ቢቀር ኖሮ የሚያስደስት ነበር ብለህ ታስባለህ ?»

ሽበቶው ገሬ ዓይኖቹን እንደገና ገለጣቸው ። በገጹ ላይ ከባድ ሀዘን
ይታይበት ነበር ። «ሕይወቴን ያሳለፍኩት በማሰብና በማሰላሰል እንዲ
ሁም በምርምር ነው» አላቸው ረጋ ብሎ ፤ «የሀገር ጥሪ ድምጽ በሰማሁ
በት ወቅት ዕድሜዬ ስድሳ ዓመት ደርሶ ነበር ። የጥሪውን ድምጽ ሰምቼ
ዝም አላልኩም ። ጥሪውን ተቀበልኩ ። በሥልጣን የመባለግ ሁኔታ
ሰፍኖ ነበር ። ተዋግቼዋለሁ ። ሞክሬያም ነበር ። ታግዬዋለሁ ። መሠረታዊ
መብቶችና መመርያዎችም እንዲከበሩ አቅሜ በፊቀደልኝ መጠን ሠርቻ
ለሁ ። አገራችን ስትወረር ከወራሪው ጋር ተሞግቻለሁ ። ደረቴን ለጦር
ሰጥቻለሁ ። ድሮም ቢሆን ሀብታም ሰው አልነበርኩም ። ዛሬም ድሃ ሰው
ነኝ ። የመንግሥት ባለሥልጣን ነበርኩ ። የመንግሥት ሀብት ንብረት ፥
ወርቅና ብር በቁጥሬ ሥር ነበር ። ይሁን እንጂ ሰምሳ ወይም ሰራት
ከ22ቱ በላይ ወጪ ያደረግሁበት ጊዜ የለም ። የተጨቆኑትን ረድቻለሁ ፥
የተሰቃዩትን አጽናንቻለሁ ። በእርግጥ የመቅደስን ልባስ ጨርቅ እንስቼ
ተድፍለሁ ። ይህንን ያደረግሁት ግን የአገሬን ቁስል ላስርበት እንጂ ለሌላ
አይደለም ። የሰው ልጅ በብርሃን ጉዳና ወደፊት እንዲራመድ ድጋፍ ሰጥ
ቻለሁ ። አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በጠላቶቼ ጉን የቆምሁበት ጊዜም አለ ። ጠላ
ቶቼ የምላቸው በእርስም ሙያ ላይ የተሰማሩት ናቸው ። በ1793 ዓ. ም.
በፒቱጂም ፥ በፍላንደር ውስጥ የሚገኘውና ጥንት የሜሮቬንጂያን ነገሥ
ታት ቤተ መንግሥት በነበረበት ሥፍራ ያለውን የእርባኒስቶች ጌዳም ፥
የሴን ክለር እን ቦልየ ቤተ ክርስቲያንን ከአደጋ አድኛዋለሁ ። በተሠጠኝ
ሥልጣን መሠረት ግዳጄን ተወጥቻለሁ ። ለመፈጸም የምችለውን ደግ
ሥራም ሁሉ ሠርቻለሁ ። ከዚያስ በኋላ ምን ደረሰብኝ ? እንደአውሬ ያድ
ኑኝ ፥ ይከታተሉኝ ፥ ያሰቃዩኝ ፥ ስሜን ያጠፉኝ ፤ ይሳለቁብኝ ፥ ይንቁኝ ፥
ይረግሙኝ ፥ ያወግዙኝም ጀመር ። ብዙ ሰዎች እኔን ለመናቅ ሰበብ ያላ
ቸው ይመስላቸዋል ። እንደተዋረደም ሰው ይቆጥሩኛል ። በበኩሴ ሞገንንም
ሰው አልጠላም ። ሰዎች ለምን ጠሉኝም ብዬ አልጨነቅም ። ሁሉንም
በጸጋ ተቀብያለሁ ። አሁን ዕድሜዬ 86 ዓመት ደርሷል ። በሞት አፋፍ ላይ
እገኛለሁ ። እና ምን ሊጠይቁኝ ነው አርስዎ ከዚህ የመጡት ?» ሲል ጠየ
ቃቸው ።

«በራሔ እንድትሰጠኝ ነው» ብለው ተንበረከኩለት ። ከአጭር ጊዜ
በኋላ ዓይናቸውን አቅንተው ቢመለከቱ የሰውየው ፊት ርጋታ ነግሶበት
አዩ ። ሕይወቱ አልፋ ኖሯል !

አቡኑ በጥልቅ ሃሳብ ተውጠው ወደ መኖርያ ቤታቸው ተመለሱ ።
ለሊቱን በሙሉ ሲጸልዩ አደሩ ። በማግሥቱ ጠዋት አንዳንድ ሰዎች ስለ


@OLDBOOKSPDF

ቀድሞው የምክር ቤት አባል ፣ ስለገዢ ሊጠይቋቸው ሞከሩ ። ወዲ ሰማይ ከማመልከት በስተቀር ሌላ መልስ አልሰጧቸውም ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለመከረኞችና ሰልጆች የነበራቸው ፍቅር እጥፍ ሆነ ። ስለመከረኛው ገዢ በሰሙም ቁጥር ሃሳብ ይይዛቸው ጀመር ። የሁለቱ መንፈስ መገናኘትና የሕሊናቸውም ተመሳሳይነት አቡነ ሚሪዬል ወደ ፍጹምነት በሚያደርጉት ጉዞ ላይ አሻራውን ሳይጥልባቸው አልቀረም ።

በአቡኑ ገብኝት ቅሬታ ያደረባቸው ጥቂቶች አልነበሩም ። «ለምን ገበኙት ? የቀድሞው የምክር ቤት አባል ከይሲ መሆኑን የማያውቅ የለም ። እሱ እንደሆነ ወዲ ክርስቲያናዊ ሕይወት ይገባል ማለት ዘበት ነው ። አብዮተኞች ሲባሉ ሁሉም ያው ናቸው ። ሥጋዊ ሕይወት እንጂ መንፈሳዊ ሕይወት የላቸውም ። እንዲህ ከሆነ ሰይጣናዊ የሆነ ሰው ምን እንደሚመስል በዓይናቸው ስማየት ካልሆነ በስተቀር ምን ሊፈጥሩ እሱ ዘንድ ሔዱ ?» እያሉ አጉረመረሙ ብዙ ሰዎች ።

— 11 —

አቡነ ሚሪዬል የፖለቲካ ሰው ቢይሆኑም በዘመናቸው ስለነበረው ሁኔታ ምን ዓይነት አስተያየት እንደነበራቸው መግለጽ ይገባል ። ይህንንም ለመግለጽ ጥቂት ዓመታት ወደ ኋላ መለስ ማለት ያሻል ።

አቡነ ሚሪዬል አቡን ሆነው ከተሰየመ በኋላ አሳቸውና ሌሎችም በርክት ያሉ አቡኖች በናፖሌዎን ቦናፓርት ፈቃድ «ባሮን» የተሰኘ የመኳንንት ማዕረግ ተሰጥቷቸው ነበር ። እንደሚታወቀው የሮማው ጳጳስ በ1809 ዓ. ም. በሐምሌ አምስትና በሐምሌ ስድስት መሐከል በነበረው ሌሊት ተይዘው ከሥራ ታግደው ነበር ። በዚሁ መነሻ የፊረንሳይና የኢጣሊያ አቡኖች በፓሪስ ከተማ ጉባዔ ተጠሩ ። ጉባዔው ሰኔ 15 ቀን 1811 ዓ. ም. ኖትረ ዳም ካቴድራል በተሰኘው በማርያም ቤተክርስቲያን ፣ በናፖሌዎን አጎት ፣ በካርዲናል ፌሽ ስብሳቢነት ተከፈተ ። በስብሰባው ከተገኙት ዘጠና አምስት አቡኖች መሐከል አንዱ አቡነ ሚሪዬል ነበሩ ። ከአቡነ ሚሪዬል በስተቀር እነዚህ ሁሉ አቡኖች በከፍተኛ ድሎት የሚኖሩ ከባድ የቤተክህነት ባለሥልጣኖች ስለነበሩ ከገጠር ቄስ የሚቆጠሩት አቡነ ሚሪዬል ከእነሱ ጋር በሃሳብ ሊጣጣሙ አልቻሉም ። በናፖሌዎን ቦናፓርት ትዕዛዝ በገባዔው መጀመሪያ ላይ ቢገኙም ከአጭር ጊዜ በኋላ ወዲ ገጠር ሰበካቸው ወደ ዴ ተመለሱ ። ለምን በፍጥነት እንደተመለሱ ቢጠየቁም «ያሳፈርኳቸው መስለኝ . . . » ሲሉ መለሱ ፤ «በውጭ ያለውን ሁኔታ በእኔ አማካይነት ለመረዳት ቻሉ ። ነገር ግን ከታፈነ ቤት ውስጥ እንደሚገባ ነፋስ ስለሆንኩባቸው በዚያ ለመቆየት አልቻልኩም ።» በሌላም አጋጣሚ ስለዚሁ ጉዳይ ተነሳና «ምን ይደረግ ! ከዚያ የነበሩት አቡኖች የተከበሩ ልዑላን ናቸው ። እኔ ግን ምስኪን የገጠር አቡን . . . !» ሲሉ ተናገሩ ።


@OLDBOOKSPDF

አቡነ ሚሪዬል በጉባዔው የተገኙትን አቡኖች ፈጽሞ አላስደሰቷቸውም ። አንድ ቀን በድሎት ከሚኖሩት አቡኖች ከአንደኛው መኖሪያ ቤት በተገኙበት ወቅት ያዩት ሁሉ አስደንቋቸው ፤ «ካባዎቹ እንዴት ያምራሉ . . . ! የቢቱ ምንጣፎች እንዴት ያምራሉ . . . ! የአሽከሮቹ የደምብ ልብሶች እንዴት ያምራሉ . . . ! ነገር ግን የተራቡ ፥ የታረዙ ፥ በስቃይና በመከራ የሚኖሩ ብዙዎን እያሉ የዚህ ዓይነት የድሎት ኑሮ መኖር አያሳፍርም . . . ? ለህሊና አይከብድም ?» አሉ ይባላል ።

ይህም ስለተባለ ድሎት ሁልጊዜም የሚነቀፍ ነው ማለት አይደለም ። ቢሆንማ ኖሮ የጥበብ ሥራም የድሎት ሥራ ስለሆነ መነቀፍ በተገባው ነበር ። እንዲሁም አልፎ አልፎ ለምሳሌ በበዓላት ቀን መፈንጠዝ ፥ መደስት አያስነውርም ። በተረፈ ግን ካህን የሆነ ሰው ለዘለቄታው ተንደላቅቆ በድሎት መኖር አይገባውም ። የድሎት ሕይወት ከመንፈሳዊ ሥራ ጋር አብሮ አይሔድም ። «ሀብታም ካህን» ሲሉ ቃሉ ሊጀር ይከብዳል ። ካህናት ከድሆች መራቅ አይገባቸውም ። የድሆችን ኑሮ መኖር አለባቸው ። ደሃ ያልሆነ ካህን ከድሆች ተቀራርቦ ለመኖር እንዴት ይቻለዋል ? የጉል በት ሥራ የሚሠራ ሰው ከት ቢያና ከአቧራ ሊርቅ አይችልም ። ከእሳት ማንደጃ አጠገብ የተቀመጠ ሰው ከመሞቅ ሊርቅ አይችልም ። የእሳት ወላፈን ካለበት ሥፍራ የሚሠራ ሠራተኛ ከጸጉሩ አንድ ዘለላ እንኳ ሳይለ በለብበት ፥ ጥፍሮቹ ሳይጠቁሩ ፥ ሰውነቱን ሳያልበው ፥ ጥላሸት ሳያርፍበት ሊቀር እንዴት ይችላል ? የእውነተኛ ካህን ፥ በተለይም የእውነተኛ አቡነ ምልክቱና ማረጋገጫው ድህነቱ ነው የሚሉ ነበር የአቡነ ሚሪዬል አስ ተሳሰብ ።

ስለካህናት አኗኗር የነበራቸው አስተሳሰብ ይህ ቢሆንም በዘመኑ አክራሪ በነበሩ የፖለቲካ» ወይም የመንፈሳዊ ፍልስፍና ጉዳዮች እጅግም አይከፉሉም ነበር ። መንግሥትንና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለ ከት ጉዳይ አስተያየት ከመሰንዘር በጣም ይቆጠቡ ነበር ። አስተያየት እን ዲሰጡ ቢገደዱ ኖሮ ግን የፊረንሳይን ካቶሊኮች አስተያየት ከመደገፍ ይልቅ የጣሊያን ካቶሊኮችን አስተያየት በደገፉ ነበር ። የጣሊያን ካቶሊ ኮች ከመንግሥት ሥልጣን የሮማ ጳጳስ ሥልጣን ይበልጣል ባዮች ነበሩ ።

ከዚህ በተጨማሪም ከ1813 ዓ. ም. ጀምሮ ፤ ይህም ማለት ናፖሌዎን ቦናፓርት ከሥልጣን ለመውረድ በመንገዳገድ ላይ በነበረበት ጊዜ አቡነ ሚሪዬል አሱን በመደገፍ ፈንታ የሱን ተቃዋሚዎች ይደግፉ ጀመር ። ናፖሌዎን ቦናፓርት ለመጀ ቀናት በኤልባ ደሴት በግዞት በቆየበት ወቅት ስለሱ በገሐድ ጸሎት እንዳይደረግ አገዱ ። ከግዞቱም በኋላ እግረ መንገዱን በደ ከተማ በሚያልፍበት ወቅት ሒደው ሊያነጋግሩት ሳይፈቅዱ ቀሩ ።

ከዚህ ጋር የተያያዘ ሴላም ነጥብ አለ ። አቡነ ሚሪዬል ሁለት ወንድ ሞች ነበሯቸው ፤ አንደኛው ጄኔራል ፥ ሁለተኛው ጡረታ የወጣ የቀድሞ አገረ ገዥ ። አልፎ አልፎ ለወንድሞቻቸው ደብዳቤ ይጽፉላቸው ነበር ። በፓሪስ ከተማ ፥ በክሴት ጐዳና ይኖር ዕንበረው ለቀድሞው አገረ ገዥ



@OLDBOOKSPDF

ሠንድማቸው የሚጽፉት ደብዳቤ ወንድማዊ ፍቅር የተመላበት ሆኖ ሳለ ለጀኔራሉ ወንድማቸው የሚጽፉት ደብዳቤ ግን እስከዚህም የሞቀ አልነበረም ። ይኸውም ናፖሌዎን ቦናፓርት ሊያዝ ሲል ባመለጠበት ወቅት ጀኔራሉ ወንድማቸው 1200 ወታደሮችን ይዞ ቢከታተለውም ናፖሌዎንን ሳይዝ በመቅረቱ ሆን ብሎ ያደረገው መስሏቸው አኩርፈውት ስለነበረ ነው ።

እና ሃሳባቸው ዘለዓለማዊ በሆኑ ነገሮች የተያዘ ቢሆንም ጊዜአዊ በሆኑ ነገሮች የሚጠመዱበትና ለክፉም ለደጉም ወገናዊ የሚሆኑበት ጊዜ ነበራቸው ። በእርግጥም እንደሳቸው ያለ ሰው በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ ባይገባ ይመረጣል ። የፖለቲካ ጉዳይ ስንል ለዕድገት የሚደረግ ጥረት ፣ አገር ወዳድነት ፣ ሰብአዊነት ፣ ዲሞክራሲና የመሳሰሉት ማለታችን አይደለም ። ይህንንማ ማለታችን ቢሆን ኖሮ ሰው ሁሉ በደገፈው ነበር ። በአጠቃላይ ለማለት የፈለግነው ፤ አቡነ ሚሪዬል የንጉሣዊ አገዛዝ ደጋፊ ባይሆኑ ኖሮና ሃሳባቸውንም በማንኛውም ጊዜ ከእውነት ፣ ከፍትህ ፣ እና ከችሮታ ሀር ባያደርጉት ኖሮ በጣም የተሻለ በሆነ ነበር ለማለት ያህል ነው ።

አቡነ ሚሪዬል ስፖለቲካ ሥልጣን የተፈጠሩ ባይሆኑም በመብትና በነጻነት ስም ፊላጭ ቆራጭ የነበረውን ናፖሌዎን ቀደም ብሰው ቢቃወሙት ኖሮ እናደንቃቸው ነበር ። አሳቸው ግን የተቃወመውን ሰመውደቅ በሚንገዳገድበት ጊዜ እንኪ ሥልጣን ላይ ተደላድሎ በተቀመጠበት ወቅት አልነበረም ። ሰዎች ስንባል ይኸው ነን ። አንድ መሪ ሥልጣን ሲይዝ የሚፈጽማቸውን ድርጊቶች ስናደንቅ አንኖርና ከሥልጣን ለመውረድ በሚንገዳገድበት ጊዜ የሚፈጽማቸው ተግባሮች አይጥሙንም ። መሪው ሥልጣን ሲይዝ ዝም ያሉት ወይም የደገፉት ሰዎች ከሥልጣን ለመውረድ በሚንገዳገድበት ጊዜ እሱን መቃወም አይገባቸውም ። አስከመጨረሻው መቃወም ያለባቸው ከመጀመሪያ ጅምሮ የተቃወሙት ብቻ መሆን ይገባቸዋል ።

በዚህ ረገድ 1812 ዓ. ም. የምንለውን ያሳጣን ጀመር ። ናፖሌዎን በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ እንደ ጣዖት ሲያመልከው የነበረው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት በ1813 እና በ1814 ዓ. ም. አፉ ተከፍቶ ናፖሊዎንን ያዋርደውና ያወግዘው ጀመር ። ይህ ድርጊት በጣም የሚያስቆጣ ነበር ። እንዲሁም በ1815 ዓ. ም. ፣ የፈረንሳይ አገር ለጠላቶቿ ልትንበረከክ በተቃረበችበት በዚያ ቀውጢ ወቅት ፣ የዎተርሉም ውርደት መታየት በጀመረበት በዚያ ሰዓት አቡነ ሚሪዬልም ሆኑ ሌሎች ሰዎች የናፖሌዎንንና የአገሩን አሳዛኝ ሁኔታ አለመገንዘባቸው ሊያስወቅሳቸው እንኪ ሊያስመሰግናቸው አይችልም ።

በተረፈ ግን አቡነ ሚሪዬል ትክክለኛ ፣ እውነተኛ ፣ ከቀና አስተሳሰብ ያልራቁ ፣ እውቀትና ትህትና ያላቸው በጎ ሰው ነበሩ ። በእርግጥ የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን ነቅፈናል ። ይሁን እንኪ በፖለቲካ አስተሳሰባቸውም



@OLDBOOKSPDF

ቢሆን ከብዙዎቻችን የተሻሉ ነበሩ ። የሆነ ሆኖ በአዛኝነታቸው ተወ ዳዳሪ አልነበራቸውም ። ለምሳሌ አንድ የማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ነበር ፤ በናፖሌዎን ፈቃድ የተቋጠረ ። የመኰንንነት ማዕረግ ያልነበረውና የቀ ድሞ ክብር ዘበኛ አባል የነበረ ሽማግሌ ሰው ነበር ። በአስተርሊዝ በፊጸ መው ጀብዱ ምክንያት «ሌዠዮ ዶነር» የተባለ የክብር ሠራዊት አባል ነበር ። የናፖሌዎን ቦናፓርት ደጋፊም ነበር ። ይህ ሰውዬ ሉዊ 18ኛን በሚ መለክት አዘወትሮ የዘለፋ ቃል በመናገሩና ዘለፋውም ሕገ ወጥ በመሆኑ ከማዘጋጃ ቤቱ ሥራ ተባረረ ። «የእንግሊዝ ገምባሌ የሚያደርግ ማንቁር ቲያም . . . ! እስከነተክታዮቹ ወደ ጥሩስያ ቢሰደድ ይሻለዋል !» የሚል ነበር የዘለፋው ቃል ። ይህንን ያለበት ምክንያት እንግሊዝንና ጥሩሲያን ይጠላ ስለነበረ ነው ። ታዲያ ከሥራ ከተባረረ በኋላ ሚስቱንና ልጅቡን የሚመግብበት ገንዘብ አጣ ። በጣም ተቸገረ ። አቡነ ሚሪዬል መቸገሩን ሰምተው ስለተናገረውም የዘለፋ ቃል ክገሰጹት በኋላ በካቴድራሉ ውስጥ ሥራ እንዲሰጠው አዘዙ ። አቡኑ የዚህ ዓይነት ሩህሩህ ሰው ነበሩ ።

የዴ ከተማ ሕዝብ ናፖሌዎን ቦናፓርትን ያደንቅ ነበር ። አቡነ ሚሪ ዬልን ግን ያፈቅራቸው ነበር ፤ ያውም ናፖሌዎንን እንደሚቃወሙ እያ ወቀ ! በዴ ከተማ ውስጥ ለዘጠኝ ዓመታት በፈጸሙት መንፈሳዊ ሥራ ምክንያት የማያከብራቸው ሰው ከቶም አልነበረም ።



ጄኔራል የሆነ ሰው በመኰንኖች ይታጀባል ። አቡነ የሆነ ሰው በካ ህናት ይታጀባል ። ማንኛውም ባለሥልጣን የሆነ ሰው ከሥራ አጫፋሪዎች ፣ አሽቃባጮች አሉት ። ይህውም በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ ባለሥልጣነ ጥላ ሥር ያሉ ሁሉ ለወደፊት ለመሾምና ለመሸለም ፣ በመደቻውም ዕድ ገት ለማግኘት የበላያቸውን ባለሥልጣን መለማመጥ ፣ ማስደሰት ፣ ማክ በር ፣ ማቆላመጥ ፣ ማጅብና ማኩራራት ስላለባቸው ነው ።

በቤተክህነት ውስጥ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ፣ በቤተ መንግሥት አካ ባቢም የታወቁ ከባድ አቡኖች አሉ ። እነዚህ ከባድ የቤተ ክህነት ባለሥ ልጣኖች በቤተክህነትና በመንግሥት መሐከል እንደድልድይ ሆነው ያገለግላሉ ። እነሱን የሚጠጉ የታዳሉ ናቸው ። ምክንያቱም ተደማጭ ነትና ሥልጣን ስላላቸው በእነሱ ሥር ላሉት ታታሪዎች ፣ የማቆላመጥ ጥበብ ላላቸው ፣ እንዲሁም ለታላላቆችና በየደረጃው ለሚገኙትም ያብ ሮች ስጦታ ያዘንቡላቸዋል ። እነሱ ከፍተኛ ሹመት ሲያገኙ በነሱ ሥር ያሉትም ደረጃቸው ከፍ እያለ ይሔዳል ። ባለሥልጣኑና በሥሩ ያሉት ሁሉ በአንድ ላይ እንደሚጓዙ የሰማይ ከዋክብት ናቸው ። ባለሥልጣኑን የሚከበው ብርሃን ለጭፍሮቹም ይደርሳል ። ባለሥልጣኑ ከአቡንነት ወደ ሊቀ አቡንነት ፣ ከሊቀ አቡንነት ወደ ካርዲናልነት ከፍ እያለ ሲሔድ



@OLDBOOKSPDF

በሱ ሥር ያሉትም በየደረጃቸው ከጥ ዙጥ እያሉ ይሐዳሉ ፥ ይሾማሉ ይሸለማሉ ። የቤተክህነት ፍርድ ቤት ዳኛ ፥ ሂሳብ ተቆጣጣሪ ፥ የሮማው ጳጳስ የእልፍኝ አስከልካይ የመሆን ዕድል ያገኛሉ ። ብጹዕ ፥ ብጹዕ ወቅዱስ ፥ እና በመጨረሻም የሮማ ጳጳስ የመሆን ዕድልም ሊያጋጥማቸው ይችላል ። ስለሆነም ከቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ተመርቆ የወጣ ሁሉ በጣም ሰፊ የሆነ የዕድገት ዕድል አለው ፤ ካወቀበትና ከከባድ የቤተ ክህነት ባለሥልጣን ከተጠጋ ። ምንም እንኳ ክህነት ጥሪ ነው ቢባልም ስንቶቹ ናቸው በጥሪው ስም ለሥልጣን የሚራኮቱት !

አቡነ ሚሪዬል በድህነት የሚኖሩ ፥ ትሁትና አለሁ አለሁ የማይሉ ሰው በመሆናቸው ከከባድ ባለሥልጣን የሚቆጠሩ አልነበሩም ። በዚህ ምክንያት ወጣት ካህናት አያጅቧቸውም ። በእሳቸው አማካይነት እሾማለሁ እሸልማለሁ የሚል ቂስ የለም ። በእሳቸው አካባቢ የነበሩት እንደ እሳቸው አዛውንት የሆኑና ያሰቀሳቸው ፥ ወደፊት እሾማለሁ እሸለማለሁ የማያሉት ብቻ ነበሩ ። ወጣት ካህናት በአቡነ ሚሪዬል እጅ ከተካኑ በኋላ በእሳቸው አስተዳደር ሥር ሆነን እናድጋለን የሚል ተስፋ ስላልነበራቸው ወዲያውኑ ከእሳቸው ርቀው ሔደው በኤክስ ወይም በአች ሊተ ጳጳስ ሥር ያገለግሉ ነበር ። በእሳቸው ሥር ማገልገል እንደመቆርቆዝና ደህይቶ እንደ መቅረት ይቆጥሩት ነበር ። በዚህ ምክንያት አቡነ ሚሪዬል ብቸኛ ሆነው ይኖሩ ነበር ።

የኑሮ ስምረት የሥራ ውጤት ነው ብለው የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ ። ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ሁል ጊዜ ትክክል አይደለም ። የስኮሪ ተከት የወጣለት ሰው ሕይወቱ ሲለምርለት ይችላል ። ነገር ግን በአጋጣሚ የተገኘ ሀብት የሥራ ውጤት ነው ስማለት ይቻላል ? ገቨናልና ታሲት የዚህ ዓይነቱን አስተሳሰብ ይነቅፉታል ። በጥንቱ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በአኝም ዘመን ለኑሮ ስምረት አገልጋይ የሆነ ፍልስፍና አለ ። ይህ ፍልስፍና ኑሮህ የሰመረ እንዲሆን ተጣጣር ፤ ብልጽግና የችሎታ ውጤት ነው ይላል ። ነገር ግን አንድ ሰው በስኮሪ እጣ ሊበለጽግ ይችላል ብለናል ። በስኮሪም ሆነ በአጋጣሚ የከበረ ሰው ታላቅ ሰው ነው ማለት አይደለም ። ብዙ ሰዎች ግን ታላቅነትን ከብልጽግና ጋር ያዛምዱታል ። ባለጸጋውን ያከብሩ ታል ። ሰደስታና ለማንኛውም ነገር ቁልፉ ሀብት የሆነ ይመስላቸዋል ። ይህ ግን በጠባብ አስተያየት የተመሠረተ እምነት እንጂ እውነት አይደለም ። በብዙሃኑ ዘንድ ግን አንድ ሰው በማናቸውም መንገድ ሕይወቱ ቢስምርለት እንደ ሙሴ ፥ እንደ ኤቪል ፥ እንደ ዳንት ፥ እንደ ሚቬል አንዥ እንደ ናፖሊዎን ቦናፓርት ያደነታል ። አንድ ተራ ሠራተኛ ከፍተኛ ባለሥ ልጣን መስሎ ቢቀርብ ፥ አንድ አጭበርባሪ ዶራሲ ኮርኔይን መስሎ ዣትሪዬት» የተባለውን ድርሰት ያረስኩ ቢል ፥ አንድ ስልብ የሆነ ሰው ቁባቶች አሉኝ ቢል ፥ አንድ አራጣ አበዳሪ የሆነ ሰው ባጭር ጊዜ ውስጥ ሚሊየኔር ቢሆን ፥ አንድ አነፍናፊ ቂስ አቡን ሆኖ ቢሰየም ፥ አንድ ከበ ርቱ የሆነ ሰው ጡረታ በሚወጣበት ጊዜ የጎንዘብ ሚኒስትር ሆኖ ቢሾም . . ወዘተርፈ . . . እነዚህ ሁሉ ታላላቅ ሰዎች ናቸው ማለት ነው ? ከንቱ አስተ ሳሰብ !



@OLDBOOKSPDF

በእምነት ረገድ የተለያየ አቋም ቢኖረንም በሌላው ሰው እምነት ውስጥ የሚገኙ በጎ ገጽታዎች የተዋበና የላቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ ልንክድ አንችልም ። የአቡነ ሚሪዬል እምነት በማብዝነት ላይ የተመሠረተ አልነበረም ። ባለኃይላቸው አማኝ ነበሩ ።

አቡነ ሚሪዬል ብርቱ አማኝ ከመሆናቸውም በላይ ሰመላው የሰው ልጅ የላቀ ፍቅር ነበራቸው ። በዚህ ምክንያት በቀላሉ ሊታለሉ የሚችሉ ሰው ነበሩ ። ሰውን የሚያፈቅርና የሚያምን ሰው በክፉ ሰዎች በቀላሉ ሊታለል ይችላልና ።

አቡነ ሚሪዬል ሰውን ከማፍቀራቸው የተነሳ ለማንኛውም ሰው ደግ ነበሩ ። ደግነታቸው ለሰው ልጅ ብቻም አልነበረም ። ለእግዚአብሔር ፍጡራን ሁሉ ደግ ነበሩ ። ለምሳሌ ፤ ለእንስሳት በጣም ይሳሱ ነበር ። በዚህ ረገድ ብራሀሚን ነበሩ ባይባልም በመጽሐፈ መክብብ ፤ «የእኔ ንስሳት ነፍስ ወዴት እንደሚሔድ ማን ያውቃል ?» የተባለውን አባ ባለ ቡዙ ሳያስቡበት የቀሩ አይመስልም ።

በፍጡራን ላይ የተፈጥሮ ጉድለት ወይም ቀውስ ሲያዩ በጥንቃቄና በትዕግሥት ይመረምሩት ነበር ። በዚህ ረገድ እንግዳ የሆነ ነገር የሚናገሩ በት ጊዜም ነበራቸው ። ለምሳሌ ፤ አንድ ቀን በአትክልቱ ቦታ ሲንሸራሸሩ ሳለ አንድ ነገር አዩ ... ሸረሪት ። በጣም ቅልጥ ፣ ከስል ጥቁር ፣ ጸጉራማና የሚያስፈራ ሸረሪት ። አሳቸው አላወቁም አንጂ እህታቸው ማድሚዜል ባፕቲስቲን ከእላቸው ሆና ታስተውላቸው ነበር ። አቡነ ይሆንን አስቱያ ሚና አስፈሪ ሸረሪት በጥሞና ተመለከቱትና «የሚያሳዝን ፍጡር ! እንዴ ዚህ ሆኖ መፈጠሩ የሱ ጥፋት አይደለም !» ሲሉ ሰማቸው ።

ይህ አባባላቸው ከደግነታቸው የመነጨ ነበር ። በእርግጥ ይህ ዓይ ነት አባባል የልጅ ፣ ወይም ያልበሰለ ሰው አባባል ሊመስል ይችላል ። ነገር ግን የአሲዚው ቅዱስ ፍራንሲስና ማርከስ አሬሊዩስም የዚህ ዓይነት አባባል ነበራቸው ።

አቡነ ሚሪዬል ለጥቃቅን ነፍሳት አንኳ ያስቡ ነበር ። ከዚህ የተነሳ አንድ ቀን እግራቸውን ወለም አሳቸው ፤ በመንገዳቸው የነበረውን ጉንዳን ጨፍልቀው እንዳይገድሉት እግራቸውን ሲያዘዙ ።

አቡነ ሚሪዬል ሌሊት በጭለማ በአትክልቱ ቦታ ብቻቸውን ሆነው በሚንሸራሸሩበት ወቅት የሰማያት ሰማያትን እርጋታ ከፊሳቸው መንፈስ ርጋታ ጋር አያነጻጸሩ በልባቸው ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ነበር ። ሰማይ በከዋክብት ደምቆ ሲያዩ የእግዚአብሔር ታላቅነት በልባቸው ውስጥ ያድራል ። ልባቸው ወደር በሌለው ደስታም ይመላል ። አቡነ ሚሪዬል ስለ እግዚአብሔር ምንነት በጥናት ሊደርሱበት መሞከራ ያደረጉበት ጊዜ የለም ። የእግዚአብሔር ምንነትና ታላቅነት የሚገነዘቡት ተፈጥሮን በማ ስተዋልና አልት የሌለው ጊዜ ማለት ዘለዓለማዊነት መሆኑን በመገንዘብ ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

«እግዚአብሔር መላው ስነ ፍጥረት ነው ፤ መላው ስነ ፍጥረትም እግዚአብሔር ነው ። እግዚአብሔር ግላዊነት ያለው ኃይል አይደለም» የሚልና «ፓንቴኢዝም» በሚል ስያሜ የታወቀ ፍልስፍና አለ ። ስለአቡነ ሚሪዩል እምነት የተሰጠው መግለጫ አቡነ ሚሪዩልን በ«ፓንቴኢዝም» የሚያምኑ አስመስሏቸው ይሆናል ። የሳቸው ፍልስፍና ግን ከልባቸው የመነጨ ብርሃን እንጂ በፓንቴኢዝም የተመሠረተ አልነበረም ።

አቡነ ሚሪዩል ነቢይ አልነበሩም ። ወደፊት የሚመጣውን ለመተንበይ መነሻ ያደረጉበት ጊዜ የለም ። የተነቀባበረ ፍልስፍና ያላቸው ፈላስፋም አልነበሩም ። የተቀነባበረ ፍልስፍና ያላቸው «ዣርኒ» በሚል ቅጽል የታወቁ ወደር የሌላቸው የአእምሮ ተመራማሪዎች ናቸው ። እነዚህ ተመራማሪዎች ስለ እግዚአብሔር ምንነት ይናገራሉ ። እነሱ የሚያቀርቡት አስተያየትም ብዙ ዓይነት ጥያቄና ክርክር ያስነሳል ። አቡነ ሚሪዩል ግን ከነዚህ ሰዎች የሚመደቡ አይደሉም ። እንደ ፓስካልና እንደስዊድንበርግ ያሉት ታላላቅ የአእምሮ ሰዎች ደፍረው የተመራመሩትን ያህል እንኳ ለመመራመር አይደፍሩም ነበር ። በእርግጥ የዚህ ዓይነቱ መመራመርና መረዳሰፍ የሞራል ጥቅም አለው ። ከሃሳባዊ ፍጹምነት ለመድረስ ባያስችልም ከዚያ ለመቅረብ የዚህ ዓይነት ምርምር ያሻል ። አቡነ ሚሪዩል የተከተሉት መንገድ ግን የዚህ ዓይነቱ መመራመር ሳይሆን አጭሩን መንገድ ነበር . . . የወንጌል መንገድ . . . የፍቅር መንገድ ።

ለፍቅር ወሰን የለውም ። ለጸሎትም እንዲሁ ። ማንኛውም ሰው ከልክ በላይ አፈቀርኩ ወይም ከልክ በላይ ጸለይኩ ለማለት አይችልም ። ከልክ በላይ ጸለይኩ የሚል ቢኖር ኖሮ ቅድስት ተሬዛና ቅዱስ ገርሮም ባሉ ነበር ። በዚህም ምክንያት እንደመናፍቃን በተቆጠሩ ነበር ። አቡነ ሚሪዩልም የሰውን ልጅ በጣም አድርገው ያፈቅሩ እንደነበረ ሁሉ በጣም አድርገው ይጸልዩም ነበር ።

ለሚሰቃዩትና ለሚጸጸቱት ሁሉ ሀዘኔታ ነበራቸው ። መላው ዓለም በደዌ የሚኖር መስሎ ይታያቸዋል ። በመላ አካባቢያቸው የስቃይ ድምጽ ይሰማሉ ። በመላ አካባቢአቸው ሕመምተኞች የሆኑ ሰዎችን ያያሉ ። በዓለም ውስጥ መከራ መኖሩ ለምን እንደሆነ ሊገባቸው ባይችልም እነዚህን መከረኞች ለመርዳት ያልተቆጠበ መከራ ያደርጋሉ ። አዛኝ ያደረጋቸውም በዙርያቸው የሚያዩት መከራና ስቃይ ነበር ።

ጳውሎስ በቆላስይ «ተፋቀሩ» የሚለው አባባል ቀኖናቸው ፣ እምነታቸው ፣ ፍልስፍናቸውም ነበር ። ከዚህ በላይ የሚሸትም አልነበራቸውም ። አንድ ሃን ፈላስፋ ነኝ ባዩ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ፤ «ዓለምን ልብ ብለው ይመለከቱ... ሁሉም እርስ በርሱ የሚናከስ መሆኑን ያስተውሉ... በንክሻው አሸናፊው ኃይለኛው ነው ። ስለዚህ እርስ በርሳችሁ



@OLDBOOKSPDF

ተፋቀሩ የሚለው መመሪያ ትርጉም የለሽ ባዶ ቃል ነው» አላቸው ። አቡነ ሚሪዬል ሊከራከሩት አልፈለጉም ። «እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ የሚለው መመርያ ትርጉም የለሽ ባዶ ቃል ከሆነ የሰው ነፍስ በዚሁ ቃል ውስጥ ተዘግቶ መኖር ይገባዋል ፤ ሉል በ'ኦይስተር' ውስጥ ተዘግቶ እን ደሚኖር ሁሉ» ሲሉ መለሱዶት ። እሳቸውም ሚታሪዚክስንና መላ ምት አስተሳስቢን ወደ ጐን ትተው ባለበት አካባቢ ተዘግተው ይኖሩ ነበር ።

ይህ የአቡነ ሚሪዬል ታሪክ የዋናው ታሪክ መግቢያ እንጂ የዋናው ታሪክ አካል አይደለም ። ሆኖም ያለዚህ መግቢያ ዋናው ታሪክ የተሟላ ሊሆን አይችልም ።



@OLDBOOKSPDF

# መጽሐፍ ሁለት

## ውድቀት

— 1 —

በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ፣ በ1815 ዓ. ም. ፒዮበር ለመጥለቅ አንድ ሰዓት ያህል ሲቀራት አንድ መንገደኛ ቪዬ ከተማ ውስጥ ታየ ። በየቢታቸው በራፍ ቆመው ይመለከቱት የነበሩት የከተማው ነዋሪዎች እንግዳ ደራሹን አልወደዱትም ። ገና ሲያዩት ቸረሩቸው ።

ሰውዬው ፣ ቁመቱ መሐከለኛ ሰውነቱ ደንዳና ሆኖ ዕድሜው ከአርባ ሰድስት እስከ አርባ ስምንት ዓመት የሚገመት ነበር ። ቆብ ደፍቷል ። ቆቡ ፊቱን በክፊል ሸፍኖታል ። ፊቱ ጸሐይና ነፋስ ስለተፈራረቁበት ጠየ ምየም ብሏል ። ደሞም በላብ ርሷል ። ጉንጩና ጉንጩን ቢሳጨውም አገ ጩ ላይ ረጅም ጢም ይታያል ። የሰበሰው ቢጫ ሽሚዝ ከሻካራ ጨርቅ የተሰፋ ሆኖ አንገትጌው በመርፌ ቁልፍ በደጉ ተይዟል ። ጸጉራማው ደረቱ በክፊል ይታያል ። ሰዓ ክራቫት አስሯል ። ሰሚያሟ ሱሪም ታጥቧል ። አሮጌ ነው ሱሪው ፤ አንድ ጉልበቱ ነጣ ያለ ሲላው ጉልበቱ የተቀደደ ። ኮቱም አሮጌና አመድ የመሰለ ሆኖ ተቧጫጭቆ ይታያል ። አንደኛው ክርኑ ላይ ጣፈት አለበት ፤ በጠንካራ እረንጓዴ ክር የተደረቱ ። በጀርባው ሳያ የጉዞ ከረጢት ተሸክሟል . . . ከሸራ የተበጀ ከረጢት . . . አዲስ . . . ባለቀቢዮ . . . በዕቃ ታጭቂዋል ከረጢቱ ። ቁቢቶው በጥብቅ ታስሯል . . . በዘለበት ። ጀት ያለው ዘንግ ይሟል ፤ ሰውዬው ፣ መንገደኛው ። ባለከምሱር ጫማ አድርጓል ። የግር ዙራብ ግን የለውም ።

ላቦቱ ፣ ሙቀቱ ፣ የእግር ጉሠው ፣ አቧራው . . . ይህ ሁሉ ተዳምሮ ሰውዬውን ናዱር ሰው አስመስሎታል ። ባጭር ተቆርጦት የነበረ ጸጉሩ እንደገና ማደግ ስለጀመረ ብሩሽ መስሏል ።

ማንም ሊያውቀውም ሰውዬውን ። ተላላፊ መንገደኛ ነው ። ለመሆኑ ከወዴት ይሆን የመጣው ? ከበሰተደብብ ፤ ምናልባትም ከወደቡ አካባቢ የመጣ ሳይሆን አይቀርም ። ምክንያቱም ወደ ዴ ከተማ የገባው ከሰባት



@OLDBOOKSPDF

ወራት በፊት ናፖሌዎን ቦናፓርት ከካን ወደ ፓሪስ በሚጓዝበት ጊዜ ባለ ፈበት መንገድ ነበር ። ሰውዬው ቀኑን ሙሉ በእግር ሲኳትን የዋለ ሳይሆን አይቀርም ። በጣም የደከመው ይመስላል ። ከከተማው በታች ካለው ጥንታዊው የገበያ ቦታ ሲደርስ በጋሲንዲ ጐዳና ፤ ከዛፍ ሥር አረፍ ማለ ቱንና ከዚያም አለፍ ብሎ የቧንቧ ውሃ ከሚፍለቀለቅበት ሥፍራ ሲደርስ ውሃ መጠጣቱን በዚያ አካባቢ የነበሩ ሴቶች አይተዋል ። ሰውዬው በጣም ተጠምቶ የነበረ ይመስላል ። ምክንያቱም ሁለት መቶ ያህል ርምጃ ከተ ጓዘ በኋላ እንደገና ከአንድ ከሚፍለቀለቅ የቧምቧ ውሃ ደርሶ ውሃ ሲጠጣ ከኋላው የተከተሉት ልጆች አይተውታል ።

ከፑዋሽቪ ጐዳና ሲደርስ ወዴ ግራ ተጠምዞ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ አመራ ። ከማዘጋጃ ቤቱ ደርሶ አስራ አምስት ደቂቃ ያህል ከቆየ በኋላ ተመልሶ ወጣ ። ከበሩ አጠገብ በድንጋይ መቀመጫ ላይ የተቀመጠ አንድ ፖሊስ ነበረ ። መንገደኛው ቆሙን አውልቆ ለፖሊሱ ዝቅ ብሎ እጅ ነሳው ። ፖሊሱ ለሰላምታው አጸፋ በመመለስ ፈንታ አተኩሮ አየው ። ለትንሽ ጊዜም በሳያ ኑ ሲከተሉው ቆየና ተነስቶ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ሕንጻ ውስጥ ገባ ።

በዚያን ጊዜ በደጌ ከተማ ውስጥ በጣም የታወቀ የመንገደኞች ማረፊያ ሆቴል ነበር ። ባለቤቱ ጉርዝን ላባር ይባላል ። ጉርዝን ላባር የተከበረ ሰው ነበር ፤ በዘመዱ ምክንያት ። ዘመዱ ከደጌ ከተማ መቶ ሀያ ኪሎሜትር ያህል ርቆ ከሚገኘው ከግረኖብል ከተማ ዝነኛ የሆነ የመንገደኞች ማረፊያ ሆቴል አለው ። አንድ ሰሞን ናፖሌዎን ቦናፓርት በግረኖብል ከተማ በተ ገኘበት ወቅት የከተማው ከንቲባ ማረፊያ አዘጋጅቶ ከዚያ እንዲያድር ቢጠይቀው ናፖሌዎን ቦናፓርት ስለዝግጅቱ አመስግኖት «ከአንድ ክማ ውቀው ጐበዝ ቤት አድራለሁ» ብሎት በማረፊያው ሆቴል ቤት ውስጥ በማደሩ ሆቴሉና ባለቤቱ ዝና አተረፉበት ። ጉርዝን ላባር የዚህ ሰውዬ የቅርብ ዘመድ በመሆኑ እሱና ሆቴሉም ዝነኛ ለመሆን በቁ ።

መንገደኛው ወደዚህ ፤ ወደ ጉርዝን ላባር ሆቴል አመራ ። የሆቴሉ ወጥ ቤት ከመንገድ ትይዩ ኖሮ መንገደኛው በቀጥታ መደዚያ ገባ ። በወጥ ቤቱ ውስጥ ያሉት ምድጃዎች ሁሉ እሳት ይነድባቸዋል ። በእሳት ማንደ ጃው ቦታም እሳት ያንቀለቀላል ። የሆቴሉ ዋና ወጥ ሠሪ ባለቤቱ ጉርዝን ላባር ራሱ ስለሆነ አንዴ ድስት ከተጣደበት መደሌላው እየተዘዋወረ በመ ብሰል ላይ ያለውን አስጐምጂ ምግብ ይመለከታል ። በርከት ያሉ የሠረገላ ነጂዎች በሆቴሉ ውስጥ አርፈዋል ። የሚዘጋጀው ምግብ ለነሱ ነበር ። ነጂ ዎቹ ቀጥሎ ባለው ክፍል ተቀምጠው ሙክ ብለው ሲያወሩና ሲስቁ ይሰ ማል ። ነጂዎች ተደሳቾች መሆናቸውን የሚያውቅ የለም ። መሳቅና መጫ ወት ይወዳሉ ።

ከሚንቀለቀለው እሳት ላይ የዱር አውሬ ሥጋ ፣ የቆቅና የሌሎችም የዱር አእዋፍ ሥጋ ፤ በምድጃው ከሚነደውም እሳት ላይ የተሰያዩ የእሳ ማይነቶች ሲንጨረጨሩ ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

መንደኛውም ሲገባ በሩን ቢጠጥ ስላደረገው ባለቤቱ ግርክን ላባር ይሽንኑ ሰምቶ ዓይኑን ግን ከምድሽው ሳይነቅል ፣ «ምን ይፈልጋሉ ጌታዬ ?» ሲል ጠየቀው ።

«ምግብና መኝታ ይገኝ ይሆን ?»

«ሞልቷል !» ብሎ ዓይኑን አቅንቶ ቢመለከት የመንገደኛው አለባበስና ጠቅላላ አቋሙ ጥርጣሬ ስላሳደረበት ፣ «መክፈሉን ከቻለህ ማለቴ . . .» አለው ።

መንገደኛው ከኪሱ ትልቅ የቆዳ ቦርሳ አውጥቶ አሳየውና «በቂ ግን ዘብ አለኝ» አለው ።

«እንግዲያውስ ቤት ለእንግዳ !»

መንገደኛው የገንዘብ ቦርሳውን መልሶ ኪሱ ውስጥ ወሽቀውና ሸክሙን አውርዶ ከበሩ አጠገብ አስቀመጠው ። ዘንጉን በእጁ እንደያዘም ከእሳቱ አጠገብ አጭር ወንበር ላይ አረፍ አለ ። ይኼ ከተማ በደጋው አገር የሚገኝ ስለሆነ ማታ ማታ ይበርዳል ።

ግርክን ላባር ከወዲህ ወዲያ ከወዲያ ወዲህ እያለ ምግብ በሚያዘጋጅ ጊዜ መንገደኛውን ከእሁን አሁን ያስተውሰው ነበር ።

«ራት በቶሎ ይደርስ ይሆን ?» ሲል ጠየቀው መንገደኛው ።

«አዎን . . . አሁን ይደርሳል» አለው ግርክን ላባር ።

መንገደኛው ጀርባውን ሰጥቶት አሳት ሲሞቅ ሳለ ግርክን ላባር ከኪሱ እርሳስ አውጥቶ ፣ ከመስኮቱ አጠገብ ከነበረ ጋዜጣም ቁራጭ ወረቀት ቀድዶ አውጥቶለት ቀለም ካልወደቀበት ሥፍራ አንድ ሀሳቅ መስመር የሚሆን ጽሑፍ አሰፈረበትና አጣጠፈው ። ከዚያም በኋላ የሚላላከውን ልጅ ጠርቶ ፣ በጆሮው አንዳች መልእክት ሹክ ብሎት ፣ ቁራጩንም ወረቀት ሰጠውና ልጁ መልእክቱን ሰሚድረስ ከከፍሉ ወጥቶ ወደማዘጋጃ ቤቱ አቅጣጫ ይሮጥ ጀመረ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን መንገደኛው አንዳችም ነገር አላየም ። ልጁ ከሔደም በኋላ ዓይኑን ወደ ግርክን ላባር አዙሮ «ራት በቶሎ ይደርስ ይሆን ?» ሲል ጠየቀው እንደገና ።

«አዎን . . . አሁን ይደርሳል» ሲል መለሰለት ግርክን ላባር አንደበቱ ፊቱ

የታላከው ልጅ መልእክቱን አደርሶ ፣ ይዘት የሌደውን ቁራጭ ወረቀት መልሶ አምጥቶ ለጌታው ሰጠው ። ግርክን ላባር በጥድፊያ ዘርግቶ



@OLDBOOKSPDF

ተመለከተው ። እንደማሰበም ብሎ ራሱን ነቀነቀና ወደ መንገደኛው ሬመድ ብሎ ሔዶ ፤ «እዚህ ልታርፍ አትችልም ጌታዬ» አለው ።

መንገደኛው ደንገጥ ብሎ እንደመነሳት ቃጣው ። «እዚህ ልታድር አትችልም . . . ? ገንዘብ አይከፍሰኝም ብለህ ተጠራጥረህ ከሆነ ሂሳቡን በቅድሚያ ልክፍልህ ፈቃደኛ ነኝ ። በቂ ገንዘብ አለኝ ብዬህ ነበር ።»

«ችግሩ እሱ አይደለም ።»
«ታዲያ . . . ?»

«አንተ ገንዘብ አለህ ። እኔ ግን ከፍል የለኝም ።»

«እንደሱ ከሆነ በረት ውስጥ ቢሆንም አላድረኝ . . . ግድ የለም ።»

«አይቻልም ጌታዬ ።»

«ለምን አይቻልም ?»

«በረቱም ውስጥ ቦታ የለም ። በዚያ የሚያድሩ ፈረሶች በርከት ያሉ ናቸው ።»

«እሺ . . . በረቱም የሚይዝ ከሆነ ቆጡ ላይ አላድረኝ ። ማር ጉዝ ጓዝ ላይ ብተኛ ፈቃደኛ ነኝ» አለና ፤ «ለማንኛውም ከራት በኋላ በይበልጥ ብንነጋገርበት አይሻልም ?» አለው ።

«ራት ላቀርብልህ አይቻለኝም ጌታዬ ።»

መንገደኛው ይሠንን ሲሰማ በስጨት ብሎ ተነስቶ ቆመ ። «በጣም ርበኛል» አለው ቀጠል አድርጎ ፤ «ከማለዳ ጀምሬ በእግር ስጓዝ ነው የዋልከት ። አምሳ ስድስት ኪሎ ሜትር ያህል ነው የተጓዝከት ። ሂሳቡን ከፍ የሠ እህል ውሃ ቢታቀምሰኝ . . . »

«ምንም የሚቀምስህ የለኝም ።»

መንገደኛው የመገረም ላት ላቀና ዓይኑን ወደሚንጨረጨረው ሥጋና አሳ መለሰ ፤ «ይህ ሁሉ እያለ ምንም የሚቀምስህ የለኝም ትለኛለህ ?» አለው ።

«ይሽከ ስለሎ'ት ሰምኙ የሚዘጋጅ ነው ።»

«ሴሎ'ት ሰምኙ . . . ?»

«እምን . . . ለሠረገላ ነጂዎች ።»

«ለንት ጥቁው ለመሆኑ ?»

«አለሪ ሁለት ።»



@OLDBOOKSPDF

«ይህ ሁሉ የሚዘጋጀው እራት ለሀያ ሰው ያንሳል ታዲያ ?»

«ሁሉም ለነሱ ነው ብዬሃለሁ ። ቀድመው ከፍለውበታል ።»

መንገደኛው መልስ ተቀመጠና ዝቅ ባለ ድምጽ ፤ «ሆቴል ቤት ነው የመጣሁት . . . ርቦኛል . . . እና እዚሁ እቆያለሁ» አለ ።

ባለቤቱም ጐንበስ ብሎ ፥ ወደሰውዬው ጆሮም ጠጋ ብሎ ፤ «ቤትሄድ ይሻልሃል» አለው ።

ሰውዬው ለመናገር ሲቃጣ ሳለ ባለቤቱ «ቆይ . . . ቆይ . . . ምንም የምትነግረኝ ነገር የለም ። ስምህ ማን እንደሆነ ልንገርህ . . . ? ግን ቫልግ ትባላለህ ። እና ምን ዓይነት ሰው እንደሆንህ ልነግርህ ትፈልጋለህ ? ግና ስትገባ ነው የተጠራጠርኩህ ። ስማረጋገጥ ብዬ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ሰው ልኬ ነበር ። የተሰጠኝ መልስ ይሸውልህ . . . » ብሎ ፤ «ለመሆኑ ማንበብ ትችላለህ ?» ሲል ጠየቀው ። ይህንንም እያለ ወረቀቱን ዘርግቶ አሳየው ። መንገደኛው ወረቀቱን ተመለከተው ። ባለቤቱም ለአጭር ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና «በተለምዶ ማንንም ሰው ለማስቀየም ጥላት የለኝም ። እና ከዚህ ብትሄድልኝ . . . » አሰው ።

መንገደኛው ጐንበስ ብሎ የጉሮ ከረጢቱን አንስቶ ፥ ከሆቴል ቤቱ ወጥቶ ፤ አንገቱን ደፍቶ በዋናው ጐዳና ይንገዋለል ጀመር ። ውርደት ተሰምቶት አንድ ጊዜ እንኳ ዞር ብሎ ሳይመለከት መንገዱን ቀጠለ ። ግርክን ሳባርና እንግዶቹ ደጅ ወጥተው ይመለከቱት ጀመር ። በመንገዱ የሚተላለፉ ሰዎችም እየሳቁና እየተጫወቱ ጣታቸውን ወደሱ ቀስረው ሲያመለክቱ ነበሩ ። በጠቅላላው የከተማው ሰው ሁሉ ስለሱ ነበር የሚያወራው ።

እሱ ግን አንድ ጊዜ እንኳ ዞር ብሎ ሳይመለከት ወደፊት ገሰገሰ ። የተዋረዱ ስዎች መለስ ብለው ኢይመለከቱም ። መለስ ብለው ቢመለከቱ የባሰ ውርደት እንደሚያጋጥማቸው ያውቃሉና ።

ርቆ ከሔደ በኋላ አነስተኛ የሆነ የመንገደኞች ማረፊያ ሆቴል ባገኝ ብሎ ግራ ቀኙን ቃኘ ። ከመንገዱ ማለቂያም ሲታረብ የመብራት ብርሃን ታየውና ወደዚያው አመራ ።

ብርሃን ያየበት ሥፍራ መጠጥ ቤት ነበር ። መንገደኛው ከዚያ ሲደርስ ቆም ብሎ በመስኮት ወደ ውስጥ ተመለከተ ። የበራው መብራት ጠረጴዛ ላይ ነው ። ከእሳት ማንደጃው ቦታ እሳት ይነድዳል ። አንዳንድ ሰዎች መጠጥ ይጐነጫሉ ። የቤቱ ባለቤት ከእሳቱ አጠገብ ተቀምጧል ። እሳቱም ላይ የሚበስል ምግብ አለ ።

መጠጥ ቤቱ ሆቴል ቤት ቢጤም ነበር። ሁለት መግቢያ በሮች አሉት። አንደኛው ከመንገዱ ትይዩ ፤ ሁለተኛው ከአንድ አነስተኛ ሜዳ ትይዩ ሆኖ



@OLDBOOKSPDF

ሚዳው በእህባ ተመልሷል ። መንገደኛው በዋናው በር ሊመግባት አል ደፈረም ። ወደ ሚዳው ገባ ብሉ ቆመ ። ከዚያም በኋላ ሲፈራ ሲቸር የኋ ላውን በር መንጠቆ እነሳውና በሩን ከፈት ሲያደርገው ባለቤቱ ዋግ ነው ነው ሲል ተጣራ ።

«ምግብና መኝታ ይገኝ ይሆን ?» አለው መንገደኛው ።

«እይጠፉም» ሲል መለሰለት ባለቤቱ ።

መንገደኛው ወደ ውስጥ ገባ ። በዚያ የነበሩ ጠዉምት ዓይናቸውን እትንቶው ተመለከቱት ። የፊቱ እንደኛው ጉን በመብራቱ ብርሃን ፣ ሁለተኛው ጉን በእሳቱ ነበልባል በርቶው ይታዩ ነበር ።

«ምግቡ እየተዘጋጀ ነው ። እሳቱም ይሽውለህ ወንድም ጠጋ ብለህ ሙቅ» አለው ባለቤቱ ።

መንገደኛው የጉዞ ከረጢቱን መሬት ሳይ አውርዶ ወደ እሳቱ ተጠ ግቶ ቁሞ አለ ፣ የደከሙ እግሮቹን ወደ እሳቱ ዘርግቶ ። ፊቱ የተዝናና ቢመ ስልም እንዳች በቅቀን ይነበብበት ነበር ። ከትንድቡ ሥር ያሉት ዓይናቹም በቁጥጥጠ ሥር ያለ እሳት ይመስሉ ነበር ። የምግቡ አበሳሰልና ከድስቱ እምልጦ የሚወጣው እንፋሎት ሽታ ረሃቡን አባባሱበት ።

ከጠዉምቹ መሐከል መንገደኛውን ተደም ብሎ ያየው እንድ ሰውዬ ነበር . . . የእሳ ነጋዴ ። እሳ ነጋዴው ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ፈረሱን ለማሳደር ከጎኮን ላባር ሆቴል ሔዶ ነበር ። መንገደኛውን ከዚያ አደቶ ታል ። እንደአጋጣሚ ሆኖም ያንኑ ቀን ጠዋት በመንገድ ተገናኝተው ነበር ፣ በብራ ጸሰና በአስኩብሎ መሐከል ። መንገደኛው ደክሞት ስለነበረ የእሳ ነጋዴው በፈረሱ እንዲያፈናጥጠው ለምኖት ነበር ። እሳ ነጋዴው ግን መልሰ እንኳ ሳይሰጠው ቀርቶ ነበር ። እንዲያውም ፈረሱን ኩርኩር እድርጎ ርቆት ሔዶ ነበር ። አሁንም ከዚህ መጠጥ ቤት ሲያየው የመጠጥ ቤቱን ባለቤት በጥቅሻ ጠራው ። ባለቤቱ ወዲ እሱ ሔዶ ገቹ ባለ ድምጽ ታል ይሰዋወጡ ጀመር ። ይህ ሲሆን መንገደኛው ከሃሳብ ባሕር ውስጥ ገብቶ ነበር ።

የመጠጥ ቤቱ ባለቤትና የእሳ ነጋዴው የሚነጋገሩትን ተጎጋግረው ሲጨርሱ ባለቤቱ ወደ እሳቱ ቦታ ተመልሶ ፣ እጁን በመንገደኛው ትከሻ ላይ አሳርፎ ፣

«ወንድም . . . ከዚህ መውጣት አለብህ» አለው ።

«ኧ . . . ፣ እንተም ግን እንደሆንከ ታውቃለህ ?» አለው ።

«አዎን . . . ግን እንደሆንክ አውቃለው ።



@OLDBOOKSPDF

«ከዚያኛው ሆቴል አስወጡኝ ፡ ከዚህኛውም . . . ››

‹‹ከዚህኛውም መውጣት አለብህ ፡››

«እና የት ልሒድ ?»

«ወደፈለግህበት . . . ከዚህ ግን መውጣት አለብህ ፡»

መንገደኛው የጉዞ ከረጢቱን አንስቶ ፣ ዘንጉንም ይዞ ወጥቶ ሔደ ። ከጎርከን ሳባር ሆቴል ወደዚህኛው ሲመጣ ከኋላው የተከተሉት ሕጻናት ልጆች ነበሩ ። ከመጠጥ ቤቱ ሲገባ እነሱ እውጭ ሊድፍጠው ሲጠብቁት ነበሩ ። መውጣቱን ሲያዩ ድንጋይ ወረወሩበት ። ድሮውንም ቢሆን ሆዱ ቆስሎ ስለነበረ በር ብሎ ዱላውን እየወዘወዘ አስፈራራቸው ። ሕጻናቱም እንደ ወፍ መንጋ ብትን አሉ ፤ ባለው አቅጣጫ ሁሉ ።

በከተማው ወህኒ ቤት በኩል አሰፈ መንገደኛው ። በወህኒ ቤቱ በር ላይ ከሰንሰለት ጋር የተያያዘ ደወል አለ ። መንገደኛው ሰንሰለቱን ሳብ ሲያደርገው ደወሉ ‹‹ደወለ›› ወዲያውኑ በሩ ተከፈተ ። የእስር ቤቱ ቁልፍ ያዥ ብት ሲል ፤ «ከዚህ ልታሳድረኝ ትችላለህ ?» ሲል ጠየቀው መንገደኛው ።

«ይኸኮ ወህኒ ቤት እንጂ ሆቴል ቤት አይደለም ። እዚህ ለማደር ከፈለግህ በቅድሚያ በአንዳች ጥፋት ተከሰስህ እስራት እንዲፈረድብህ ያሻልህ ብለህ በሩን እጅግጫው ላይ መልሶ ዘጋበት ።

መንገዱን ተጠለና በርከት ያሉ አትክልቶች ካሉበት ሥፍራ ደረሰ ። እንጻዝዶቹ በጥሻ ቢጤ ተከበበዋል ። በዚህ ምክንያት ለዓይን ደስ ይሳሉ ። በእነዚህ አትክልቶች መሐከል ባለአንድ ፎቅ ቤት አለ ። በመስኮቱ በኩል ብርሃን ይታያል ። መንገደኛው ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ ወደ ውስጥ ተመለከተ ። ክፍሉ ለፋ ያለና ግድግዳውም ኖራ የተቀባ ነው ። የእዋቂ አልጋ ፣ የሕጻን አልጋ ፣ ጥቂት ወንበሮችም አሉበት ። በግድግዳው ላይ ባለሁለት አፈሙዝ ጠበንጃ ተንጠልጥሎበታል ። በክፍሉ መሐከል ጠረጴዛ አሰ ፤ ነጭና ሸካራ ጨርቅ የለበሰ ። በጠረጴዛው ላይ ከመጻብ የተሰራና የበራ ፋኖስ ይታያል ። ወይን ጠጅ የተሞላ ዝምቦ በፋኖሱ ብርሃን ይጥበረበራል ። የሸርባ ማቅረቢያውም እንዲሁ ። ትኩስ ሸርባ ስላለበት ከሳቡ ላይ እንፋሎት ቢነሳ ይታያል ። ዕድሜው አርባ ዓመት የሚገመት ጐልማሳ ከጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጦ ሕጻን ልጁን በጉልበቱ ኢያስዘለለ ያጫውተዋል ። ከአጠገቡም ወጣት ባለቤቱ ሕጻን ልጇን ታቅፋ ታጫውተዋለች ። አባት ዱውና ልጁ ይሰቃሉ ። ሚስቲቱ ፈገግ ትላለች ።

መንገደኛው ይህንን መልካም ቤተሰብ እያየ ዝም ብሎ ቆመ ። በልቡ ምን እንደሚሰማው እሱ እንጂ ሌላ የሚያውቅ ሰው አልነበረም ። ምናልባት ያሳድጉሻል በሚል ተስፋ የመስኮቱን መስታወት ቀስ ብሎ እንኳኳው ። አልሰሙትም ። እንደገና ተስ ብሎ እንኳኳው ።



@OLDBOOKSPDF

«የሚቆረቁር ሰው አለ መሰለኝ» አለች ወጣቷ የቤት እመቤት ።

«አይመስለኝም» አሳች ባሏ ።

መንገደኛው ለምሰተኛ ጊዜ መስታወቱን ቀስ ብሎ አንኳኳው ። ባል ዬው ከነበረበት ተነስቶ ፣ ፋኖሱን ይዞ ወደ በሩ ሔድ አለና ከፈተው ።

ረጅም ሰው ነው የቤቱ ባለቤት ፤ በከፊል አርሶ አዶር በከፊል የእጅ ሙያተኛ የሆነ ። ትልቅ የቆዳ ሽርጥ ታጥቋል ፤ ከላይ እስከ ግራ ትከሻው የሚደርስ ። መዶሻ ፣ ቀይ መሐረብ ፣ የባሩድ መያዣ ቀንድ ፣ እና ሌሎችም ቁሳቁሶች የሽርጡን ወገብጌ አሳብጠውት ይታያል ። ጭንቅላቱን ወደ ኋላ መልሶታል ። የሸሚዙ አንገትጌ ክፍት ነው ። ሴጣ አንገቱ ነጭ ሆኖ ከበሬ ጫንቃ ጋር ይመሳሰላል ። ቅንድቡ ችምችም ብሎ በቅሏል ። ጥቁር ሪዙም እንዲሁ ። ዓይኖቹ ትንሽልቅ ናቸው ። የፊቱ ታችኛው አጋማሽ ከዱር አውሬ አፍና አፍንጫ ጋር ይመሳሰላል ። በጣዛ ቤቱ ውስጥ ስለሆነ መሬቱን ቱደላድሎ ረግጦ ቆሟል ።

«ይቅርታ ያርጉልኝና ጌታዬ . . . » ሲል ጀመረ መንገደኛው ፤ «አንድ ሳህን ሾርባና ከዚያ በኦትክልቱ ቦታ ካለው መጠለያ ማደሪያ ሊሰጡኝ ይችላሉ ? ገንዘብ ከፍዬ ያህንን ሊያደርጉልኝ ይፈቅዳሉ ?»

«አንተ ማነህ ?» ሲል ጠየቀው የቤቱ አባወራ ።

«ከጥቂ—ሚሶ የመጣሁ ሰው ነኝ ። 56 ኪሎሜትር ያህል ተጉዠ ዓው የመጣሁት ። ገንዘብ ከፍዬ ሾርባና መኝታ ሊሰጡኝ ይችላሉ ?»

«ጨዋ ሰው ከሆንክና ገንዘብ ከከፈልክ ይህንን ላደርግልህ እችላለሁ ። ብቻ . . . ወደ ሆቴል ቤት ሰምን አልሔድክም ?»

«ሔጄ ነበር ። ቦታ የለም አሉኝ ።»

«የሚይመስል ነው . . . ! ዘራፊ የገበያ ቀን አይደለም ። ብዙ ሰው የለም» አለውና «ለመሆኑ ማከን ሳባር ዘንድ ሞክረሃል ?» ሲል ጠየቀው ።

«አዎን ።»

«እና ?»

«ለምን እንደሆነ አላውቅም ። ግን ሊቀበለኝ አልፈለገም» አለው እፍረት እየተሰማው ።

«ማነው ዘንድስ ሞክረሃል . . . ! ወዲያ . . . በሻፎ ጐዳና ያለው ሆቴል ?»



@OLDBOOKSPDF

«አሱም ሊቀበለኝ አልፈለገም» አሰው ይበልጥ እጥረት እየተሰማው።

ሰውዬው ተጠራጠረው ። ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ አስተውሎ አየውና ፤ «ሰውዬው አንተ ትሆ—ን !?» ብሎት ወደኋላው አፈገፈገ ። ከዚያም በኋላ ፋኖሱን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ጠመንጃውን ከግድግዳው አውርዶ ያዘ ።

ሚስቱ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ፡ ልጆቿንም ይዛ ከባሏ በስተ ጀርባ ቆመች ። ፍርሃት ፍርሃት አላት። ጠቷን አንኳ በልብሷ አልሸፈነችውም ። « ዱር አዳሪ መሆን አለበት ! » አለች ዝቅ ባለ ድምጽ ።

ባልዬው እባብ እንዳየ ሁሉ መንገደኛውን ደጋግሞ ተመለከተውና ወደ በሩ ሐድ ብሎ «ከዚህ ወጊድ !» አለው ።

«ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ አንድ ብርጭቆ ውሃ እንኳ ብታጠጡኝ . . . »

«ይልቁንስ ይህንን ጥይት እንዳሳጠግህ ፤ ወጊድ ብዬሃለሁ» ብሎት በሩን ዘግቶ ቀረቀረው ። ወደ መስኩቱም ሐዩ የብረት መጋረጃውን አውርዶ እንዳይከፈት አድርጎ ዘጋው ።

ምሽቱ እየገፋ ሐዲ ። ቀዝቃዛ ነፋስ ይነፍሳል ፤ ከወደ አልፕስ አቅጣጫ የሚመጣ ። መንገደኛው ግፍት ሐዲ ከአንድ ሥፍራ ሲደርስ ጎጆ የሚመስል ነገር ታየው ፤ እየጨለመ በሚሐደው የምሽት ብርሃን ። ጎጆው በአትክልት ቦታ ውስጥ ነው . . . በአጥር የተከበበ አትክልት ። መንገደኛው አጥሩን ዘሎ ገብቶ ወደ ጎጆው አመራ ። አውራ ጎዳና የሚሠሩ የሶን ሙያተኞች የሚያርፉበት ዓይነት ጎጆ ነበር . . . መግቢያ በሩ በጣም ጠባብ ።« የዚህ ዓይነት ጎጆ ቀን ቀን ለማረፊያ ያገለግላል እንጂ ሰው አያ ድርበትም» ሲል አሰበ መንገደኛው ፤ «እዚህ ባድር ሌላ ባይሆን ከብርድ እድናለሁ» ብሎ በሆዱ ተኝቶ እየተሳበ ከጎጆው ውስጥ ገባ ። ወለሉ በእርግጥም ይሞቃል ። ግር የተገዘገዘበት አልጋም አለ ። መንገደኛው በጣም ደክሞት ስለነበረ አልጋው ላይ ጋደም አለ ። ይሁን እንጂ በጀርባው የተሸከመው የጥይ ከረጢት አሳመሸ ስላለውና በያወርደውም ትራስ ሊሆንለት እንደሚችል በመገንዘብ ዘለበቱን ይፈታ ጀመር ። ልክ በዚህ ቅጽበት የቁጣ ድምጽ ሰማ ። ዓይኑን አቅንቶ ቢመለከት ከበሩ አጠገብ ትልቅ የውሻ ጭንቅላት ታየው ።

ሰካስ ጎጆው የውሻው ማደርያ ፍሯል !

መንገደኛው ጉልበተኛ በመሆኑ ውሻውን ለመቋቋም የሚያቅተው አልነበረም ። ዘንጉን በአንድ እጁ አመቻችቶ ይዞ ፡ የጥይ ከረጢቱን እንደ ጋሻ መክቶ ከውሻው ማደርያ ጎጆ እንደበፊቱ እየተሳበ ወጣ ። ቢጮቶዎቹ ግን በይበልጥ ሳይኮዳደዱ አልቀሩም ።



@OLDBOOKSPDF

ውሻው ከኋላው እንዳይቦጭቀው በመፍራት እስከአጥሩ ጥግ ድረስ የኋለኛ ሲሔድ ቆየና በመጨረሻም አጥሩን ዘሎ ወዲ መንገድ ዳር ወጣ። እንደገና ብቅኝነት ተሰማው ። መጠጊያ የለውም ። መጠለያ የለውም ። በውሻው ጎጆ ውስጥ በዚያ ሣር በተጐዘጐዘበት አልጋ ላይ ለማደር እንኳ ሳይችል ቀረ ። በመንገዱ ደንጋይ እየና ከዚያ አረፍ ብሎ ፤ ቁከውሻ እንኳ ልነስ ነው» ሲል አሰበ ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደገና ተነስቶ መንገዱን ቀጠለ ። መጠለያ የሚሆን ዛፍ ወይም የነፋስ ወጥመድ አገኛለሁ በሚል ተሰፋ ከከተማው ወጥቶ ሔደ ። ርጭ ካለ ሜዳ ሲደርስ ራሱን አቅንቶ ዙሪያውን ቃኘ ። ከፊት ለፊቱ ኮረብታ አለ ። በኮረብታው ላይ የነበረው አሀል ታጭዶ ስለነገ ኮረብታው የታሳጨ የሰው ሞንቅላት ይመስላል ።

ለማዩ ጠቁሯል ። ከባድ ዳመና አለ ። ዳመናው በኮረብታው ላይ እንዘፍ ያለ ከመምሰሉም በላይ በእየአቅጣጫው በመሠራጨት ላይ ነበር ። ጨረቃ ለመወጣት ተቃርባለች ። ይሁን እንጂ የምሽት ጨረር ዳመናውን በሳስቶ ነጭ ቅስት የመሰለ ቅርጽ ሠርቶ ይታያል ።

በሜዳውም ላይ ሆነ በኮረብታው ላይ ምንም አይታይም ፤ ከአንድ የቆረቆዘ ዛፍ በስተቀር ። ቆርቋዛው ዛፍ መንገደኛው ከቆመበት ሥፍራ ትንሽ ራቅ ብሎ ይታያል ። ይወዘወዛል ።

የሰማዩ ጥቁር ዳመና ፣ ኮረብታው ፣ ሜዳው ፣ ጐዶሎው ዛፍ ፣ . . እነ ዚህ ሁሉ ውስጣዊ ሜንና ፈጠራበት ። ከዚያ ርጭ ካለ ቦታ መምጣቱ ስህ ተት መሆኑን ተረዳ ።

. . ፊቱን ወደመጣበት አቅጣጫ አዙሮ ይራመድ ጀመር ። ከከተማው ግምብ አጥር ሲደርስ በርቹ ተዘግቶው አገኛቸው ። በኃይማኖት ጦርነት ዘመን ከጠላት ሰመከላከል ታስቦ ነበር ግምቡ የተገነባው ። ተደም ብሎ አራት ማዕዘን ያላቸው ረጅጅም አምዶችም አልፎ አልፎ ከግምቡ ጉን ነበሩ ። በ1815 ዓ. ም. ግን አምዶቹ ፈርሰው ነበር ። መንገደኛውም ግምቡ ከተደረመሰበት በኩል ሾልኮ ወደ ከተማው ውስጥ ገባ ።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ሲሆን መንገደኛው እያላበረ ሔዶ ከአ ንድ መሥሪያ ቤት ሕንጻ ደረሰ ። እሱን አልፎ ከአጠገቡ ካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ደረሰ ። እሱንም አልፎ ካቴድራሉ ካለበት አደባባይ ሲደ ርስ ወዲ ካቴድራሉ እያየ ቡጢውን ሰንዝሮ ይወዘውዘው ጀመር ፤ ካቴ ድራሉ በደል እንዳደረሰበት ሁሉ ።

ከዚው አደባባይ ጥግ አንድ ማተሚያ ቤት አለ ። ናፖሊዎን በናፓርት በኤልባ ደሴት ሆኖ ያወጣቸው አዋጆች ለመጀመሪያ ጊዜ የታተሙት ከዚያ ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

ከዚህ ግቶሚያ ቤት ደጅ ላይ ከድንጋይ የተሠራ አግዳሚ መቀመጫ አለ ። መንገደኛው በጣም ደክሞትና ተስፋም ቆርጦ ስለነበረ በድንጋይ መቀመጫው ላይ ጋደም አለ ።

ወዲያውኑ በእድሜ የገፋች አንዲት እመቤት ከቤቱ ከርስቲያኑ ስትወጣ መንገደኛውን አየችና ወደሱ መጥታ «ከዚህ ምን ትሠራለህ ሰውዬ ነው ስትል ጠየቀችው ።

«እንደምታይኝ ተኝቻለሁ» አላት ቆጣ ብሎ ።

«ድንጋይ መቀመጫ ላይ ነህ

«አዎን» ተላምጄዋለሁ። ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት እንጨት ላይ ነበር የማድረው ። ዛሬ ደሞ ድንጋይ ላይ ።»

«ወታደር ኖረሃል ?»

«አዎን ወታደር ነበርኩ ።»

«ለምንድነው ወደ ሆቴል የማትሔደው ነህ

«ገንዘብ የለኝም» አላት ።

«ያሳዝናል . . . ! እንዳልረዳህ በቦርሳዬ ውስጥ ከአራት ሱ በስተቀር ምንም አልያዝኩም ።»

«አሱው ይበቃኛል ።»

— እመቤቷ አራቱን ሱ አውጥታ ሰጠችውና «በዚህ ቤስታቡስቲ መኝታ የሚያከራይህ የምታገኝ አይመስለኝም . . . ብቻ . . . መኝታ ለማግኘት ሙከራ አድርገሃል ?

«ያልሞከርኩት ቦታ የለም እመቤቴ ።»

«እና ነህ

«በሐዲኩበት ሁሉ አባረሩኝ ። የሚቀበለኝ አጣሁ ።»

እመቤቷ ወደ አበት መኖሪያ ቤት እትጣጫ ተመለከተችና «ያልሞከርኩት ቦታ የለም ነው ያልከው ነህ ስትል ጠየቀችው ።

«አዎን ። ያላንኳኳሁት በር የለም ።»

@OLDBOOKSPDF

ያንን «ሞክረሽዋል ነህ ወደ አቡጉ ቤት እያመለክሁሽ ።

«እሱንስ አልሞክርኩትም ።»

«እንግዲያውስ ሕዱህ ሞክረው ። ከዚህ ብታድር ጥሩ አይሆንም ።»

— 2 —

ያን ቀን ማታ አቡነ ሚሪዩል ከሽርሽር መልስ ብዕሣውን አስቀላቸው ውስጥ ሥዕም ጠው « ግዳጅ » በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ ሊያዘጋጁ ነበሩ ። መጨረስ ሲቃታቸው እንጂ ጽሑፉን ከጀመሩት ጊዜው ውስ አድሮአል ። አበውና ምሁራን የጻፋቸውን መሠረት በማድረግ አርእስቱ ትኀሩን በሁለት ከፈሉት ፦— 1ኛ. የሁሉም ሰው ግዳጅ ፤ 2ኛ በእየመደቡ የእያንዳንዱ ሰው ግዳጅ ። የመጀመሪያውን ግዳጅ በአራት መደብት ፤ ቅዱስ ማቴዎስን በመከተል ፦—

— ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ግዳጅ (ማቴዎስ 6)
— ሰው ለራሱ ያለው ግዳጅ (ማቴዎስ 5 29, 30)
— ሰው ለባሪቢቱ ያለው ግዳጅ (ማቴዎስ 7 12)
— ሰው ለአንስላት ያለው ግዳጅ (ማቴዎስ 6 20, 25)

ሌሎቹን ግዳጆች ከሰፈሙት የጽሑፍ ምንጮች እገኙዋቸው አቡኑ ፦—

— ሰው ለገጢና ለተገዢ ያለውን ግዳጅ ለሮማውያን ከተጻፈው መልእክት ።
— ለሰው ለዳኞች ፣ ለሚሰድቱ ፣ ለእናቱቹና ለወጣቶች ያለውን ግዳጅ ከሳዱስ ጴጥሮስ ።
— ሰው ለአባቶች ፣ ለባሎች ለልጆችና ለእቨከሮች ያለውን ግዳጅ ለኤፌሶን ሰዎች ከተጻፈው መልዕክት ።

— ለወ ለምዕመናን ያለውን ግዳጅ ለዕብራውያን ከተጻፈው መል እክት ።
— ሰው ለደናግል ያለውን ግዳጅ ለቆሮንቶስ ሰዎች ከተጻፈው መል እክት ።

አቡኑ ከእነዚህ ሁሉ ምንጮች ያገኟቸውን አተነባበረው ለምዕመ ናኑ ለማቅረብ ነበር ጽሑፋቸውን የሚያዘጋጁት ።

የተዘረጋ መጽሐፍ በጉልበታቸው ላይ ነበር . . . ከባድ መጽሐፍ ። የሚጽፉባቸው ወረቀቶች ቅጥንሽ ነበሩ . . . ቁመትና ወርዳቸው እኩል የሆነ ። እንዲሁ ሲሠሩ ላሉ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ሲሆን ግዳም


@OLDBOOKSPDF

ማኧር ከክፍላቸው ውስጥ ገብታ ወደ ቱም ሳጥኑ አመራች ። መንዚያና ሹካዎቹን ለመውሰድ ነበር አመጣጧ ። ገበታ መዘጋጀቱንና እህታቸውም ትጠብቃቸው እንደነበር ተገንዝበው ከትንሽ ጊዜ በኋላ መጽሐፋቸውን አጥፈው ፣ ከነበሩበት ተነስተው ወደ ምግብ ቤቱ አመሩ አቡኑ ።

ምግብ ቤቱ ውስጥ አሳት ይነዳል። በጠረጴዛው ላይ የበራ ፋኖስ አለ። የገበታው ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል ። ማዳም ማኧርና ማድሚዘል ባፕቲስቲን ይጨዋወታሉ ።

ማድሚዘል ባፕቲስቲን በናማ ቀለም ያለው ፣ ረጅምና ዘርፋፋ የሐር ቀሚስ ለብሳለች ። ቀሚሱን ከፓሪስ ከተማ በ1806 ዓ. ም. የገዛችው ስለነበረ የዚያን ጊዜ ፋሽን የተከተለ ነበር ። ወገቡ አጠር ፣ ጠበብ ያለ ሆኖ እጅጌው ሰፊ ። ማድሚዘል ባፕቲስቲን ሸበቶ ጸጉሯን በሰው ሰራሽ ጸጉር ሸፍናዋለች ።

ማዳም ማኧር በበኩሏ ነጭ ቆብ ደፍታለች ። አንገቷ ላይ የወርቅ መስቀል አንጠልጥላለች . . . የወይን ጠጅ ቀለም ባለው ማቀብ ። ከሸካራ ሱፍ የተሠራ ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች ። የቀሚሷ እጅጌ ጉርድና ሰፊ ነው ። በትከሻዋ ላይ በጣም ነጭ የሆነ ጨርቅ ጣል አድርጋለች ። በቀይና በአረን ጓዴ ቀለም የተሸራረገረገ ሽርጥ ታጥቃለች ። ሽርጡን በአረንጓዴ መቀነት ሸብ አድርጋዋለች ። ከደረቷ ላይ በሁለት አስርለሞች የተያዘ ሌላ ጨርቅ ይታያል ፤ ከጥጥ የተሠራ ። ሽካራ ጫማ አድርጋለች ። የእግር ሹራቧ ቢጫ ነው ፤ የማርሴይ ሴቶች የሚያደርጉት ዓይነት ።

አቡኑ በገቡበት ወቅት ማዳም ማኧርና ማድሚዘል ባፕቲስቲን የሚ ጨዋወቱት ስለማይዘጋው በር ነበር ። ይኸውም ያለምክንያት አልነበረም ። ጅምበር ከመጥለቋ በፊት ማዳም ማኧር ለራት አስፈላጊ የሆኑትን ለመግ ዛት ወደ ከተማ በወጣችበት ሰዓት በከተማው ውስጥ አንድ እንግዳ ደራሽ የሆነ ሰው መታየቱን ሰምታ ነበር ። እንግዳ ደራሽ ክፉ አመለካከት አለው . . . ዘዋሪ ወንበዴ ነው . . . በከተማው ውስጥ አደጋ ሲጥል ይችላል . . . እያንዳንዱ ሰው መጠንቀቅ ይገባዋል . . . እያንዳንዱም ቤት በሚገባ መቆለፍ ይገባዋል ተብሎ ሲወራ ሰምታ ነበር ።

አቡኑ ከበራድ ክፍላቸው ወደ ምግብ ቤቱ መጥተው በእሳቱ አጠገብ ሲቀመጡ ማዳም ማኧር ስለዚሁ ጉዳይ ስታወራ ነበረች ።

«ማዳም ማኧር የምትለውን ይሰማሉ ?» ስትል ጠየቀቻቸው ማድ ሚዘል ባፕቲስቲን ።

«ድምጿን ሰማሁ እንጂ ያለችውን ቃል በትክክል አልሰማሁም» አሏት አቡኑ ፤ እጃቸውን ጉልበታቸው ላይ ጣል አድርገው ። ፊታቸው በእሳቱ ነበልባል ይጥበረበራል ። ዓይናቸውን ወደ ማዳም ማኧር አዙረው ፤ «ምን ስትዪ ኖሯል ማዳም ማኧር ?» አሏት ፤ «ክፉ ነገር ደርሶ ይሆን ?»


@OLDBOOKSPDF

ግዳም ማሷር ስጋታን ለመግለጽ ዕድል ስላገኙ ለማድማዜል ባፕቲስቲን የነገረቻትን መልላ ለአቡነ ሚሪዬል ትተርከላቸው ጀመር ። ያን ቀን ታይቶ የማይታወቅ ዘዋሪ ወንበዴ ከከተማው ውስጥ መግባቱን ፣ መኝታ ቤቷን ከጥከን ሳባር ሆቴል መሔዱን ፣ ከዚያ መባረሩን ፣ ከዚያ በኋላ በጋሲንዲ ጉዳና ሲዘዋወር መታየቱን ፣ ይህንን ሁሉ እያጋነነች ገለጸችላቸው ።

«እውነትሽን ነው ?» አሏት ።

ጥያቄአቸው የማወቅ ገጥት ያደረባቸው ስላስመሰለባቸው ግዳም ማሷር ደስ ብሏት ጨዋታዋን ቀጠለች ፤ «አዎን ብጹዕነትዎ . . . አሁን ያል ሁት ሁሉ እውነት ነው ። ዛሬ ሴሊት አንዳች አደጋ ሳይደርስ አይቀርም ። የከተማው ሰው ሁሉ የሚያወራው ስለዚሁ ሰውዬ ነው ። በዚያ ላይ በአሁኑ ጊዜ የፖሊስ አገልግሎት እስከዚህም የሚያስቸግም አይደለም ። ይቺ ውም በከንቲባውና በፖሊሱ አዛዥ መሐከል አለመግባባት ተፈጥሯል ስለሚባል ነው ። የመንገድ ሙበራት እንኳ የለም ። ወጣ ሲሉ ዓይን ቢወጉ አይታዩ ጭለማ . . . ! እና እኔም ሆንኩ ማድሚዜል ባፕቲስቲን የምን ሰው . . . » ስትል ማደሚዜል ባፕቲስቲን «እረ እኔ ምንም አላልኩም» አለቻት ። ወንድሚን ስለምትፈራቸው ነው ይህንን ያለችው ። ግዳም ማሷር ግን ማድሚዜል ባፕቲስቲን ያለችውን እንዳልሰማች ሆና ጨዋታ ዋን ቀጠለች ፤ «እኛ የምንለው ይህ ቢት ለአደጋ ተጋልጧል ብጹዕነትዎ ። የሚፈቅዱልኝ ከሆነ አሁኑኑ ቁልፍ ሠሪው ፣ ፖሊን ሚዩዝባ ዘንድ ሔጀ አሮጌዎቹን መወርወሪያዎች በአዳዲስ መወርወሪያዎች እንዲተክቸው ላድርግ ። አዳዲስ መወርወሪያዎች እዚሁ ስላሉን እንዘህን ከመጣጠም በስተቀር ሌላ ችግር የለም ። በአጭር ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ሥራ ነው ። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ማንም ሰው ከውጭ ሆኖ በሮቹን ገፋ አድርጎ መን ሐቆዎቹን አውልቆ ሰላት ብሎ ሲመግባት የሚያጸግሥው ነገር የለም ። ስለዚህ ለክፉ አደጋ ተጋልጠን ነው የምንኖረው ብጹዕነትዎ ። በሮቹ ከው ስጥ መወርወርያ ያሻቸዋል ። ለሌላ ጊዜ ባይሆን እንኳ ለዛሬ ሌሊት ጥን ቃቄ ቢደረግ ይሻል ይመስለኛል ። ብጹዕነትዎ እንደሆኑ ሰው በመጣ ቁጥር ጣባ !» ማለት ይቁናዎታል ። በውድቅት ጨለማ ቢሆን እንኳ ጣባ !» ነው የሚሉት ብጹዕነትዎ ።»

ልክ በዚህ ቅጽበት በሩ በኃይል ተንኳኳ ።

«ጣባ !» አሉ አቡኑ ።

— 3 —

በሩ ወገግ ብሎ ተከፈተ ። ያንኳኳው ሰውዬ እንድ ሮምጀ ገባ ብሎ ቆመ ። በሩን ከፍቶ ትቶታል ። የንብ ከረጢቱ እትከሻው ላይ ነው ። ዘን ጉን ጨበጥ አድርጎ ያዞታል ። በዓይኑ ላይ ድካም ቢነበብበትም የአጥቂ

@OLDBOOKSPDF

ነት መንፈስ ይታይበታል ። ፊቱ በእሳቱ ነበልባል በርቷል ። ደስ አይ
ልም ። ከፋት ያዘለ ያመሰላል ።

ማጻም ማኒር ከመደንገጢ የተነሳ ፈገፃ ቀረቾ ። ማድሚዜል ባፕቲስ
ቲንም ውስጣዊ ሽብር ተሰማት ። አቡኑ ግን ሰውዬውን አተኩረው ተመ
ለከቱት ፤ ረጋ ብለው ።

መንገደኛው አቡኑንና ሁለቱን ሴቶች አፈራርቆ እየተመለከተ ጮክ
ብሎ ይናገር ጀመር ። ገና ማንም ምንም ሳይጠይቀው ፤ «ገፆን ቫልግ አባ
ሳለሁ ። ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት ወህኒ ቤት ታሥሬ ቆይቻለሁ ። ከእስር
ቤት ከተለቀቅሁ አራት ቀናት አልፈዋል ። አሁንም ያንታልሪዩ ወደተ
ባለ አገር በመንገዝ ላይ ነኝ ። ከቱሎ ከተነሳሁ ይኸው አራተኛ ቀኔን ይገፃ
ሰሁ ። ባሬ ብቻ በእግር አምሳ ስድስት ኪሎሜትር ያህል ተጓዦለሁ ።
ከዚህ ከተማ እንደደረስኩ ወደ አንድ ሆቴል ብሔድ የሆቴሉ ባለቤት
አሳሳድር አለኝ ፤ በመታወቂያ ወረቀቱ ምክንያት ። ቀደም ብዬ የመታወ
ቂያ ወረቀቴን ለማሳየት ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ሔጄ ነበር ። የመታወቂያ ወረ
ቀቴን ማሳየት ግዴታ ነበረብኝ ። ከዚያም በኋላ ወደ ሌላ ሆቴል ሔድኩ ።
'ከዚህ ውጣ !' ብለው አባረሩኝ ። ከሁለቱም ሆቴሎች ከተባረርኩ በኋላ
ወደ ወህኒ ቤቱ አቀናሁ ። እዚያም ቁልፍ ያገቡ ሲያሳድረኝ ባይፈልድ ቀረ ።
ቀጥሎም አንድ የውሻ ሜንዴሪያ ንጅ አገኘሁና ከዚያ ገባሁ ። ውሻውም
ሰው እንደሆነ ሁሉ አባረረኝ ። ከከተማው ወጣቾ ሔድኩ ፤ ሜዳ ላይ ለማ
ደር ። ዳመና ሆነ ። የለማይም ከዋክብት ሳይወጡ ቀሩ ። ሳይዘንብ አደቀ
ሮም ብዬ ሰለሰጋሁ ተመልሼ ወደ ከተማው ገባሁ ። ከአንድ ሕንጻ ደጅ
ድንጋይ መቀመጫ ላይ ለማደር ጋደም አልኩ ። ወዲያውኑ አንዲት እመ
ቤት ከነበርኩበት ቦታ መጥታ ወደ እዚህ ቤት እያመለከተች 'ከዚያ ሔደህ
በሩን እንኳኳ' ስትል መከረችኝ ። እንዳሰችኝም እደረግሁ አሰና ፤ «ለመ
ሆኑ ይህ ቤት ምንድነው ፣ ሆቴል ቤት ይሆን ? ከሆነና ልታሳድሩኝ ፈቃ
ደኛ ከሆናችሁ ገንዘብ አሉኝ . . . መቶ ዘጠኝ ፍራንክ ከአስራ አምስት
ሱ . . . በወህኒ ቤት ሳለሁ የተከፈለኝ የጉልበት ዋጋ . . . . በአስራ ዘጠኝ
አመታት ያጠራቀምኩት ። ለመክፈል ዝግጁ ነኝ ። በጣም ደክሞኛል ።
በአንድ ቀን አምሳ ስድስት ኪሎሜትር መንገዝ ቀላል አይደለም ፤ ደሞም
በጣም ርቦኛል ። እና ከዚህ ለማደር እችላለሁ ? ይፈቀድልኛል ?» ሲል
ጠየቀ ።

አቡኑ ዓይናቸውን ወደ ማጻም ማኒር መልሰው «ማጻም ማኒር . . .
በተጨማሪ አንድ ሳህን ፣ አንድ ማንኪያና አንድ ሹካ ብታዘጋጂ . . .»
አሏት ።

ሰውዬው ምስት ሮምጫ ወደፊት ሔድ ብሎ ከጠረጴዛው ላይ ወደነበ
ረው ፋፍስ ጠጋ አለ ። አቡኑ ምን እንዳሰቡ በውል ስላልሰማ ፤ «ያልኩትን
ሰምታችኋል ለመሆኑ ፣ ወህኒ ቤት የጥርዙ መንጀለኛ ነኝ ስል ነበርኩ»
'አለና ከኪሱ የመታወቂያ ወረቀቱን አውጥቶ እያሳየ ፤ «ፓስፖርቴ ይህ
ነውና አለ ፤ «እንደምታዩት በጫ ነው ብለው ። ከሔድኩበት ሁሉ እንድ

@OLDBOOKSPDF

ባረር ያስደረገኝ ይህ ወረቀት ነው ። ልታነብቡት ትችላላችሁ ። ከፈለጋ
ችሁም እኔ ራሴ ላነብላችሁ እችላለሁ ። በወህኒ ቤት ሳለሁ ማንበብ ተምሬ
አለሁ ። አዎ . . . መማር ለሚሹ ከዚያም ቢሆን ትምህርት ቤት አለ›› ብሎ
ጽሑፉን ያነብላቸው ጀመር ። «ሣጉ ቫልጣ . . . ከወህኒ ቤት የተሶቀቀ
ወንጀለኛ . . . የ———ተወላጅ ለአስሪ ዘጠኝ ዓመታት ወህኒ ቤት ቆይ
ቷል ። አምስት ዓመት ፤ ቤት በመስበሩና የስርቆት ወንጀል በመፈጸሙ
ምክንያት ። አስራ አራት ዓመት ፤ አራት ጊዜ ለማምለጥ በመሞከሩ ምክ
ንያት ። በጣም አደገኛ ሰው ነው»

አንቦ ሲጨርስ ፤ «ይኸውላችሁ እንግዲህ . . . ሰው ሁሉ አላሳድርም
ብሎ የሚያባርረኝ በዚህ ወረቀት ምክንያት ነው» ብሎ ፤ «እና እናንተ
ልታሳድሩኝ ፈቃደኛ ናችሁ . . . ? ስመሆኑ ይህ ቤት ሆቴል ቤት ነው
ወይስ ሌላ ?» ሲል ጠየቀ ።

«ማዳም ማሏር . . . » አሉ አቡኑ እንደገና ፤ «ስዚህ እንግዳችን
መኝታ ብታዘጋጂለት . . . በጸሎት ቤቱ ውስጥ ባለው አልጋ ላይ ንዲህ
እንለላ ብታነጥፊለት . . .» አሏት ።

ማዳም ማሏር የአቡኑን ፈቃድ ለመፈጸም ወጥታ ሔደች ። አቡኑም
ዓይናቸውን ወደ መግደኛው አዙረው ፤ «ቁጭ በል ጌታዬ . . . ቁጭ
በልና እሳት ሙቅ ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ አራታችንን እንበላለን ። መኝታም
እየተዘጋጀልህ ነው» አሉት ።

የሰውዬው ፊት በደስታ በራ ። እየተርበተበተም ይናገር ጀመር ።
«እውነት ተቀብላችሁኛል ? ደሞም 'ጌታዬ' ብለው ነው ያነጋገሩኝ . . . !
ሌሎች ሰዎች ግን 'ከዚህ ጥፋ ! አንተ ውሻ !' ብለው ነው የሚያባርሩኝ ።
ታሪኬን ዝክዝክ አድርጌ የነገርኳችሁ ያው ሳታባርሩኝ አትቀሩም በማለት
ነበር ! እና በእውነት ተቀብላችሁኛል . . . ? ይህንን ቤት ያመለከቱኝ
ሴትዮ እንዴት ያለች ደግ ሴት ነች ! አራት ይቀርብልኛል . . . አልጋ ላይ
እተኛለሁ . . . ፍራሽ ያለው ፤ አንሶላ የተነጠፈበት አልጋ . . . እንዴሌላ
ሰው ሁሉ ተዝናንቼ ተኝቼ አድራለሁ . . . ለማመን አልችልም ! »አለና
ንግግሩን በመቀጠል ፤ «እንዴት ያላችሁ ደጋግ ሰዎች ናችሁ ! ለማንኛውም
ገንዘብ አለኝ ። የጠየቃችሁኝን ያህል ለመክፈል ዝግጁ ነኝ ። ይቅርታ
ያድርጉልኝና ሙሴ ባለሆቴል . . . ስምዎንኮ ገና አልነገሩኝም ። ስምዎ
ማነው ? የሆቴሉ ባለቤት መሆንዎ እርግጠኛ ነኝ።ወይንስ ተሳስቼ ይሆን ?»
ሲል ጠየቀ ።

«እኔ ከዚህ የምኖር ካህን ነኝ» አሉት አቡኑ ።

«ካህን . . . ? የዚያ ታላቅ ቤተክርስቲያን ኃላፊ እርስዎ ነዎት ማለት
ነው ? ለመሆኑ ምን ዓይነቱ ዝንጉ ሰው ነኝ ! ቆብ ማድረግዎን እንኳ ልብ
አላልሁም» አለና የጉዞ ከረጢቱንና ዘንጉን ከአንድ ጥግ አኖራቸው ።
የመታወቂያ ወረቀቱንም መልሶ ኪሱ ውስጥ ጨመረውና ቁጭ አለ ።

@OLDBOOKSPDF

ማድሚዘል ባጥቲስቲን በበኩሏ ዝም ብላ ትመለከተው ነበር ። ጨዋታውን ቀጠለ ፤ «ስብእዊ ርኅራሄ ያለዎት ካህን ነዎት ፤ አልናቁኝምና . . . » አላቸው አቡኑን ፤ «እና ካህን ከሆኑ ግንዘብ እያስከፍሉኝም ማለት ነው ?» ሲል ጠየቃቸው ።

«አላስከፍልህም» አሉት አቡኑ ፤ «ግንዘብህን ሰራስህ አድርገው ። ስንት ነው አለኝ ያልከኝ ለመሆኑ ? መቶ ዘጠኝ ፍራንክ ነበር ያልከኝ ?»

«መቶ ዘጠኝ ፍራንክ ከአስራ አምስት ሱ ።»

«ስንት ጊዜ ፈጅብኝ አልከኝ ይቸገን ለማጠራቀም ?»

«አስራ ዘጠኝ ዓመታት ።»

«አስራ ዘጠኝ ዓመታት !» አሉና በኃይል ተነፈሱ አቡኑ ።

ሰውዬው ጨዋታውን ቀጠለ ፤ « ግንዘቡ በመሉ በእጄ ይገኛል ። በአራት ቀናት ውስጥ ከሀያ አምስት ሱ በላይ አሳጠፋሁም ። ስዚሁም ከወህኒ ቤት ከወጣሁ በኋላ ማራስ ከሚባለው ቦታ የጉልበት ሥራ ሠርቼ የተከፈለኝ አንጂ ከዋናው ግንዘቤ የተቀነሰ አይደለም » አሉና « ካህን ስለሆኑ ሌላም የምነግሮት አለኝ ። በአስር ቤት ውስጥ ሳለን አንድ ቄስ ነበሩን ። ደሞም አንድ ቀን አንድ አቡን መጥተው ገበኙን ። ብጹዕ ነታቸው ተበለው ይጠራሉ ። በማርሴይ ውስጥ ማግኮር ተበሎ የሚጠራው ቦታ አቡን ናቸው ። በራሳቸው ላይ ከወርቅ የተሠራና ወደ ላይ የሾለ የራስ ቆብ ያደርጋሉ..... በጸሐይ ብርሃን የሚጥበረበር የወርቅ ቆብ ። አቡን ማለት የካህናት አለቃ ማለት ነው ። ያውቁ የለ .....? ታዲያ አቡኑ ከዚያ መጥተው ቅዳሴ ቀደሱ ። እኛም በሦስት ረድፍ ቆመን ተመለከትናቸው ። ከፊት ለፊታችን መድፍ ተጠምዶ ነበር ። አቡኑ ንግግር አደረጉ ። ነገር ግን ከኛ ራቅ ብለው ስለነበር ምን እንዳሉ ሊመስማት አልቻልንም ። እና አቡን ማለት እንዲያ ያለ ሰው ነው» ሲል አስረዳቸው ፤ እሳቸው ፡ ራሳቸው አቡን መሆናቸውን ባለመረዳት ።

በሩ እስካሁን ድረስ ሳይዘጋ በመቅረቱ ይበርድ ስለነበረ አቡኑ ተነ ስተው ዘጉትና ወደመቀመጫቸው ተመለሱ ። ማዳም ማኟርም ሹካና ማንኪያ ይዛ መጥታ ጠረጴዛው ላይ አኖረቻቸው ። «ማዳም ማኟር..... እነሱን እቃዎች ከእሳቱ አጠገብ ባታርቂያቸው .....» አሉና ፊታቸውን ወደ እንግዳቸው መልሰው ፤ « በአልፕስ ተራራ አካባቢ ነፋሱ የሚጋረፍ ስለሆነ በጣም ሳይበርድህ አልቀረህም ጌታዬ » አሉት ።

« ጌታዬ » ብለው በጠሩት ቁጥር የሰውየው ፊት ብርሃን ይለብስ ነበር ፤ ጌታዬ ተበሎ መጠራት ለወንጀለኛ ሰው ብርቁ ነውና ።

« የዚህን ፋኖስ ብርሃን እጅግም አልወደድኩትም » አሉ አቡኑ ቀጠል አድርገው ። ምን ማለታቸው እንደሆነ ግባትና ማዳም ማኟር ሁለቱን መቅረዞች ከመኝታ ቤታቸው አምጥታ ሻማዎቹን አበራቻቸው ።



@OLDBOOKSPDF

« ሙሴ ካህን ..... ደግ ሰው ነዎት ። እኔን ሳይነቁ እቢተም ውስጥ ያስተናግዱኛል ። ለኔ ብለው በብር መቅረዝ የተሰኩ ሻማዎች እንዲበሩ አድርገዋል ። ከየት እንደመጣሁና ያልታደልሁ ሰው መሆኔን ሳልደብቅ ብንነግርዎትም ቅሉ አክብረው ተቀብለውኛል » አላቸው ።

አቡኑ ቀሰ ብለው እጅን ነክተና ፣ « ታሪክህን ሳትነግረኝ ልት ቀር አይቻልህም ነበር» አሉት ፣ ወደሞም ይህ ቤት የኔ ቤት አይደለም ። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤት ነው ። እዚህ ቤት የሚገባ ሰው ጥሩ ስም ይኑረው አደኑረው አይጠየቅም ። የሚጠየቀው ችግረኛ መሆን አለመሆኑ ብቻ ነው ። አንተ ችግረኛ ነህ ። በጣም ተሰቃይተሃል ። ተርበሃል ። ተጠም ተሃል ። ቤት ለእንግዳ ብለኃሃል ። ደሞም እንድታመሰግነኝ አልፈል ግም ። እቢትህ ውስጥ አስተናግድኸኝ አትበለኝ ። በዚህ ቤት ሲዝናና የሚችል መጠጊያ ያጣ ብቻ ነው ። ምንም እንኳ ተሳላፊ መንገደኛ ብትሆን ይህ ቤት እኔን ከሚቀበለኝ ይልቅ አንተን ይቀበልሃል ። እዚህ ቤት ውስጥ ያለው ሁሉ ያንተ ነው ። ስምህን ነገርከኝ አልነገርከኝ ምን ያደርግል ኛል ! ደሞም ማን እንደሆንክ ሳትነግረኝ በፊት አወቅ ነበር » አሉት ።

ሰውዬው በመገረም ዓይኑን ከፈት አድርጎ አያቸው ። « እውነት ማን እንደምባል ያውቁ ኖሯል ? » ሲል ጠየቃቸው ።

« አዎን ..... 'ወንድሜ' ትባላለህ » አሉት ።

« ኧረ አሁንስ በቃኝ ሙሴ ካህን ..... ! እዚህ ስገባ ርቦኝ ነበር ። አሁን ግን ያለቅጥ ደግ ሰለሆኑብኝ ረሃቡም ለቅቆኛል ። »

አቡኑ በርህራሄ ዓይን አዩትና « በጣም ተሰቃይተሃል ..... መከራም ደርሶብሃል » አሉት ።

« አሱማ ምኑ ይጠረጠራል ! መኝታዬ እንጨት ነበር ። ሐሩሩ ..... ቁሩ ..... ድካሙ ..... ግርፋቱ ..... በድርብ ሠንሠለት መታሠሩ ..... አንድ ቃል ቢተነፍሱ ተነጥሎ ለብቻ መታሠሩ ..... » አሰና « ቢታመሙ እንኳ ሰንሰለቱ አይፈታም ። ከአስረኛ ሕይወት የውሻ ሕይወት ይበልጣል! በዚህ ሁኔታ ለ 19 ዓመታት ወህኒ ቤት ኖሬአለሁ ። አሁን ዕድሜዬ 46 ዓመት ሆኖኛል ። በመጨረሻም በጫወታ የመታወቂያ ወረቀት ይገር ወጣሁ » አላቸው ።

« በእርግጥም በጣም ከሚያሳዝን ቦታ ነው የመጣኸው » አሉት ፣ « ስማኝ ..... ከመንግሥት ሰማይ ወስጥ መሩ በጎ ሰዎች ከሚያገኙት ደስታ አንድ የተጸጸተና ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀ ኃጢአተኛ የሚያገኘው ደስታ ይበልጣል ። ወህኒ ቤት ውስጥ በመሰቃየት ሠ ሰው ሁሉ የሚስጠላህና የሚያሰቅጣህ ከሆነ እንዲታዘንልህ ይገባል ። በሃሳብህ ከነመንፈስና ሰላም ይዘህ ከመጣህ ግን ከሠላችንም ትበልጣለህ ። »

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ጊዜ ማዳም ማሲር የሚበላ ነገር ይዛ ቀረበች ፣ — ሾርባ ፣ ዳቦ ፣ ጨው ፣ ትንሽ ያሳማ ሥጋ ፣ ትንሽ የጠቦት ሥጋ ፣ ፍራፍሬና ትኩስ እይብ ። በገዛ ፈቃድዋም የሞቀ ወይን ጠጅ አቀረበች ማዳም ማሲር ።

አቡኑ ጥሩ እንግዳ ተቀባይ እንደመሆናቸው መጠን በቀረበው ሁሉ ደስ አላቸው ። « ገበታ እንቅረባ ! » ብለው ተነሱ ። እንግዳቸውን በስተ ቀኛቸው አስቀመጡት ፤ እሀታቸውን በስተግራቸው ። ከዚያም በኋላ አሳረጉና ሾርባውን ራሳቸው ጨልፈው አደሉ ። መንግደኛውም ጥሞት ይበላ ጀመር ።

« እንዳች የጐደለ ነገር አለ መሰለኝ » አሉ አቡኑ ። በገበታው ላይ ሦስት ማንኪያዎችና ሦስት ሹካዎች ብቻ ነበሩ ። በተለምዶ ግን እንግዳ ሲኖር ስድስት ማንኪያዎችና ስድስት ሹካዎች ይቅርቡ ነበር ። የዚህ ዓይነቱ ትርዒት አቡኑን ያስደሰታቸው ነበር ፤ እንደ ሕጻን ልጅ ። ቤቱ በቁጠባ የሚኖርበት ቢሆንም ስድስት የብር ማንኪያዎችና ሹካዎች ተዶርድረው ሲታዩ የብልጽግና አካባቢ ይፈጥሩ ነበር ።

ማዳም ማሲር አቡኑ ምን እንደፈለጉ ገብቷት እንዳችም ቃል ሳትተነፍስ ወጥታ የተቀሩትን ሦስት ሹካዎችና ማንኪያዎች ይዛ መጥታ በገበታው ጨርቅ ላይ አኖረቻቸው ። ማንኪያዎቿና ሹካዎቿም እንደተለመዱ ደው በሻማዎቹ ብርሃን ይጥበረበሩ ጀመር ።

— 4 —

ገበታ በቀረቡበት ስዓት አቡኑና እንግዳቸው ምን እንደተነጋገሩ ለመግለጽ ግድ ሚዜል ባፕቲስቲን ለወዳጇ ለማዳም ቧሽቭሮ ከጻፈቻቸው ደብዳቤዎች በአንደኛው የገለጸችውን በከፊል ከማቅረብ የተሻለ ዘዴ አይገኝም ። ደብዳቤው እንሆ ፤

« ____ ይህ ሰው ለማንኛችንም ቢሆን ደንታ አልነበረውም ። በጣም ርቦት ስለነበረ ራቱን ተስገብግቦ በላ ። በልቶ ለመጨረስ ሲቃረብም 'ይህ ሁሉ ምግብ ለኔ ይበዛብኛል አለ' ፤ 'ይሁን እንጂ ከተባረርኩበት ሞቴል ለሹፌሮቹ ይዘጋጅ የነበረው ምግብ ከዚህኛው በጣም የተሻለ ነበር ።'

« በአንቺና በእኔ መሐከል ይቅርና የሰውዬው እነጋገር በጣም አስደነገጠኝ ። ወንድሜም ፣ 'ሹፌሮቹ ከእኔ የተሻለ ምግብ ቢበሉ ይገባቸዋል ——ከእኔ ይበልጥ ይደክማሉና' ፤ አሉት ።

@OLDBOOKSPDF

‘የለም ! ’ አለ ሰውዬው ፡ ‘ሹፌሮቹ የተሻለ ምግብ የሚበሉት ከእርስዎ የበለጠ ገንዘብ ስላላቸው ነው ። እርስዎ ድሃ መሆንዎ በግልጽ የሚታይ ነው ። እውነት የደብር አለቃ ነዎት ሰመሆኑ ? ደኑ እግዚአብሔር ፍትህ የሚያውቅ ከሆነ የደብር አለቃ መሆን ያገባዎታል ።’

‘ደኑ እግዚአብሔር ፍትህ አዋቂ ብቻ አይደለም ። ከዚያም በላይ ነው’ አሉትና ‘ሙሴ ግን ቫልግ ..... ወደ ፖንታርልዬ ነው የም ትሔደው ?’ ሲሉ ጠየቁት ።

‘አዎን ..... በቀጥታ ወደዚያ ነው የምገሰግሰው ። ነገ ጠዋት ጎሕ ሲቀድድ መንገድ መጀመር ይገባኛል ። የግር ጉዞ ቀላል አይደለም ። ሴሲት ቁር ፡ ቀን ሐሩር አለ’ አሳቸው ።

‘ወደ ጥሩ አገር ነው የምትሔደው’ አሉት ወንድሜ ፤ ‘በአብዮቱ ወቅት ወላጆቹ ዱብ ዕዳ ወድቆባቸው የነበራቸውን ሁሉ አጡ ። እኔም በመጀመሪያ ወደ ፍራንሽ ኮንቲ ሐጂ ከዚያ መጠጊያ አገኘሁ ። እዚያ እያለሁ የጉልበት ሥራ እየሠራሁ እተዳደር ነበር ። ቀኑ አስተሳሰብ ስለ ነበረኝ ሥራ አላጣሁም ። የሥሪም ምርጫ ተትረፍርፎ ይገኝ ነበር ። ፤ወረቀት ፋብሪካ ፡ የቆዳ ሚሰስለኛ ፋብሪካ ፡ የአረቄ ፋብሪካ ፡ ሰዘይት ፡ ፋብሪካ ፡ የሰዓት ፋብሪካ ፡ የብረታ ብረት ፋብሪካ ፡ የመያዣ ፋብሪካ ፡ ከሠያ የማያንሱ የብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች ፡ እነዚህ ሁሉ ነበሩ ። ከሠያዎቹ የብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች አንደኛው በሴሞድ ፡ ሁለትኛው በሻቲ ዮን ፡ ሶስተኛው በኦዲንኩር ፡ እና አራተኛው በበር ነበሩ’ አሉትና አይናቸውን ወደ እኔ መልሰው ፤ ‘በእነዚህ ቦታውች ዘመድ የሉን ይሆን ሲሉ ጠየቁኝ ። ‘ነበሩን ..... ሌላ ባይሆን ከለወጡ በፊት በፖንታርልዬ የዘበኞች ሻምበል የነበረው ዩ ሉሲኦ ከዚያ ይኖር ነበር’ አልኳቸው ።

‘አዎ ..... ! ብቻ በ1793 ዓ. ም. ዘመድ የሚባል ሰው አልነበረም ። የእያንዳንዱ ሰው ዘመዱ በእጁ የያዘው መሣሪያ ነበር ።’ አሉና ሃሳባቸውን ወደ ግርን ባልግ መልሰው ፤ ‘በምትሄድበት አገር ፡ በፖንታርልዬ በጣም ደስ የሚል አንዱስትሪ አለ ..... የአይብ ኢንዱስትሪ ። እዚያ እንኳ ፍሩቶዬር ብለው ይጠሩታል’ ሲሉ አስረዱት ። ቀጥለውም ፤ ‘ብላ እንጂ .....ብላ’ ብለው ጋበዙትና ስለ አይብ አሠራር በበለጠ ያስረዱት ጀመር ። ከጨዋታቸው እንደተረዳሁት ከዚያ ቦታ ሁለት ዓይነት የከበት ማደሪያ በረቶች አሉ ። አንደኛውና ትልቁ የሀብታሞች ንብረት ሆኖ ከአርባ እስከ ሃምሳ ከብቶች ያድሩበታል ። ከእነዚህ ላሞች የሚታለበው ወተት ከስባት እስከ ስምንት ሺ አሰር የሚደርስ አይብ ይወጣዋል ። በሁለተኛው በረት የድሆች አርሶ አደሮች ከብቶች ያድሩበታል ። እነዚህ ከብቶች የአርሶ አደሮቹ የወል ንብረትን ናቸው ። ከወተታቸው የሚሠራው አይብም የወል ንብረት ስለሆነ ይከፋፈሉታል ። አርሶ አደሮቹ ግሩፈ የተባለውን አይብ ሠሪ ቀጥረው አይብ ያሠሩታል ። አይብ ሠሪው በቀን ሦስት ጊዜ ከአርሶ አደሮቹ አስፈላጊውን ወተት ይቀበላል ። አይብ መሥራት የሚጀምረው በሚያዝያ ወር መጨረሻ አካባቢ ሆኖ በስኔ ወር አጋማሽ ላይ ከብቶቹ ወደጋራው ይነዳሉ ።



@OLDBOOKSPDF

«ሰውዬው እራት በሚበላበት ጊዜ ይበልጥ ደስ እያለው ሔደ ። ወንድሚም ወይን ጠጅ እንዲጠጣ ጋበዙት ። እሳቸው ግን ሞቭ ወይን ጠጅ አይጠጡም ፤ ዋጋው ውድ ነው በማለት ። ወንድሚ ከሰውዬው ጋር የሚጫወቱት ተዝናንተው እንኟ ተጠበበው ፡ ተጨንቀው አልነበረም ። መቼም ጠባያቸውን ታውቂአለሽ ። ለሰውዬው ቀጥታ የሆነ ምክር ባይሰጡትም የአይብ ምርት ሥራ ጥሩ መሆኑን ደህና አድርገው ነገሩት ፤ በዚያ ሙያ ቢሰማራ ይጠቅመዋል በማለት ። ያስገረመኝ ነገር ቢኖር ባጨዋታቸው መጀመሪያ ላይ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ጥቂት ከማንሳታቸው በስተቀር ስለሰውዬው ማንነትም ሆነ ስለራሳቸው አነዳችም ነገር አለ ማውራታቸው ነው ። ሲሰብኩትና አሻራቸውን በእሱ ላይ ሊተው ፡ ሥጋ ውን ብቻ ሳይሆን ነፍሱን ሊመግበት ፡ ሊገስጸውና የሞራል ትምህርት ሊሰጠት ፡ ለወደፊት የተሻለ ሰው እንዲሆን ሊመክሩት ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። እሳቸው ግን ይህንን ሁሉ አላደረጉም ። ስለሕይወት ታሪክና ስለመጣበት አገር እንኳን አልጠየቁትም ። በሕይወት ታሪኩ ውስጥ እንዳች እንኩን እንዳለበት ጥርጥር የለውም ። ወንድሜም ስለሕይወት ታሪኩ ሳይጠይቁት የቀሩት ይህንን ቁስሉን እንዳይኩነበት በመፍራት ሳይ ሆን አይቀርም ። እንዲያውም በፖንታርልዬ የሚኖሩት ደኅኖች በጥሩ ሥራ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውንና ንጹህ ስምች በመሆናቸውም ተደስተው እንደሚኖሩ ጠቅስ ካደረጉለት በኋላ ጨዋታቸውን ቁርጥ አደረጉት ። ይኸውም ሰውዬውን የሚያቆስል ነገር ሳያነሳበት እንዳያነሱበት በመ ጠንቀቅ መስለኝ ። ይህ ግን ኻልኟ የተባለው ሰው በሕይወቱ ብዙ መከራ የደረሰበት በመሆኑ የመከራውን ቁስል እንዳይነኩበት ቢጣም ነው የተጠ ነቀቁት ። መከራና ስቃዩን እንዲረሳ ከማድረግ የተሻለ ሌላ ዘዴም አል ነበረም ። ይህንንም ለማስረሳት እንደማንኛውም ሰው ቆጥሮ ማነጋገር ኦስ አስፈላጊ ነበር ። ለሰው ደህንነት ማሰብና መቆርቆር ማሰት ይኸው አይ ደል? ወዳጄ ማዳም.....ይህ ታዲያ እውነተኛ ሐዋርያዊ ሥራ አይደለም ይሆን? የሰውን ቁስል ከመንካት መቆጠብ አዛኝነትም አይደል? የወንድሜም አስ ተሳሰብ ይኸው ነበር ይመስለኛል ። ለማንኛውም ግሳባቸው ይህ ስለመሆኑ አንዳችም ጥንቄ አላሳየም ። ከመጀመሪያ አስከ መጨረሻ የተለምዶ ራሳ ቸው ነበሩ ። ራት የበሉትም ከዚህ ሰውዬ መሆኑ ቀርቶ ከሙሴ ጌዴዎን ለ ፕሬቮ ወይም ከደብሩ ካህን ቢሆን ኖሮ ምንም ልዩነት ባልኖረው!

«በመጨረሻም ፍራፍሬ ለመብላት ስንቃረብ በሩ ተንኳኳና እማሆይ ጌርቦ ገቡ ። ሕጻን ልጅ ታቅፋው ነበር የመጡት ። ወንድሚ ሕጻኑን ልጅ ግምባሩ ላይ ሳመት ። ከዜም 15 ሰ ተበድረው ለእማሆይ ጌርቦ ሰጪቸው ። ሰውዬው በዚያን ጊዜ መንፈሱ ከኛ ጋር አልነበረም ። መናገርም አቁሞ ነበር ። ደሞም በጣም የደከመው ይመስል ነበር ። እማሆይ ጌርቦ ከሔዱ በኋላ ወንድሜ ጸሎት አደረጉና ዓይናቸውን ወደሰውዬው አዙረው 'ለመ ተኛት ሳትቻኮል አልቀረህም' አሉት ። ወዲያውኑ ማዳም ማኟር የበላንባ ቸውን ቁሳቁሶች አነሳቻቸው ። ከዚያ በኋላ መሔድ እንዳለብን ስለገባን እኔና እሷ ወደ ፎቁ ወጣን ። ከክፍላችን ከደረስን በኋላ ግን ማዳም ማኟር ከእኔ ክፍል የነበረውን ቁርበት ለሰውዬው እንድታወርድለት ላክኋት ። ቁርበቱ ከፍየል ቆዳ የተሩተ ነው ። ሌሊቱ ይበርድ ስለነበረ ትንሽ ቢያ



@OLDBOOKSPDF

ሞቱው ብዬ ነው የላክሁለት ። ሆኖም ቁርበቱ አሮጌ በመሆኑ እዘንኩ ፥ ጸጉሩም ሁኔታቅሉ በመውደቅ ላይ ይገኛል ። ወንድሜ ጀርመን አገር በነበሩበት ጊዜ ከፉትሲንግን የገዙት ነበር ፣ ከዳኑብ ወንዝ መነሻ አጠገብ ። እኔ የምገለገልበትና የዝሆን ጥርስ እጀታ ያለው ትንሹ ቢላዋም ከዚያ ነበር የተገዛው ።

ፈሚዳም ማሷር ቁርበቱን አድርሳ ከመጣች በኋላ ልብስ ከምናለማበት ክፍል ውስጥ ጸሎት አድርገን ወዴ የመኝታ ክፍላችን አመራን ።

— 5 —

ሲቶቹ ከወጡ በኋላ አቡነ ሚሪዩል አንዱን መቅረዝ አንስተው ይዘው ሁለተኛውን ለእንግዳቸው ሰጠትና «በል እንግዲህ— ወደምታድርበት ክፍል ልውሰድህ» አሉት ። አቡ ከኋላ አሳቸው ከፊት ሆነው ወደ ጸሎት ቤቱ አመሩ ። በአሳቸው መኝታ ቤት ሰያልቅ ማዶም ማሷርን አይዋት ። ማዶም ማሷር ከብር የተሠሩትን ማንኪያዎችና ሹካዎች ከአቡኑ አልጋ ራስጌ ባለው ቁም ሳጥን ውስጥ ስታኖራቸው ነበረች ። ከራት በኋላ ወደ መኝታ ቤታ ገብታ ከመተኛቷ በፊት በመጨረሻ የምታከናውነው የዕለት ተግባሯ ይኸው ነበር ።

ከጸሎት ቤቱ ደርሰው ሰውዬው መቅረዙን አሰከነሻማው በእንድ ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ከሰቀመጠው በኋላ አቡኑ«ወበል ደህና እደር— ነገ በዋት እንዳች ነገር ሳትቀምስ መንገድ እንዳትጀምር ። አንድ ሁለት ሳምት ሰላ ሉኝ ትኩስ ወተት አይጠፋም» አሉት ። እሱም አመሰገናቸው ። ከዚያ በኋላ ግን በድንገት አስደንጋጭ ቃል ተናገራቸው ። ማዶም ማሷርና ማድ ሟዜል ባጥቂስቲን ከዚያ ጥረው ያለውን ቢሰሙ ኖሮ ሕሊናቸውን ስተው ሳይወድቁ ባልቀሩም ነበር ። እንዲህ ያለ ቃል ለምን እንደተናገራ ቸው የሚያውቅ የለም ። ምናልባት ሲያስጠነቅቃቸው ወይም ሲያስፈራ ራቸው አስቦ የተናገረው ሲሆን ይችላል ። አለዚያም ሊቆጣጠረው የማይ ችል ውስጣዊ ኃይል አስገድዶት ሊሆን ይችላል ። በድንገት ወዴ አቡኑ ዞሮ ፣ እጆቹን በደረቱ ላይ አጣምሮ ፣ እንደተናከሸ አውሬ እፍጥ እየተመለ ከታቸው የተናገረው ቃል እንዲህ የሚል ነበር ፣ «ግሩም! እዚህ ሲያሳድሩኝ ነው—? ያውም ከመኝታ ቤትም ለጥቆ ባለው ክፍል!» ቀጠል አድርጎም የሸር ሳቅ እየሳቀ ፣ «ለመሆኑ በነገሩ አስበውበታል፣ የሚያደርጉትን አረ ጋግጠው ያውቃሉ፣ ነጭሰ ገዳይ ብሆንስ!—» አላቸው ።

«ይህ የደኅ እግዚአብሔር እንጂ የኔ ጉዳይ አይደለም» አሉትና በዝ ምታ ጸሎት እንደሚያደርግ ሰው ከንፈራቸውን እያንቀሳቀሱ የቀኝ እጃቸ ውን ሁለት ጣቶች ወዴ ላይ እንስተው ቡራኬ ሰጡት ። ሰውዬው ግን እን

@OLDBOOKSPDF

ግብን እንኳ ቀለሰ አላደረገላቸውም ። ከዚያ በኋላ አቡኑ ፈታቸውን ወደ መኝታ ቤታቸው መለሱ ።

እንግዳ ባለ ጊዜ በጸሎት ቤቱ ውስጥ ያለው መቅደስ ከእንግዳው እልጋ በጨርቅ መጋረጃ ይከለል ነበር ፣ ከአንዱ ግድግዳ አስከሌላው ግድ ግዳ በሚደርስ መጋረጃ ። አቡኑ ወደ መኝታ ቤታቸው ሲመለሱ ሰሉ በመ ጋረጃው አጠገብ ተንበርክከው ለአጭር ጸሎት አደረጉ ። ከዚያ በኋላ ወደ አትክልቱ ሥፍራ ወጥተው ይንሸራሸሩ ፣ ያስቡ ፣ ያሰላስሉ ፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የሰማይ ነዋክብትንም ያስተውሉ ጀመር ።

ሰውዬው በበኩሉ በጣም ደክሞት ስለነበረ ሰሉ ተብለው የተነጠፉ ትን ንጹህ አንሶላዎች በዚያ እንደሌሉ ያህል ትኋቸው ልብሶቹን እንኳ ሳያወልቅ ከአልጋው ላይ ወርዶ ጋደም አለ ። ሻማውን በአፉ ትንፋሽ እፍ ብሎ ሲያጠፋው ሰኞል የማያመቹ ወንጀለኞች እንደሚያደርጉት በአፍንጫው ትንፋሽ እፍ ብሎ አጠፋው ። ወዲያውኑም ከጥልቅ የእንቅ ልፍ ባህር ውስጥ ገብቶ ሰጠመ ።

አቡኑ ከአትክልቱ ቦታ ወደ መኝታ ቤታቸው ሲመለሱ መንፈቅ ለሊ ሊት ሆኖ ነበር ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሁላቸውንም እንቅልፍ ያዟቸው አልም አለ ።



ዣን ቫልጋ ብሪ ከተባለ ሥፍራ ፣ ከአርስ አደር ቤተሰብ ይወለዳል ። እናቱ ዣን ማትዮ ትባል ነበር ፣ አባቱም ዣን ቫላገ ። ገና ሕጻን ሳለ ሁለ ቱም ሞቱበት ። እናቱ የተበላሸ ወተት ጠጥታ ሞተች ። አባቱም ከሠፍ ላይ ወጥቶ እንጨት ሲመለምል ወድቆ ሞተ ።

እነሱ ካረፉ በኋላ ታላቅ እህቱ አሳደገችው ። እሷም ባለትዳርና የሰባት ልጆች እናት ነበረች ። በልጅነቱ ቄንጮት ነበር ዣን ቫልጋ ። ነገር ግን ቀሰስተኛና ለዓይን የማያሞላ ልጅ ነበር ።

ዣን ቫልጋ ዕድሜው ሀያ አምስት ዓመት ሲደርስ የእህቱ ባል ሞተ ። በዚያን ጊዜ ከሰባቱ የእህቱ ልጆች የመጀመሪያው ስምንት ዓመት ዕድሜ ነበረው ። የመጨረሻው ገና የአንድ ዓመት ሕጻን ነበር ። በዚህ ምክንያት የቤተሰቡ ኃላፊነት በዣን ቫልጋ ትከሻ ላይ ወደቀ ። እንደ እባቱም ዛፍ መልማይ ሆኖ ይተዳደር ጀመር ። የሚከፈለው የጉልበት ዋጋ በጣም እንስተኛ ነበር ።



@OLDBOOKSPDF

ማታ ማታ ከሚሠራበት ቦታ ፥ ከሩቬሮል ድክምክም ብሎት ይመለ
ሳል ። እህቱ ምግብ ታቀርብለታለች ። አቀርቅሮ በዝምታ ይበላል ። እን
ዲህ በሚያቀረቅርበት ጊዜ ጸጉሩ በሳህኑ አካባቢ ይነጠሳል ። ዓይኑንም
ይሸፍነዋል ። እህቱ ከቀረበችለት ምግብ ፥ ከጥሩ ጥሩው እየቀነጠረች ፥
ከልጅቷ ለአንዱ ትሰጠዋለች ። ግን ቫልጣ እንዳላየ ሆኖ ዝም ይላታል ።

ሩቬሮል ውስጥ እነ ግን ቫልጣ ከሚኖሩባት ትጅ አትራቢያ ፥ ከመን
ገዱ ማዶ የምትኖር ማሪ ክለሎድ የተባሉች የአንድ ገበሬ ሚስት ነበረች ።
የግን ቫልጣ የእህቱ ልጆች ብዙ ጊዜ ስለሚራቡ አልፎ አልፎ ወደ ማሪ
ክለሎድ ዘንድ እየሄዱ በአናታቸው ስም ወተት ይበደራሉ ። በሷ ስም
ወተት እንደማበደሩ ግን ቫልጣ ያወቅ እንጂ እናታቸው አታውቅም ፥
የተበደሩትን ወተት ከእጣር መንገድ ጥግ ወይም ከጥሻ ሥር ሆነው ይጠጡ
ታል ። እየተሻሙ ፥ እየተናጠቁ ስለሚጠጡት ወተቱ በልብሳቸውና በአን
ታቸው ይፈነጠቃል ። በመጨረሻም የከፍያው ጊዜ ሲደርስ ሂሳቡን የሚ
ከፍለው ግን ቫልጣ ነበር ። ልጆቹ ሳይሳቡ ተልከናል ብለው ከማሪ ክለሎድ
ወተት ተበድረው እንደሚጠጡ እናታቸው ብታውቅ ኖሮ ከግርፋት ባል
ዳኑ ነበር ። እሷ ግን ፈጽሞ አታውቅም ነበር ።

ግን ቫልጣ በቀን 18 ሱ እየተከፈለው ዛፍ መልማይ ሆኖ ለተወሰነ
ጊዜ ከሠራ በኋላ በተሰያየ ሙያ ሳይ ተሰማራ ። አንድ ሰሞን ድርቅሽ
አድራቂ ሆኖ ሠራ። ቀጥሎም የቀን ሙያተኛ፣የከብት እረኛ፣እና ቁሻሻ አንሺ
ሆኖ ሠራ ። እንደነገሩ እህቱም ሥራ ነበራት ። ነገር ግን የሁለቱም ገቢ
በጣም አነስተኛ ስለነበረ ሰባቱን ልጆች ማሳደግ ቀላል አልነበረም ።
ከዚያም በኋላ ይባስ ብሎ ግን ቫልጣ ሥራ አጥ ሆነ ። ወራቱ ክረምት
ነበር ። የሚላስ የሚቀመስ ነገር አልነበረም ።

አንድ ቀን እሁድ ማታ በዚሁ ወራት በሩቬሮል፣ በካቱድራሉ አደባባይ
ይኖር የነበረና ሞቤር ኢዛቦ ተብሎ ይጠራ የነበረው ዳቦ ጋጋሪ ከመሻታ
ቤቱ ገብቶ ለመተኛት ይዘገጃጅ በነበረበት ሰዓት ከዳቦው ሱቅ በኩል በኃ
ይል የሚንጓጓ ድምጽ ሰማ ። ሌባ ይሆናል ብሎ በመጠራጠር ወደ ሱቁ
አመራ ። በእርግጥም አንድ ሌባ የሱቁን የመስታወት መስኮት በቡጢው
ሰብሮ ዳቦ ሲሰርቅ ነበር ። ሞቤር ኢዛቦ ከቦታው ሲደርስ ሌባው ዳቦውን
ይዞ ፈረጠጠ ። ሞቤር ኢዛቦ ተከታተለው ። ሌባው ሩጦ ለማምለጥ የተቻለ
ውን ያህል ጥረት አደረገ ። ሞቤር ኢዛቦ ግን አልለቅ ብሎ ተከታተለውና
በመጨረሻም አስቆመው ። ማምለጥ አለመቻሉን ሲረዳ ሌባው ዳቦውን
ሶ ባለቤቱ መረመረለት።እጁንም መስታወቱ ቆርጦት ኖሮ ደም ሲፈስሰው
ነበር ። ሌባው ግን ቫልጣ ነበር ።

ይህ የሆነው በ1795 ዓ፡ ም፡ ነበር ። ግን ቫልጣ በስርቆት ወንጀል
ተከስሶ ፍርድ ቤት ቀረበ ። ወንጀሉን ይበልጥ ያከበደበት ሌላም ነገር
ነበር ። ግን ቫልጣ ቀድም ብሎ ሕገ ወጥ አደን ያድን ነበር ። ለዚህም አስቦ
የጣው ጠበንጃ እንደነበረው ተረጋገጠበት ። ሕብረተሰቡ ሕገ ወጥ አደን

@OLDBOOKSPDF

በሚያድኑና ስውር ንግድ በሚያካሂዱ ሰዎች ላይ መጥፎ አስተያየት ነበረው ። እነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች እንደወንበዴዎች ይቆጠሩ ነበር ። ይሁን እንጂ እነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ከከተማ ነፍሰ ገዳዮች የሚመደቡ አልነበሩም ። የከተማ ነፍሰ ገዳዮች በጣም ጨካኞች ናቸውና ።

የሆነ ሆኖ ጐን ቫልጣ የስርቆት ወንጀል በመፈጸሙ ከፍርድ ቤት ቀርቦ የአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈረደበት ።

በሚያዝያ 22 ቀን 1796 ዓ. ም. በቤስትር ጽኑ እሥራት የተፈረደባቸው ሰዎች ፣ ጐን ቫልጣ ጭምር ሰንሰለት ውስጥ ገቡ። በዛሬው ጊዜ ዕድሜው 80 ዓመት ለመድረስ የተቃረበና የወህኒ ቤት ዘበኛ የሆነ አዛውንት ስለዚያን ቀን እንዲህ ይላል። «ጐን ቫልጣ ያን ቀን እንዴ ሌሎቹ እስረኞች መሬት ላይ ተቀምጠ ነበር ። ሰንሰለቱን አንገቱ ላይ አድርጓው ከወደማጅራቱ በመዶሻ እየመቱ ሲያጠብቁት እንባ አውጥቶ አለቀሰ ። እንባው አሳ ናማር አሰው ። አልፎ አልፎ ግን በሩቼሮል ባጭ መልማይ ነበርኩ ይል ነበር ። ከዚያም በኋላ እጁን አንስቶ ቀስ በቀስ በስባት ደረጃ ወደታች እየወረደ ያሳይ ጀመር ። የተለያየ ቁመት ያላቸው ሰባት ራሶችን በእጁ የሚነካ ይመስል ነበር ። ወንጀል የፈጸመውና ጽኑ እሥራት ሲፈረድበት የቻሶውም ሰባቱን ሕጻናት ልጆች ከረሀብ ለማዳን ያደረገው መሆኑን መላ ለጹ ነበር ።»

ጐን ቫልጣ ከሴሎቹ እሥረኞች ጋር ሆኖ ሰሀያ ሰባት ቀናት በጋሪ ተጉዞ እሥራቱ ወደሚፈጸምበት ወደ ቱሎ ተጓዘ ። ሰንሰለቱ እልወለቀለትም ። ቱሎ ምሲደርስ ቀያ ቀለም ያለው የእሥረኛ ልብስ አለበሱት ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ማንነቱን አጣ ። መጠሪያ ስሙ እንኳ ጐን ቫልጣ መሆኑ ቀርቶ ቁጥር 24,601 ሆነ ።

እሱ ከታሠረ በኋላ እህቱና ሰባት ልጆቿ ያለረዳት ቀሩ ። መሪ የላቸውም ። ደጋፊ የላቸውም ። መጠለያም የላቸውም ። ወዴት እንደባከኑ እንኳ አይታወቅም ። ምናልባት እየንዳንዳቸው እግራቸው ወደመራቸው ሳይሄዱ አልቀሩም ። የሠፈራቸው ሰውም ረሳቸው ። ከጊዜ በኋላ ጐን ቫልጣ እንኳ ረሳቸው ። ሆኖም ቱሎ ውስጥ አራት ዓመት ያህል ታሥሮ ከኖረ በኋላ አንድ ቀን ስለ እህቱ ወሬ ሰማ ። ጋሪስ ከተማ ውስጥ ፣ በዝሆን ድር ጐዳና ከሴን ሱፐሊስ አቅራቢያ ችግረኞች ከሚኖሩበት ቀበሌ እንደምትኖር ተነገረው። የመጨረሻ ልጅዋ ብቻ ከሷ ጋር ነበር ። የተቸገሩት ስድስቱ ከምን እንደደረሱ ሴላ ሰው ይቅርና እሷ ራሷ ማወቋ ያጠራጥራል ።

እህቱ በሳቦ ጐዳና ቁጥር 3 በሚገኝ ማተሚያ ቤት ትሠራ ስለነበረ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ከዚያ ትሄድ ነበር ። ከንጋቱ በ12 ሰዓት ከሥራ በታጣ መገኘት ነበረባት ። በማተሚያ ቤቱ ሕንጻ ውስጥ ትምህርት ቤትም ስላለ የሰባት ዓመት ዕድሜ ያለው ሕጻን ልጅዋ እዚያ ይማራል ። ይሁን እንጂ ት/ቤቱ የሚከፈተው በአንድ ሰዓት ስለሆነ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሚያው ላይ ይቆያል ። በተለይ በክረምት ወራት ብርዱ በጣም በሚከፋበት ጊዜ



@OLDBOOKSPDF

ለአንድ ሰዓት ሙሉ እውጭ መቆየት ተላልፎ አይደለም ። ሕጻኑ ልጅ እና ቱን ተከትሎ እንዳይገባ ሥሪ ያስፈታል ተብሎ ስለሚታሰብ አይፈቀድለ ትም ። ሚጻው ላይ ቱጭ ብሎ ያንገላጫል ። የማተሚያ ቤቱ ሠራተኞች በዚያ ሲያልፉ ያየታል ። አንዳንድ ጊዜ ከማንገላጀትም አልፎ እንትልፍ ይታኛል... ኩርምት ብሎ ።

ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ በማተማያ ቤቱ በተላላኪነት የምታገለ ግል አንዲት አሮጊት ሴትዮ ታገኝለት ነበር ። አንስተኛ ከፍሏ ወሎጥ ይዛው ትገባለች ። በከፍሏ ውስጥ የሣር ገብጓጊ ፣ የመፍተያ መሣሪያና ሁላት ወን በሮች አሉበት። ሕጻኑ ልጅ ከጥግ ሄዶ ይተኛል ፣ እንዲምቀው ከዚያ ትገኛ ከነበረችው ድመተ ታከኮ ። አንድ ሰዓት ሲደርስ ብቻ ተነስቶ ወደ ትምህ ርት ቤቱ ያመራ ነበር ። ግን ቫልግ ስለ እሁቱና ስለ ሕጻን ልጅዋ የሰማው ወሬ ይኸው ነበር ።

ከአራት ዓመታተ በኋላ ግን ቫልግ ከአሥር ቤቱ አመለጠ ። በማ ምለጡ ተማባር የአሰር ቤት ባለደረቦቹ ተባበሩት ። ለሁለት ቀናት ነጻ ሆኖ የትም ሲዋልል ቆየ ። ይሁን እንጂ ከአሁን አሁን እደገ ይሆናል ብሎ ይጨ ነት ነበር ። ገልመጥ ገልመጥ እያለ ዙርያ ገቡን ይመለከታል ። ድምጽ በሰማ ቱጥር ይደነግጣል ። መላ አካባቢውን ይጠራጠራል ። ጪሰ ሲወጣ ሲያይ ፣ ተላላፊ መንገደኛ ሲያጋጥመው ፣ የሚርመሀ ውሻ ወይም የሚጋልብ ፈረስ ድምጽ ሲሰማ ፣ እና ሰዓት ሲጮህ ይደናበራል ። አውራ ጉዳናው ፣ የእግር መንገዱ ፣ ጥሻው ፣ ይህ ሁሉ ያስደነግጠዋል ። ሲተኛም ያባንን ዋል ። ቀንም ሆኑ ልሊት ይኸው ነው ። ፍርሃት..... ድንጋጤ— ስጋት— ጥርጣሬ ።

በሁለተኛው ቀን ማታ ግን ቫልግ ታድኖ ተያዘ ። ለሠላሳ ስድስት ሰዓታት እህል ውሃ አልተመሰም ነበር ። የባህር ከፍሉ ፍርድ ቤተ በማም ለጥ መንጀሉ ተጨማሪ ሦስት ዓመት ፈርዶበት እሥራቱ እስከ ሰምንት ዓመት ተራዘመበት ። እሥር ቤቱ ውስጥ ስድስት ዓመት ዘቆየ በኋላ እን ደገና አመለጠ ። አንድ ቀን የእስረኞች ስም በሚጠራበት ሰዓት ከዚያ አልነበረም ። የእሥር ቤቱ ዘበኞች በእየአቅጣጫው ሲፈልጉት ውለው ያንኑ ቀን ማታ በመሠራት ላይ ከነበረ ከአንድ መርከብ ውስጥ ተደብቆ አገኙት ። እጁን ሳለመስጠት ዘበኞቹን ታገላቸው ። ነገር ግን አልሆነለ ትም ። ሰፀለተኛ ጊዜ በማምለጡና ዘበኞቹንም በመታገሉ ተጨማሪ የአ ምስት ዓመት እሥራት ተፈረደበት ። እንዲያውም ለሁለት ዓመታት ጊዜ በድርብ ሰንሰለት እንዲታሠር ተወሰነበት። ጠቅላላው የእስራቱ ጊዜ እስከ አስራ ሦስት ዓመት ተራዘመ ማለት ነው ። ይሁን እንጂ የእሥራቱ ዓመ ታት መራዘም ለማምለጥ ሙከራ ከማድረግ አላገደውምለአስር ዓመታት በወህኒ ቤት ከቆየ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ አመለጠ ። ወጥቶ ግን አልቀረም ። ታድኖ ታያዘ። እንደገና ሦስት ዓመት ተፈረደበት።የእሥራቱ ጊዜ በጠቅላ ላው አስራ ስድስት ዓመት ሆነ ። አስራ ሦስት ዓመታት ዘታሠረ በኋላ ለአራተኛ ጊዜ አመለጠ ። ከአራት ሰዓታት በኋላ እንደገና ተያዘ ። ለአራ ተኛ ጊዜ በማምለጡ አሁንም እንደገና ሦስት ዓመት ተፈረደበትና በጠ

@OLDBOOKSPDF

ቅላላው ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት ወህኒ ቤት ሲማቅቅ ኖረ ። በጥቅምት ወር 1815 ዓ. ም. ቅጣቱን ፈጽሞ ከወህኒ ቤት ተለቀቀ ። ዣን ቫልዣ እስር ቤት የገባው በ1796 ዓ. ም. ነበር ፤ የመስኮት መስታወት ሰብሮ አንድ ዳቦ በመሥረቁ...ሰባቱ የእህቱ ልጆች በመራባቸው ምክንያት ።

በረሀብ ምክንያት የዳቦ ስርቆት ወንጀል የሚፈጸመው በፈረንሳይ አገር ብቻ አይደለም ። በእንግሊዝም አገር ተመሳሳይ ሁኔታ አለ ። በሎንዶን ከሚፈጸሙ አምስት የስርቆት ወንጀሎች አራቱ መነሾአቸው ረሀብ እንደሆነ የሎንዶን እስታቲስቲክ ያረጋግጣል ።

ዣን ቫልዣ ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት ታስሮ ፣ ከባድ የጉልበት ሥራ ሲሠራ ፣ ይህም ማለት ከባርነት ባልተሻለ ሁኔታ ከባድ ጀልባ ሲቀዝፍ ኖሮ ከእስር ቤት ሲለቀቅ መሳ መንፈሱ ጨለመበት ፤ የተስፋ ጭላንጭል ለማየት ተሳነው ።

— 7 —

ዣን ቫልዣ የስርቆት ወንጀል በፈጸመበት ወቅት ማይም ነበር ። ይሁን እንጂ በተፈጥሮው የሚያስብና የሚያሰላስል ሰው ነበር ። በእሥር ቤት በነበረባቸው ዓመታት በዱላ ቢቀጠቀጥም ፣ በሰንሰለት ቢታሰርም ፣ ለቀን ሐሩር ቢጋለጥም ፣ መከራና ስቃይ ቢያይም ፣ ይህ ሁሉ የተፈጥሮ እውቀቱን ስላዳበረለት በአእምሮው ይመራመር ነበር ።

ዣን ቫልዣ ሳያጠፋ እንዳልተቀጣ፣የሚያስቀጣም ጥፋት እንደሠራ ያውቅ ነበር ። የሠረቀውን ዳቦ በመስረቅ ፈንታ ቢለምን ኖሮ ሊሰጠው ይችል እንደነበረም ያውቅ ነበር ። ደግሞም ረሀብ ጊዜ የማይሰጥ ነገር ቢሆንም በእውነተኛ ረሀብ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ነው ። ምክንያቱም ሰው የሆነ ፍጡር ለሞት ከመቃረቡ በፊት ከፍተኛ የሆነ የአካልም ሆነ የሞራል መከራና ስቃይ ለመቋቋም ችሎታ አለው ። ስለዚህ ማንኛውም ሰው መታገስ አለበት ። ዣን ቫልዣና ሕጻናቱ ልጆችም ረሀብ ቢሞረሙ ራቸውም ቅሉ መታገስ ይገባቸው ቸነበር ። ዣን ቫልዣ ግን አልታገሰም ፣ የስርቆትን ወንጀል ፈጸመ ። ወንጀሉም በሕብረተሰቡ ዘንድ የማይፈቀድ በመሆኑ ሊያስቀጣው ቻለ ።

ሆኖም ሳለ ጉዳዩ ያለ ጥያቄ የሚታለፍ አይደለም ። ለመሆኑ ጥፋተኛው እሱ ብቻ ነበር ወይስ ዣን ቫልዣ ዳቦ በሰረቀበት ወቅት ሥራ አልባ እንደነበረና ተርቦም እንደነበረ ለአንድ አፍታ እንኳ መዘንጋት አይገባውም ። የተራበ ሰው ወደ ስርቆት ወንጀል ይገፋፋል ፣ እሱም ተገፋፍቶ ሠረቀ ። በወንጀሉም ተቀጣ ። ነገር ግን ቅጣቱ ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ ነበር ወይስ እሱ ከፈጸመው ወንጀልና ሕግ ከበየነበት ቅጣት ሕጉ ወይም ሕብረተሰቡ በሱ ብዳል? እርሱ ሕብረ[illegible] [illegible]

@OLDBOOKSPDF

ላይ የፈጸመው ወንጀል አያይልም? ፍርዱ ወንጀሉን እንዳልተፈጸመ አላ ደረገውምን እውነተኛው በዳይ ዣን ቫልዣ በመሆኑ ፈንታ ሕጉ ራሱ አል ሆነምን ጨቋኙን ታያለህ ሕግተጨቋኙና ደካማው ዣን ቫልዣ አልሆኑምን ጭቆናው ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት አልቆየምን

ኧረ ለመሆኑ ሕብረተሰቡ ግለሰቡን ለመጨቆን መብት አለው ወይ? ሕብረተሰቡ ምን ያህል ነው አርቆ የሚያየው? በአንድ በኩል ለግለሰቡ ሥራ መንሳት ፡ በሌላ በኩል ያንኑ ግለሰብ በወንጀልና ቢቅጣት ስም መጨ ቆን አግባብ ነው? ሕብረተሰቡ ሥራ አጦችንና ችግረኞችን መጨቆን ይገ ባዋል ወይንስ እነሱን መርዳት?

ዣን ቫልዣ እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች በሀሳቡ ሳያወጣና ሳያወርዳቸው አላለፈም ። አውጥቶ ባወረዳቸውም ቁጥር ሕብረተሰቡን ሳያወግዝ አል ቀረም። ከማውገዝም አልፎ ሕብረተሰቡን ከአንጀቱ ይጠላ ጀመር ።

«የስቃዬ መነሾ ሕብረተሰቡ ነው..... አንድ ቀን ሕብረተሰቡን አፋረ ደዋለሁ.....እኔ በሕብረተሰቡ ላይ ያደረስኩት ጥፋት ሕብረተሰቡ በእኔ ላይ ካደረሰው ጥፋት ጋር ፈጽሞ አይመጣጠንም..... እኔ የሠራሁት ጥፋት ከተ በየነበኝ ቅጣት ጋር ሲመዛዘን እንደሰማይና ምድር የተራራቁ ሆነው ይታዩኛል» በማለት ክፍ ያለ ቁጣና ምሬት አደረበት ።

ዣን ቫልዣ በፍትህ ስም የተፈጸመበት በደል እንጂ ሌላ ነገር አል ታይህ አለው ። ከሰዎች ጋር መሆን አስመረረው ። በሕጻንነቱ ዘመን እናቱና እህቱ ካሳዩት አዛኝነት በስተቀር ደግ የሞለት ሰው አልታይህ አለው ። በሕይወቱ ያየው ስቃይና መከራ መላው የሰው ልጅ ሕይወት ብትግል ላይ የተመሠረተ መሆኑን አስተማሩት። ይህንኑ ትግል ለመቋቋም በእጁ የነበረው መሣሪያ ጥላቻ ብቻ ነበር ። በእሥር ቤት በነበረባቸው ዓመታትም ሆነ ከተፈታ በኋላ ይህንን የጥላቻ ስሜቱን በይበልጥ ሊስለው ቆረጠ ። ዣን ቫልዣ የሚጠላው ሕብረተሰቡን ብቻ አልነበረም ። ሕብ ረተሰቡን የፈጠረውን እግዚአብሔርንም ጭምር ነበር ።

ዣን ቫልዣ በእሥር ቤት በነበረባቸው ዓመታት ተስፋ ቢስ ሰው ወጥቶት እንደነበረ ተገልጿል ። ነገር ግን ተስፋ ቢስ መሆኑን እሱ ራሱ ያውቅ ነበር ወይ? ሞራላዊ መከራ ያደረሱበትን ነገሮች በዝርዝር ያውቃ ቸው ነበር ወይ? በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በአእምሮው ተነስተው የወደ ቁት ሃሳቦችና ከዚህ ከተስፋ ቢስነት ያደረሱት ሁኔታዎች ምን ምን እንደ ሆኑ ተግንዝቦአቸው ነበር ይሆን ? በሕሊናው ውስጥ የነበሩትን ሁሉ ያውቃቸው ኖሯል? ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ያዳግታል ። ዣን ቫልዣ በጥልህ ለማሰብ የሚችል ሰው አልነበረም ። አንዳንድ ጊዜ ምን እንደሚሰማው ሰማወቅ እንኳ ይሳነው ነበር ። በጥልመት ውስጥ ( ሚ ኖር ፤ በጥልመት ውስጥ የሚሰቃይ ፡ በጥልመት ውስጥ ሆኖ ሁሉንም የሚ ጠላ ሰው ነበር ። እንደ ዓይነ ስውርና በሕልም ውስጥ እንዳለ ሰው በዚህ


@OLDBOOKSPDF

ዋልመት ውስጥ በጻበሳ ይጓዝ ነበር ። አልፎ አልፎ ብቻ ስላለበተ አዘቅት በድንጉት ይገነዘብ ነበር ፤ በመብረቅ ብልጭታ እንደሚታይ ነገር ።

ያ ብልጭታ ታይቶት ወዲያውኑ ድርግም ይላል ። ጐን ቫልጣ እንደ ገና ከጭለማ አዘቅት ውስጥ ይሰጥማል ። ያለበትን ሁኔታ ሳይገነዘብ ይቀ ራል ። በዚህ ሁኔታ የሚሰቃይ ሰው ቀስ በቀስ ወደ አውሬነት ባህርይ መስ ወጡ አይቀርም ።

ይህ እውነት ስለመሆኑ ጐን ቫልጣ ለሚምለጥ ያደረጋቸውን ሙከ ራዎች ማስታወስ ይበቃል።አምልጦ በሬደ ቁጥር ይያዛል ። ከዚያም በኋላ የስቃዩ ጊዜ ይራዘምበታል ። ይሁን እንጂ ተይዣለሁ።ቅጣቱ ከብዶብኛል ፡ ስለዚህ እንደገና ለማምለጥ ሙሞክር አያቅጣኝም ያለበት ጊዜ የለም ። ድርጊቱ በክልል ውስጥ ተወስኖ ከሚኖር አውሬ ድርጊት ጋር ይመሳሰል ነበር ። የክልሉ በር ሲከፈት አውሬው ለማምለጥ ይሞክራል እንጂ ምን ይደርስብኝ ይሆን ብሎ አያስብም ። ማንኛውም አውሬ በስሜቱ እንጂ በአእምሮው አይመራም ። የጐን ቫልጣም ድርጊት ተመሳሳይ ነበር ።

በቱሎ አስር ቤት ከነበሩት ወንጀለኞች መሐከል አንዱ ጐን ቫልጣ ጉልበተኛ ሰው አንድ እንኳ አልነበረም ። በጉልበቱም የማይ ፈጽመው የሥራ ዓይነት አልነበረም ። አራት ሰው ሰመሸነም በቂ ጉልበት ነበረው ። ከባድ ሸክም ሲኖር እሱ ይጠራል ። አስፈላጊ ከሆነ ጊዜ በመሣ ሪያ ብቻ ሊነሱ የሚችሉትን ከብደቶች እሱ በእጁ ያነሳቸዋል ። በዚህ ምክ ንያት የአስር ቤት ባልደረቦቹ «ጀነ አስከሩ» ወይም የነብደት ሚንሻ ብለው ይጠሩት ነበር ።

ጎደሎኛ ከመሆኑም በላይ ሰውነቱ በቀላሉ ይታዘዝለት ነበር ። ግድ ግዳ ላይ ተንቀሳቅ መውጣትም ይችልበት ነበር ። ትንሽ ጠያጣና የእግር ማጣረፊያ ካገኘ እየተንቀሳቀሰ እስከ ሦስተኛ ፎቅ ድረስ ፡ ከዚያም አልፎ እስከ አስር ቤቱ ጣራ ድረስ ይወጣ ነበር ።

ጐን ቫልጣ ብዙ አይናገርም።ሳቅ የሚባል ነገር መኖሩንም አረሳ ቶታል።ስሜቱ በንዴት ሲቀሰቀስበት ግን ወንጀለኞች ናሚሉት ዓይነት ሳቅ ይስታል..... የዲያብሎስ ሳቅ ።

ተፈጥሮው ያልተሟላ፣ አእምሮውም የተከላሸ እንደመሆኑ መጠን አንዳች ከይሲ ነገር ብሹብሹ ብሎ ይታየዋል ። ሕግ ፣ የተባባ አስተያየት ፣ ስዎች ፣ የሰዎች ሥራ ፣ እና የመሳሰሉት ሁሉ በአእምሮው ውስጥ ብሹብሹ ብለው ይታዩታል።ያስፈሩታልም። ቂጣውንና ምሬቱን ይቀስቅሱበታል። አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ብቻ በጉልህ ይታዩታል ። ለምሳሌ ፡ የወህኒ ቤቱ የአምሳ አለቃና የሚደባደብበት ቆመጥ..... ፖሊሱና የታጠቀው ሰይፍ..... ሲቀ ዳዳሱና ቆቡ..... ንጉሠ ነገሥቱና ዘውዱ.....


@OLDBOOKSPDF

እነዚህ ነገሮች በእውነም ሆነ በምናቡ በጉልህ በታዩት ቁጥር የሚናርበትን የጥልመት ሕይወት የባሰውን ያጠልሙበታል ። ይጫነ ታል ። መከራውንም ያከብዱበታል ።

ጎርን ቫልገር በዚህ ሁኔታ ሆኖ ያስባል ፥ ያሰላስላል ፤ በወፍጮና በመጅ መሐከል እንዳለ የእህል ዘር ሆኖ ። የሚያስበውን አብራርቶ ሰመ ግለጽ ይሳነዋል ።

አንዳንድ ጊዜ ከባርነት ያልተሻለ የጉልበት ሥራ በሚሠራበት ወቅት ፍዝዝ ብሎ ይቀራል ። በሱ ላይ የደረሰው ሁሉ ትርጉም የለሽ ይሆንበታል ። በዙርያው ያለው ሁሉ እንቆቅልሽ መስሎ ይታየዋል ። «ሕልም ነው» ይላል ራሱ ለራሱ ።

የተፈጥሮ ትርዒት አይታየውም ። ጨለማ ብራ ቀኖች፥ ግልጽ ስግይ ፥ ንጋት..... እነዚህ ሁሉ ለጎርን ቫልገር እንዳልነበሩ ነበሩ ለማለት ይቻላል ።

ባጭሩ ፥ ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት ታስሮ በመከራና በስቃይ የኖረው ጎን ቫልገር ሁለት ዓይነት ክፉ ሥራ የሚሠራ ሰው ወጣው ። እንደኛ ፥ ሲያስብና ሳያሰላስል እንዴ ጉር አውሬ በድንገት የሚያከናውነው ክፉ ሥራ ፤ ሁለተኛ ፥ አስቦ ፥ ሆን ብሎ ፥ ከራሱ ጋር ተማግቶ የሚፈጽመው ክፉ ሥራ ። የመጀመሪያው ዓይነት ክፉ ሥራ ከበቀል ስሜት የመነጨ ነበር ፤ ሁለተኛውም ከውስጣዊ ቁጣና ምሬት የመነጨ ነበር ። ሁለተኛውን ዓይነት ክፉ ሥራ በሚፈጽምበት ጊዜ በትድሚያ በጉዳዩ ያስብበታል ። አስቦም እንዲፈጽመው ቁርጥ ሀሳብ ያደርጋል ። ቅጥሎም ሲይሰለችና መዶረግ ያለበትን ሁሉ በማድረግ ከጥዳሚ ያደርሰዋል ። ምንም ጥሩት ባለ ሠሩበት ሰዎች ላይ እንኳ ክፋት ሊሠራባቸው የሚያነሳሳው ኃይል ነበር ። የዚህ ሁሉ መነሾው ለሰዎች ሕግ የነበረው ጥላቻ ነበር ። ይህ ዓይነቱ ጥላቻ በጊዜ ሀልታረመ በሰላቀር ወደ ሕብረተሰብ ጥላቻ ፥ ቀጥሎም ወደ ሰው ልጅ ጥላቻ ያሸጋግረል ። በዚህም ሳይገታ ወደመላው ስነ ፍጥረት ጥላቻ ያሸጋግራል። ስለሆነም ለጎርን ቫልገር በተሰጠው የመታወቂያ ወረቀት ላይ «በጣም አደገኛ ሰው ነው» ተብሎ የተጻፈበት ያለ ምክንያት አልነበረም ።

ዓመት አልፎ ዓመት በላታካ ቁጥር የጎን ቫልገ ውስጣዊ ሕይወት እየደረቀ ሄደ። ውስጣዊ ሕይወት ሲደርቅ ዓይንም ይደርቃል።ጎን ቫልገ ከእስር ቤት በወጣበት ወቅት ለአለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት ዓይኑ እምባ አፍልቆ አያውቅም ነበር ።



አንድ ሰው ከመርከብ ሾልኮ ባህር ላይ ደወድቃል እንበል ። መርከቡ አይቆምም ። ጉዞውን ይቀጥላል ።

@OLDBOOKSPDF

ሰውዬው ብቅ ጥልት ይላል ። ሰጥሞ ይገባል ። ትመልሰ ወደ ባሕሩ ወለል ይወጣል። ይጣራል ። ርዳታ ለሚሻንት እጁን ይዘረጋል ። የሚረዳው ሆነ የሚለማው የለም ። መርከቡ በነፋሱ ግፊት እየተወሰወሰ ጉዞውን ይቀጥላል ። ሙርከበኛቹና ተጓጉዞቹ ሽልኩ የወደቀውን ሰው እያዩትም ። ከባሕሩ ሞገድ ባሻገር የሚታየው ራሱ ከገንብ አይበልጥም ። ይጮሣል ሰውዬው ። መርከቡ ግን ይበልጥ እየራቀ ይሄዳል ። ሰውዬውም በዓይኑ ያከተለዋል ። ልቡ ይክዳዋል ።

ከእጭር ጊዜ በፊት ሰውዬው ከተጓጉዞቹ አንዱ ነበር ። እንደሌሎቹ ሁሉ በመርከቡ ውስጥ ይንሸራሸር ነበር ። አሁን ግን ሰፊው ባሕር ላይ ብቻውን ነው ። የባሀሩ ሞገድ ያንገላታዋል ። ሞገዱ በላዩ ላይ ተከምሮ ሲያስጥመው የጭስማ ግዴል ይታየዋል ። የባህር አረም ይጠመጠምበታል ። በመስጠም ላይ መሆኑን ይገነዘባል ። አንደኛው ሞገድ እንደ ኳስ ይወረውረዋል ። ሌላው ሞገድ እንደ ኳስ ይቀበለዋል ። ሳይወድ የባሀሩን ውሃ ጉርጉጭ ያያርገዋል ። ባህሩ እንደ አጥቂ ጠላት ያጠቃዋል ። ሰውዬው ግን በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሞገዱን ይታገለዋል ፤ አልሰጥምም በማለት ። ለመዋኘትና በባህሩ ወለል ላይ ለመቆየት የቻለውን ጥረት ያደርጋል ።

መርከቡ ርቆ ሄዶ ከአድማስ ክልል ይደርሳል ። መርከቡም እንደ ሰውዬው ገፀምብ ያክሳል ።

ነፋሱ አውንም ይጋረፋል ። የባህሩ ወሃ አረፋ ይደፍቃል ። ሞገዱ ሰውዬውን አሁንም እንደ ኳስ ደ ጫወትበታል ። ሰውዬው ዓይኑን አቅንቶ ወደሰማይ ሲመለከት አመድ ከመስለ ዳመናና ከአእዋፍ በስተኛር ሌላ ነገር አይታየውም። ባህሩ ተቆጥቷል።ሰውዬው በባዕር ላይ ደገኛል።የባህሩ ቁጣ ያስታየዋል ። እንግዳ የሆነ ድምጽ ይሰማል፣ ከሌላ ዓለም የሚመጣ የሚመስል ድምጽ ።

ጊዜው እየጨለመ ሄደ ። ሰውዬው ለብዙ ሰዓታት ሲዋኝ ፣ ሲታገል ቆየ ። እጅ እግሩ እየላሰ ሄደ ። መርከቡ ከዓይኑ በጥፌም ተሰወረ ።

በዙርያ ገቡ ሰው የለም ። እግዚአብሔር ወዴት አለ? እንደገና ይጮህ ጀመር ሰውዬው ፤ ወንድሞች ...! እርዱኝ ...» እያለ ። የሚሰማው ግን የለም ።

ጭለማ ፣ ጉም ፣ ብቸኝነት ፣ የባህሩ ጥርምርም ታ፣እነዚህ ሁሉ ይከቡታል ። ያዋክቡታል ። ወሰላ አካሉ መትት ይላል ። በጥርዎት ይዋጣል ። ከሥሩ ጥልቁት ብቻ፡ አለ ። ደግፎ የሚይዘው ነገር የለም ። በዚያ ጥልቀት ውስጥ ፣ በዚያ አዘቅት ውስጥ ሙት አካሉ ምን እንደሚደርስበት ያስባል ። አጥንቱ ሰርስሮ የሚገባው ቅዝቃዜ ሰውነቱን በድን ያደርገበታል ። እጆቹ ይኮማተራሉ ።

ሰውዬው ይሸነፋል ። መታገሉን ያቆማል ። ባህሩ ያሰጥመዋል ። ወዴው የሰው ልጅ ፍጥረት ጉዳየ፣ ወዴው የሰው ልጅ እልቂት፣ የሰው

@OLDBOOKSPDF

ሕግ በሰፊው ባህር ይመሰላል ። ይህ ባህር ስንቱን በልቶአል! ስንቱን ይበላል! አወይ ውድቀት! አወይ እርዳታ ማጣት! አወይ የሞራል ድቀት! የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ወንጀለኞች የሚሰጥሙበት ባህር ነው ፥ መከረኞች ፍዳቸውን የሚያዩበት ። እነዚህን መከረኞች ከዚህ አዘቅት የሚያወጣቸው ፥ የሚረዳቸው ማን አለ?

— 9 —

ከባርነት ሥራ የሚገላገልበት ሰዓት ደርሶ «ነጻ ሆነሃል» ተብሎ ሲነገረው ግን ቫልጥ ለማመን ቸገረው ። አዲስ የሕይወት ተስፋ በልቡ ውስጥ ተፈጠረ ። ተስፋው ግን ሰረጅም ጊዜ በልቡ አልቆየም ። ምንም እንኳ ነጻ ሆነሃል ተብሎ ቢነገረውም ቢጫውን የመታወቂያ ወረቀት መያዝ እስከለበት ድረስ እውነተኛ ነጻነት ለማግኘት እንደማይችል ተገነዘበ ። በዚህም ምክንያት ምሬት አደረበት ።

የሆነ ሆኖ ለአስራ ዘጠኝ ዓመታት የባርነት ሥራ ሲሠራ በቆየበት ዘመን ምን ያህል ገንዘብ መስራል እንደሚገባው ያሰላ ጀመር ። መጨው ሠባ አንድ ፍራንክ መሆን አለበት ሰሌ አሰበ ። ይሁን እንጂ የዘነጋው ነገር ነበር ። እሁድ እሁድና በበዓላት ቀናት አስሥረኞች ሥራ እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም ነበር ፥ ገንዘብም አይታሰብላቸውም ነበር ። ስለሆነም የሚከፈለው ገንዘብ እሱ ካሰበው በ80 ፍራንክ ያህል ያነሰ ነበር ። በተጨማሪም በልዩ ልዩ ምክንያት ተቆራጭ የሚሆን ሂሣብ ነበር ። ስለዚህ ከእሥር ቤት ሲለቀቅ ተቆጥሮ የተሰጠው የጉልበት ዋጋ 109 ፍራንክ ከ15 ሰ· ብቻ ነበር ። የተበዘበዘ መስሎ ታየው ።

ነጻ በተለቀቀ ማግሥት ግራስ በተባለ ሥፍራ ከመጠጥ ፋብሪካው ፊት ለፊት ሰዎች ዕቃ ሲያወርዱ አየ ። እንደነሱው ዕቃ እንዲያወርድ እንዲፈቀድለት ለመነ ። ብዙ ሥራ ስለነበረ ተፈቀደለት ። ብርቱ ሠራተኛ ስለነበረ ቀጣሪው ሳይደሰትበት አልቀረም ። ግን ቫልጥ በሥራው ላይ እያለ አንድ ተላላፊ ፖሊስ አየውና መታወቂያውን እንዲያሳየው ጠየቀው ። ቢጫውን ወረቀት አሳየውና ሥራውን ቀጠለ ።

ቀደም ብሎ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ምን ያህል እንደሚከፈል ጠይቆ 30ሰ· መሆኑን ተረድቶ ነበር ። ግን ቫልጥ በበነጋታው ጉዞውን መቀጠል ስለነበረበት ያንኑ ቀን ማታ ወደ አሠሪው ሔዶ ሂሳቡ እንዲከፈለው ጠየቀ ። አሠሪው አንዳችም ቃል ሳይናገር 15 ሱ አውጥቶ ከፈለው ። ግን ቫልጥ አግባብ አይደለም በማለት ተከራከረው ። «ላንተ 15ሱ በቂህ ነው» አለው አሠሪው ። ግን ቫልጥ ግን አይሆንም ብሎ አሁንም ተከራከረው ። አሠሪውም አተኩሮ ተመለከተውና ፥ «እስር ቤት የሚባል ነገር እንዳለ አትዘንጋ!» ሲል አስፈራራው ።

— 92 —

@OLDBOOKSPDF

ግን ቫልግ እንደገና ተበዘበዝኩ ሲል አሰበ ። ቀደም ብሎ የተበዘበ
ዘው በሕብረተሰቡና በመንግሥት ነበር ። አሁን ግን የተበዘበዘው በግለሰብ
ሆነ ።

ነጻነቱ ጐደሎ ሆኖ ታየው ። ጐደሎም ነበር ። ከእስር ቤት ቢለቀቅም
እንኳ ከሌሎች ነጻ ሰዎች በእኩል ደረጃ አይታይም ነበር ። ለሌሎች ሠራ
ተኞች 30 ሱ የጉልበት ዋጋ ሲከፈላቸው ለሱ 15 ሱ የተከፈለው ለዚሁ
ነበር ።

— 10 —

ግን ቫልግ አልጋው በጣም ተመቸቶት እንቅልፉን ሲለጥጥ ቆየና
ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሲሆን የካቴድራሉ ሰዓት ተደውሎ ከእንቅልፉ ቀሰ
ቀሰው ። ከአራት ሰዓት በላይ ነበር በእንቅልፍ ያሳለፈው ጊዜ ። ድካሙም
አልፎለት ነበር ። ዓይኑን ከፍቶ ቢመለከት ዙርያው ጭልማ ሆነበት ። እን
ደገና ለመተኛት ፈልጎ ዓይኖቹን ከደናቸው ። እንቅልፍ ግን አልመጣ
አለው ። በዚህ ጊዜ ያስብ ጀመር ። የቀድሞ ኑሮው ትዝ አለው ። ያሁን
ሁኔታውም በአይነ ህሊናው ታየው ። የቀድሞውና የአሁኑ ሁኔታው ተደ
በላለቁበት ። ቀጥሎም ሰለሌላ ሌላ ነገር ያስብ ጀመር ። ከሁሉም ይልቅ
በአእምሮው ጐልቶ የታየው ስድስቱ የብር ሹካዎቹና ማንኪያዎች ነበሩ ።
የብር ጭልፋውም እንዲሁ ።

እነዚህ የብር ዕቃዎች ከተኛበት ከፍቱ ሩቅ አልነበሩም ። ማጸዳ
ሚያር በአቡነ መኝታ ቤት ውስጥ ከኤልጋው ራስጌ ባለው ቁም ሳጥን
ውስጥ ስትጨምረ ቸው ልብ ብሎ አይቷቸል ። እነዚህ ዕቃዎች ከፍተኛ ዋጋ
የሚያወጡ ሳቸው ። ጭልፋው ብቻ ቢሸጥ ከ200 ፍራንክ ያላነሰ ገንዘብ
ያወጣል ። ለ19 ዓመታት የጉልበት ሥራ ለሠራበት የተከፈለው ዋጋ
የዚህ ማማሽ ነበር ።

ግን ቫልግ በሃሳቡ ያለውን ለመቁረጥ አቅቶት ከህሊናው ጋር ይታ
ገል ጀመር ። እንዲሁ ሲታገል ሳለ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ሆነ ። ከመኝታው ብድ
ስቶ አልጋው ላይ ቁጭ አለ ። እግሮቹን ከአልጋው ጠርዝ ወደ ምድር አን
ጠለጠላቸውና ገዘም ብሎ ቆየ ። በዚህ ሰዓት እንዲህ ባለ ሁኔታ ጭልማው
ውስጥ ብቻውን መቀመጡ ለደግ አልነበረም ። ቀጥሎም ጫማዎቹን አው
ልቆ ከሥር በነበረ ምንጣፍ ላይ ቀስ ብሎ አኖራቸው ። እንደገናም ከክባድ
ሃሳብ ውለጥ ገባ ። የገዛ ሃሳቡ አእምሮውን ተጫጫነው ። በዚህ ሁኔታ
ኢየለ በድንገት ብረቱ የተባለውን መንደልኛ አስታወሰ።ቱሎ ውስጥ አብ
ረው ነበር የታሰሩት ። የብረቱ የሰሪው ጥበጣብ በአእምሮው ጐልቶ
ታየው ።

ሰዓቱ እንደገና ጮኸ ። የሰዓቱ ጩኸት ዣበልኽ....! በል....ክ የሚ
ሰው መሰለው ።



@OLDBOOKSPDF

ዝንሱዩ ቆመ ፣ ልቡ አሁንም እያመነታ ። ድምጽ መኖር አለመኖሩን ዕማረጋገጥ ጀርውን አቱም ያዳምጥ ገባ ። አንዴችም ድምጽ አልነበረም ። ይህንን ካረጋገጠ በኋላ በቀጥታ ወደ መስኮቱ አመራ ። ሌሲቱ እስከዚህም አልጨለመም ነበር ። ሙሉ ጨረቃ በሰማይ ላይ ነበር ። በንፋስ የሚነዳ ጸመና በጨረቃው ገጽ ላይ በሚያልፍበት ጊዜ ጨለምለም ይል ነበር ። ጸመናው ከለፊ በኋላ ግን ውጪም ውስጡም አንደጣና ይበራ ነበር ።

ግን ቫልግ በመስኮቱ አጠገብ ቆሞ መስኮቱን አስተዋለው ። መስኮቱ ለመከላከያ የሚሆን ዘርዛራ ብረት አልነበረውም ። ወደ ውጭ የሚከፈት ዓይነት ነበር ። ከፊት ሲያደርገው ቀዝቃዛ አየር ስለገባ መልሶ ዘጋው ። የአትክልቱንም ቦታ ደህና አድርጎ አስተዋለው ። ኖራ በተቀባና አጠር ባለ ግምብ የተከበበ ነበር ። ከዚያ ዘልሎ ለመውጣት አስቸጋሪ አልነበረም ።

ግን ቫልግ ይህንን ሁሉ ካስተዋለ በኋላ ያሰበውን ለማድረግ ቆርጦ የንዝ ከረጢቱን ካኖረበት ሥፍራ ሄድ ብሎ ከፈተው ። ከውስጡ አንዴች ነገር ፈላልጎ አወጣና አልጋው ላይ አስቀመጠው ። ጫማዎቹን አንስቶ ከሱ ውስጥ ጨመራቸው ። የንዝ ከረጢቱን መልሶ ዘጋውና አንስቶ ትከሻው ላይ አኖረው ። ቆቡን ደፋና ወደ ዓይኑ ዝቅ አደረገው ። ዘንጉን አንቡቱ መስኮቱን አስደግፎ አቆመው ። ከዚያም በኋላ ወደ አልጋው ተመልሶ በላዩ ላይ ያስቀመጠውን ዕቃ አንሰቶ ያዘው ። እጭር የብረት ዱላ የመሰለ ነበር ፤ አንደኛው ጫፉ ሹል የሆነ ።

በሞን ብርሃን ቢታይ ኖሮ ምናልባት የማዕድን ሠራተኞች የሚጠቀሙበት የሻማ መቅረዝ ነው ባሰኝ ነበር ። በዚያን ጊዜ በቱሉ አካባቢ የነበራ የሕግ አስረኞች ድንጋይ ከከርሰ ምድር ያወጡ ነበር ። የማዕድን አውጪዎች መሣሪያም ይሰጣቸው ነበር ። እነዚህ ማዕድን አውጪዎች የሚጠቀሙበት መቅረዝ ከባድ ብረት ሆኖ አንድ ጫፉ የሾለ ነበር ፣ መቅረዙ በድንጋይ ውስጥ እንዲሰካ ያመች ዘንድ ።

ግን ቫልግ ይህንን መሣሪያ በቀኝ እጁ ይዞ ትንፋሹን አጥፍቶ ቀስ ብሎ እየተራመደ አቡኑ ወደተኙበት ክፍል አመራ ። ከዚያ ሲደርስ በሩ ገርበብ ብሎ አገኘው ። አቡኑ ሳያዘጉት ነበር የተኙት ።



ግን ቫልግ ቆም ብሎ አዳመጠ ። ምንም ድምጽ የለም ። በሩን ቀስ ብሎ ገፋ አደረገው ፤ ወደቤት ውስጥ ለመግባት እንደፈሰገች ድመት ። በሩ ትንሽ ከፊት አሰሰት ።



@OLDBOOKSPDF

ለእጭር ጊዜ ዝም ብሎ ቆመና እንደገና ገፋ አደረገው ። በሩ አሀንም በይበልጥ ተከፈተ ። ይሁን እንጂ ከዚያ ይበልጥ እንዳይከፈት ከውስጥ በኩል የነበረ አንድ አነስተኛ ጠረጴዛ አገደው ። ግን ቫልገር ግን በዚህ አላቆመም ። በሩን መልሶ ገፋ አደረገው ። ግጠፊያው ቅባት አንሶት ኖሮ በሩ በዚህ ጊዜ ሲጢጥ አለ ።

ግን ቫልገር ከድንጋጤ የተነሳ ይብረከረክ ጀመር ። የግጠፊያው ሲጥሲጥታ በአእምሮው ውስጥ ያቃጭልበት ጀመር ። እሱን ለማስደነገ የሚጮህ ሕያው ነገር መስለው ። እስካሁን ድረስ በጣቱ ነበር የሚራመደው ። አሁን ግን እየቦንቀጠቀጠ በሙሉ እግሩ ቆመ ። በሩን መግፋቱም ተወው ። በደም ሥሩ ውስጥ እንዳች እንደመጮሻ የሚመታው ነገር ያለ መስሎ ተሰማው ። ትንፋሹም ከሞሻ ጭንጥሉ እንደሚወጣ ነፋስ የሚጮህ መሰለው ። የግጠፊያው ሲጥሲጥታ መላ ቤቱን ሳያነቃው በመቅረቱ ተገረመ ። በሃሳቡም ውስጥ ብዙ ነገሮች ይታዩት ጀመር ። እቡኑ ሲነቁ— ሁለቱ ቤቶች እሱ እሱ ብለው ሲጮሁ— የአካባቢው ነዋሪዎች ጩኸታቸውን ሰምተው ሰእርዳታ ሲደርሱላቸው— ፖሊሶችም መጥተው ሲይዙት—

ለጊዜው በዚህ ሁኔታ ሐውልት ሆኖ ቀረ ። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ አልደፈረም ። በርከት ያሉ ደቂቃዎች ካለፉ በኋላ ግን በትክክለኛው ቦር ቀስ ብሎ ወደ ውስጥ ተመለከተ ። ጀሮውንም አቁሞ አዳመጠ ። ነገር ግን ከውስጥ አንዳችም እንቅስቃሴ የለም ።

አፍይታ ተሰምቶት ያሰበውን በቶሎ ለማጠናቀቅ ቁርጥ ሀሳብ አድርጎ አንድ እርምጃ ሂድ ብሎ ከፍሉ ውስጥ ገባ ። ምንኒታቸው ያላወቃቸው ዕቃዎች ብዥብዥ ብለው ይታዩት ጀመር ። ጠረጴዛው ላይ የተበተኑ ወረቀቶች..... የተጠረገ ሱክ ወረቀቶች— ግርምቡድ ብጤ ላይ የተከመሩ መጻሕፍት— ልብስ የተቆለለበትና እጅ ማሣረፊያ ያለው መቀመጫ— መን በርከኪያ—

ግን ቫልገር ከአንጸባራቂ ዕቃ ጋር እንዳይጋጭ እያፈራ በጥንቃቄ ይራመድ ጀመር ። እቡኑ በእንቅልፍ ልባቸው ሲተነፍሱ ይሰማቸዋል ። ሳያስበው ከአልጋቸው አጠገብ ስለደረሰ በድንገት ቆም አለ ።

ቀደም ብሎ ሰማዩ በዳመና ተከድኖ ነበር ። ግን ቫልገር ከእቡኑ አልጋ አጠገብ ደርሶ ቆም ሲል ግን ዳመናው ተከፍሎ የጨረቃ ብርሃን በመስኮቱ ገብቶ የእቡኑን ፊት አበራው ። እቡኑ የሰላም እንቅልፍ ተኝተው ነበር ። ጊዜው በራድ ስለነበረ ልብሳቸውን እንደለበሱ ነበር የተኙት ። በላያቸው ላይ ቡናማ ተሉም ያለው የሱፍ ብርድልብስ ደርበዋል ። ሞንትሳታቸው ትራሱ ላይ ወደ ኋላ ዘንበል ብሏል ። እጃቸው አሊጋው ጠርዝ ላይ ተንጠለጥሏል ። በጣታቸው ላይ የእቡን ቀለበት አድርገዋል ። በፊታቸው ላይ ርካታ ፣ ተስፋ ፣ ደስታ ይንበባል ። እንዲያውም ፊታቸው የደስታ ብርሃን የሚፈነጥቅ ይመስላል ።

@OLDBOOKSPDF

በሰማይ ያለው ጨረቃ ፥ ከውጭ ያለው የኢትክልት ቦታ ፣ በቤቱ ውስጥ ያለው ጸጥታ ፣ ሌሊቱ፡ቅጽበቱ፡እነዚህ ሁሉ ተባብረው ለአቡኑ ዕረፍትና መኝታ አንዳች ያክሉበት ነገር ያለ ይመስል ነበር ። በእንቅልፋቸው እንኳ መለኮታዊ ባህርይ ይነበብባቸው ነበር ።

ጣጎን ቫልጣ መቅረዝ የመሰለውን መሣሪያ በእጁ እንደያዘ ድምጹን አጥፍቶ ዝም ብሎ ቆመ ። የአቡኑ ርጋታና ልበ ሙሉነት አስፈራው ። ሕሊናውን አስጨነቀው ።

በሃሳቡ ውስጥ ምን ይመላለስ እንደነበረ የሚያውቅ ሰው የለም ። እሱ ራሱ ያውቅ እንደነበረም ያጠራጥራል ። ንጹሁን ሰው ማጥቃት.....!

ዓይኑን ከአቡኑ ገጽታ ለአንድ አጭታ እንኳ አልነቀለውም ። በመደነቅ ያስታውሳቸው ነበር ። ሀሳቡም ተምታትቶበት ነበር ። ከውድቀትና ከትንሣዔ የትኛውን ልምረጥ.....? የአቡኑን ጭንቅላት ልከስክሰው ወይንስ ጐንበስ ብዬ እጃቸውን ልሳመው.....? የትኛውን ብመርጥ ይሻለኛል.....? ብሎ የሚያስብ ይመስል ነበር ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ግራ እጁን ወደ ግንባሩ አንስቶ ቆቡን አወለቀው ። ቀጥሎም ያስላስል ጣቢ ። አቡኑ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ስለነበሩ አንዲም አልተላወሱም ።

ከእሳት ማገደሻው ላይ የነበረው መስቀል በጨረታው ብርሃን ይታይ ነበር ። አቡኑን ሰመባረክና ጣጎን ቫልጣን ይቅር ለማለት መስቀሉ እጁን የዘረጋ መሰለ ።

ጣጎን ቫልጣ ቆቡን መልሶ ራሱ ላይ ደፋው ። ቀጥሎም በፍጥነት አልጋወን አልፎ ሄደ ። ወደ ቁም ሣጥኑ ማምራቱ ነበር ። ቁም ሳጥኑን በኃይል ለመክፈት እንደፈለገ ሁሉ መሣርያውን ወደላይ አንስቶ ያዘው ። ነገር ግን ቁም ሣጥኑን ለመክፈት መሣርያው አያሻውም ነበር ። ቁልፉ እንደወትሮው ቁም ሣጥኑ ላይ ተቶት ነበር ። ግን ቫልጣ ቁልፉን ጠምዝዞ ቁምሳጥኑን ከፈተው ። የብር ዕቃዎች የነበሩበትን ቅርጫት አጣንና ስቦ አወጣው ። ይዘትም ወደመኝታው ክፍል ተመለሰ ። ከዚያ በኋላ መስኮቱን ከፈተው ። ዱላውን ያዘ ። የብር ዕቃዎቹን በጣዙ ሻንጣው ውስጥ ወሸቃቸውና ቅርጫቱን ወደ ውጭ ወረወረው ። እሱ ራሱ በመስኮቱ ዘሎ ወጥቶ የኢትክልቱን ቦታ አቋርጦ ሄዶ እንደነብር የአጥር ግምቡን ዘሎ ወጥቶ ይሸሽ ጀመር ።

—12—

በማግሥቱ ጠዋት ንጋት ላይ ብጹዕ አንኳን ደህና መጡ በአጎ ክልቱ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ነበሩ ። ማዳም ማሷር ስትሮጥ ወደአሳቸው ሄዳ ፤ ጠብጹዕ


@OLDBOOKSPDF

ነትዎ! ብጹዕነትዎ!» ስትል ጮኸች ፤ «የብር ዕቃዎቹ የሚቀመጡበት ቅርጫት ወዴት እንዳለ አውቀዋል ብጹዕነትዎ?»

«አዎን..... የት እንዳለ አውቃለሁ ።»

«ኡኸ! አምላኬ ምስጋና ይግባህ!» ስት ል በኃይል ተነፈሰች ማዳም ማኒር ፤ «እኔስ እንዲያው የጠፉ መስሎኝ.....!»

አቡኑ ቅርጫቱን ከተጣለበት አግኝተው አንስተውት ነበር ። «ይሄ ውልሽ!» ብለው ለማዳም ማኒር ሰጧት ።

«ብቻ..... ብቻ..... በውስጡ የነበሩት ዕቃዎችስ.....?»

«አዎ! ዕቃዎቹን ኖሯል የፈለግሽው? ዕቃዎቹ ወዴት እንዳሉስ እኔ ራሴ አላውቅም ።»

«ወይ ፈጣሪዬ! ተሰረቁ ማለት ነው? ሴሊት ከዚህ ያደረው ሰውዬ መሆን አለበት የሰረቃቸው» ብላ በፍጥነት ሰውዬው ወዴ አደረበት ክፍል ደርሳ ተመልሳ መጣች ። አቡኑ ጉንበስ ብለው አበባቸውን ሲመለከቱ ነበሩ ። «ሰውዬው ሄዷል ። ዕቃዎቹን ሰርቆ ሄዷል ብጹዕነትዎ» ብላ ስት ጮህ አቡኑ ቀና አሉ ። ቀጠል አድርጋም ፤ «በዚያ ነው ዘልሎ የወጣው» አለቻቸው ወዴ ግንብ አጥሩ እያመለከተች ፤ «ኮቴው ይታይዎታል ብጹዕ ነትዎ? በዚያ ነው ተፈትልኮ የወጣው ። መንትፎን ጠፋም አይደል!»

አቡኑ ለአጭር ጊዜ ዝም ብለው ቆመና ፤ «ቀድሞውንስ ቢሆን የብር ዕቃዎቹ መች የኛ ኖረዋል?» አሏት ። ምን ማለታቸው እንደሆነ ስላልገባት ተደናግራ ዝም ብላ ተመለከተቻቸው ። «ማዳም ማኒር.....» አሏት አሳቸው ም ፤ «ዕቃዎቹን እስከዛሬ ድረስ እዚህ ሚቶየቱ ስሀተት ነበር ። ተሸጠው ለችግረኞች መርሿ መዋል ነበረባቸው ። አሁንም ቢሆን የወሰዳቸው ችግ ረኛ ሰው ስለሆነ ግድየለም!»

«ያለማንኪያና ሹካ በምን ይበላሉ ብጹዕነትዎ?»

«ከቆርቆሮ የሚሠራ ማንኪያና ሹካ የሶም እነዬ?»

«ከቆርቆሮ.....? ከቆርቆሮ የተሠራ ማንኪያና ሹካ ደስ የማይል ሽታ አለው ብጹዕነትዎ ።»

«እግዳያው ከብረት የተሠራ ማንኪያና ሹካ ይፈለጋላ!»

«ከብረት የተሠራውም የምግቡን ጣዕም ያበላሻል» አሉቻቸውፊቷን ኮስ አስመስላ ።

«እንዴ ከሆነም ከእንጨት የተሠራ ማንኪያና ሹካ አይጠፋም»



@OLDBOOKSPDF

ከትንሽ ጊዜ በኋላ አቡኑ ቁርሳቸውን ለመብላት ወደ ምግብ ቤቱ ገቡና በትናንትናው ምሽት ጎን ቫልጎ ተቀምጦበት በነበረ ሥፍራ ቁጭ አሉ ። እህታቸው እዚያው አለች ። አንድም ቃል አልተነፈሰችም ። ማዳም ማሷር ግን አውንም ስታጉረመርም ነበረች ። አቡኑ የቀረበላቸውን ዳቦና ወተት እየቀማመሱ ፤ «በእውነቱ ከሆነ ዳቦ ቆርሶ በወተት አጥቅሶ ለመ ብላት የብር ማንኪያና ሹካ ይቅርና የእንጨት ማንኪያና ሹካም አያስፈ ልግም» አሉ እየሳቁ ።

«ወይ ጉዴ!» አለች ማዳም ማሷር በልቧ ፤ «እንዲያ ያለውን መንታፊ ከቤት ውስጥ ማሳደር.....! ያውም ከብጹዕነታቸው መኝታ ክፍል አጠገብ..... ኧረ እንኳን አዶጋ ሳያደርስባቸው ቀረ.....! ሊገላቸው ይችል ነበርኮ.....!»

ማዳም ማሷር እንዲሁ ስታስብ ሳለች ፤ አቡኑና እህታቸውም ቁርሳቸ ውን በልተው ጨርሰው ሲነሱ ሲሉ በሩ ተንኳኳ ።

«ግባ!» አሉ አቡኑ ።

በሩ ተከፈተ ። አራት ሰዎች ከበራፉ ላይ ቆመዋል ። ሦስቱ ፖሊሶች ናቸው ፤አራተኛው ፣ ግን ቫልጎ ። ፖሊሶቹ ማጅራቱን ይዘው ነው ያመ ጡት ። አለፍ ብሎም የብርጋዴዬር ማዕረግ ያለው የፖሊሶቹ አዛዥ ቆሟል ። አዛዡ ራመድ ብሎ ገብቶ ለአቡኑ የወታደር ሰላምታ ሰጣቸውና «ብጹዕ ትዎ.....» አለ ።

ግን ቫልጎ በዚህ ጊዜ ተደናገጠ ። አቡነ ሚሪዬል አቡን መሆናቸ ውን አላወቀም ነበር ። «ብጹዕነትዎ.....? ተራ ካህን አይደሉማ!» አለ ።

«አፍህን ዝጋ!» አሉዎ ከፖሊሶቹ አንደኛው ።

አቡኑም ተነስተው ሂድ አሉና ዣን ቫልጎን እየተመለከቱ ፤ «አህ! አንተ ነህ እንዴ! እንኳን ተመልሰህ መጣህ» አሉትና ፤ «ለመሆኑ መቅረዞ ቹን ሳትወስዳቸው ለምን ቀረህ? እነሱንም ጭምር ይዘህት ሂድ ብዬህኮ ነበር ። መቅረዞቹም ከብር የተሠሩ ስለሆኑ ሁሉት መቶ ፍራንክ ያወጡልህ ነበር ። እና ለምንድነው ት ተህቸው የሄድከው ?» ሲሉ ጠየቁት ።

ግን ቫልጎ ከመገረም የተነሳ ዓይኑን በልጦ ቀረ ። በዚያን ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት እንደተሰማው በትክክል ለመግለጽ አይቻልም ።

«ብጹዕነትዎ.....» አለ የፖሊስ አዛዡ ፤ « ይህ ሰው የነገረን እውነት ይሆንን እንደሌባ ገልመጥ ገልመጥ እያለ ሲሄድ አግኙተነው በጥርጣሬ ያዝነው ። ስንፈት ሸው እነዚህን የብር ዕቃዎች አገኘንበት ።»

«እና አንድ አዛውንት ካህን ከቤቱ አሳድሮኝ እነዚህን ዕቃዎች ሰጠኝ ብሎ ነገራችሁ..... እናንተ ግን ስላላመናችሁት ይዛችሁት መጣችሁ..... አይደለም እንዴ?»



@OLDBOOKSPDF

«አልሰረቀም ካሉ.....?»

«አልሰረቀም ። ልቀቁት ።»

ፖሊሶቹ ጐን ቮልጐን ለቀቁት ። እሱ ግን ለማመን ቸገረው ። «እውነት ነጻ ተለቅቄአለሁ?» ሲል ጠየቀ ።

«ወዳጄ..... ተለቅቀሀል» አሉት አቡኑ ፤ «ከመሄድህ በፊት ግን መቅረዞቹን እንዳትረሳቸው ። እነሱንም ይዘሀቸው ሂድ» አሉትና ወደ አሳት ማንደጃው ሄድ ብለው መቅረዞቹን አገለተው ሰጡት ። ማድሚዜል ባፕቲስቲንና ማዳም ማኟር በዝምታ ሲመለከቱ ነበሩ ።

የጐን ቫልጐ ሰውነት ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ምኑንም ሊያምን አልቻለም ። ግር ብሎት አቡኑን ተመለከታቸውና መቅረዞቹን ተቀበላቸው ።

«በል እንግዲህ በሰላም ሂድ» አሉት ፤ «በነገራችን ላይ.....በሌላ ጊዜ ስትመለስ በአትክልቱ ቦታ ሳይሆን በቀጥታ በበሩ ለመግባት ና ለመውጣት ትችላለህ ። በሩ ሌሊትም ሆነ ቀን በመንጠቆ ይያዛል እንጂ አይቆለፍም» አሉትና ዓይናቸውን ወደ ፖሊሶቹ አዙረው ፤ «እናንተም ልትሄዱ ትችላላችሁ ወንድሞቼ» አሏቸው ።

ፖሊሶቹ ተስናብተዋቸው ሄዱ ። ጐን ቫልጐ ግን ሕሊናውን ሰቶ ለመውደቅ የተቃረበ ይመስል ነበር ።

አቡኑ ተጠጉትና ፤ «ቃል ገብተህልኝ የነበረውን እንዳትረሳ.....» አሉት ፤ «ከነዚህ ዕቃዎች ከምታገኘው ገንዘብ ሀቀኛ ሰው ለመሆን እንድትሞክር የገባህልኝን ቃል እንዳትዘነጋ» አሉት ።

ጐን ቫልጐ እንዲህ ያለ ቃል መግባቱን ስለማያስታውስ የሚናገረው ጠፍቶት ዝም ብሎ ቆመ ። አቡኑም ቀጠሉ አድርገው ፤ «ወንድሜ ጐን ቫልጐ.....» አሉት ፤ «ከአሁን ጀምሮ ክፉ ሰው አይደለህም ። በጎ ሰው ነህ ። ነፍስህን ለማዳን ነው ጥረት የሚያደርገው ። ነፍስህን ከክፋት አዘቅት አውጥቼ ለእግዚአብሔር ሰጥቻታለሁ.....»

— 13 —

ጐን ቫልጐ በጥድፊያ እየተራመደ ፣ ባገኘው መንገድ እያሳበረ ከከተማው ወጥቶ ይገሰግስ ጀመር ። ምግብ ሳይቀምስ ፣ ረሀብም ሳይሰማው እስከ እኩለ ቀን ድረስ እንዲሁ ሲኳትን ዋለ ። በውስጡ አንዳች ለውጥ በመካሄድ ላይ ነበር ። ውስጣዊ ቁጣ ተሰማው ። ቁጣው በማን ወይም በምን ላይ እንደነበረ ግን እሱ ራሱ ለማወቅ አልቻለም ። የአስር ቤት ሕይወቱ ስሜቱን እደንድኖበት ነበር ። አሁን ግን አንዳች ዓይነት ልስላሴ ተሰማው ።



@OLDBOOKSPDF

አልወደደውም ፥ አስፈራው ። ልቤ ከሚለስልስ ፖሊሶቹ ይዘው ቢያስሩኝ ይሻለኛል ሲል አሰበ ። የልስላሴው ስሜት መንፈሱን በጣም አደርገው ረበሸው ።

በዚሁ ሁኔታ ዋለና ወደ ማታ ጊዜ ጸሐይ አቁልቁላ ስትወርድና ጥላዎችም እየረዘሙ ሲሄዱ ከአንድ ጥሻ በስተጀርባ ደርሶ ቁጭ አለ ። ብዙርያ ገቡ ሰው የለም ። ከአድማሱም አካባቢ ከአልፐስ ተራራ ስንሰ ለት በስተቀር ሌላ ነገር አይታይም ። ግን ቫልገ ከዴ ከተማ አስራ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ከሚርቅ ቦታ ነበር ። ከተቀመጠበት ሥፍራ ትንሽ ራቅ ብሎም አንድ የእግር መንገድ ነበር ።

ከዚሁ ቦታ ቁጭ ብሎ ሲያሰላስል ሳለ ሰጀር ዴስ የሚል ድምጽ ሰማ ። ራሱን አቅንቶ ቢመለከት አንድ ታዳጊ ወጣት ታየው ... የሳቪይ ተወላጅ..... ዕድሜው አስር ዓመት የሚሆን ። በእግር መንገዱ እየተጓዘ ሲዘምር ነበር ። ጥሻንት የመሰለ የመዚታ መሣርያም ሲጫወት ነበር ። አልፎ አልፎ ቆም እያለም ሳንቲም እየተወራወረ ይጫወት ነበር ።

ልጁ ግን ቫልገን አላያውም ። ከአቅራቢያው ደርሶ እንደበፊቱ ቆም ብሎ ሳንቲሙን ወደላይ ወረወረው ። በተሰምዶ ፥ የወረወረውን ሳንቲም ሳይሰት በአይበሉባት እጁ ይቀበለው ነበር ። አውጎ ግን የአርባ ሱ ዋጋ ያለው ሳንቲሙ ከእጁ አምልጦ ወድቆ ግን ቫልገ ወዳለበት እየተንከባ ለለ ወረደ ። ከዚያ ሲደርስ ግን ቫልገ በእግሩ ረግጦ አቆመው ። ሳንቲሙ እየተንከባለለ ሲወርድ በዓይኑ ይከተለው የነበረው ታዳጊ ወጣት ይሽን ጊዜ ግን ቫልገን አየው ። ወደአሰው እየተራመደ ሄደ ።

ከግን ቫልገ አጠገብ ሲደርስ ጀርባውን ሰጸሐይ ሰጥቶ ቆመ ። ጸሐዩ ጸጉሩ ላይ ወርቃማ ቀለም ጫለበት ።

ጣንዘቤን ይስጡኝ ጌታዬ» አለው ታዳጊው ወጣት ።
«ስምህ ማን ነው?»
«ትንሹ ዝርዚ»
«በል ከፊቴ ጥፋ» አለው ግን ቫልገ ።
ጣንዘቤን ይስጡኝ ጌታዬ»

ግን ቫልገ ዝም አለው

ጣንዘቤን ይስጡኝ ጌታዬ..... ገንዘቤን»

ግን ቫልገ አሁንም ዝም አለው ። አቀርቅሮ ተቀምጧል ።

ጣንዘቤ..... ነጪ ሳንቲሜ ።»

ዝም ዝም ።



@OLDBOOKSPDF

ታዳጊው ወጣት በንጹህ ልብ የጣን ቫልጣን አንገት ይዞ ይነቀንቀው ገባ ። እግሩንም ከሳንቲሙ ላይ ሰማንሳት ይታገል ጀመር ።

«ጣንዘቤን.....አርባውን ሱኤን ይስጡኝ ጌታዬ» እያለ ማልቀስ ጀመረ ታዳጊው ወጣት ። ጣን ቫልጣ ካቀረቀረበት ቀና አለ ። የተጨነቀና የተግ ረመ መስሎ ታዳጊውን ወጣት አተኩሮ አየው ። እጁንም ወደበትሩ ዘረ ጋና «አንተ ማነህ?» ሲል ጮኸበት ። የሚያስፈራ ጩኸት ።

«ትንሹ ዝርቪ እባላለሁ ጌታዬ ። ሳንቲሜን ይስጡኝ ። እግርዎን ከሳንቲሜ ያንሱልኝ ።»

«ኣ.....እ..... አንተው ነህ?» አለና ጣን ቫልጣ ተነስቶ ቆመ ። እግሩን ግን ከሳንቲሙ አላነሳውም ። «አንተው ነህ.....? በል ከፊቴ ጥፋ ።»

ታዳጊው ወጣት ፈራው ። ሰውነቱም ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ከዚ ያም በኋላ እግሬ አውጪኝ ብሎ ይሮጥ ጀመር ። አንድ ጊዜ እንኳ መለስ ብሎ ሳይመለከት በርሮ ሄደ ። ራቅ ካለ ሥፍራ ከደረሰ በኋላ ግን ትንፋሽ አጥሮት ቆም አለ ። ተንሰቅስቆም ሲያለቅስ ጣን ቫልጣ ሰማው ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ትንሹ ልጅ ከጣን ቫልጣ ዓይን ተሰወረ ።

ጀምበር ጠለቀች ። ብርድ ወረደ ። ጣን ቫልጣ በቆመበት ቀረ ። ከፊት ለፊቱ ጥቂት እልፍ ካለ ሥፍራ ዛር ላይ የወደቀ ሰማያዊ ገል ነበር ። ዓይኑን እዚያ ላይ ተክሎ ቀረ ። ከዚያም በኋላ የምሽቱ ብርድ ያንዘፈዝፈው ጀመር ።

ቆቡን በራሱ ላይ አመቻችቶ ኮቱን እንደመቆለፍ ብሎ አንድ ርምጃ ወደፊት ሄደና አጣንብሶ ዘንጉን አንስቶ ያዘ ። በዚህ ጊዜ በእግሩ ሥር የነ በረውን ሳንቲም አየው ። በእግሩ ተጭኖት ስለቆየ ወደመሬት ገባ ቢልም ሲበለጨለጭ ነበር ። የጣን ቫልጣን ስሜት አንዳች ነገር ወረረው ። «ምን ድነው ይሄ!» አሰ ራሱ ሰራሱ ። ሦስት ርምጃ ያህል ወደኋላው ሸሸት ብሎ ቆመ ። ሳንቲሙ የሰው ዓይን እንደሆነ ሁሉ ያፈጠጠበት መሰለው ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ለቀም አድርጉ አነሳው ። ቀና ብሎም ወደ ሰማዩ አጉጣሰ ይመለከት ጀመረ ። የበረገገና መጠለያ ያጣ አውራ ይመስል ነበር ።

ዙርያ ገቡን ቢያስተውል ምንም የለም ። ሴሊቱም እየከበደ የመሄድ ላይ ነበር ።

«አ!» አለና ታዳጊው ወጣት ወደሄደበት አቅጣጫ ይገሰግስ ጀመር ። ሠላሳ አርምጃ ያህል ከተጓዘ በኋላ ቆም አለ ። አሁንም ዙርያ ገቡን ቢመ ለከት ምንም የለም ። ቀጥሎም «ትንሹ ዝርቪ! ትንሹ ዝርቪ!» ብሎ ያጣራ ጀመር ።



@OLDBOOKSPDF

መልስ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ጀሮውን አቁሞ ያዳምጥ ገባ ። ነገር ግን ምንም ዓይነት ድምጽ አልነበረም ።

አካባቢው ጨለማለ ። ጭርም ብሏል ። እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ነፋስ ይነፍስ ጀመር ። ነፋሱ የተቆጣ ይመስል ግር ቅጠሎን ያርገበግበው ገባ ።

ጎን ቫልገር እንደገና መሪመድ ጀመረ ። ተጥሎም ይሮጥ ጀመር ። አልፎ አልፎም ቆም እያለ «ትንሹ ገርቼ! ትንሹ ገርቼ!» እያለ ይጣራል ። ትንሹ ገርቼ ቢሰማው ኖሮ መልስ ባልሰጠውም ነበር ። እንዲያውም በተደበቀው ነበር ፤ በጣም ፈርቶት ነበርና ። እሱ ግን በጣም ርቆ ሄዶ ነበር ።

ጎን ቫልገር በፈረስ የሚንዙ አንድ ቄስ አገኘ ። ጠጋ አሳቸውና «አንድ ልጅ በዚህ ሲያልፍ አይተህ ይሆን?» ሲል ጠየቃቸው ።

«አላየሁም» አሉት ቄሱ ።
«ትንሹ ገርቼ የሚባል ልጅ....»
«ማንንም አላየሁም ።»

ጎን ቫልገ አስር ፍራንክ ከቦርሳው አውጥቶ ለቄሱ ሰጣቸው ። «ለድሆችህ ስጣቸው» አሳቸውና ፤ «ልጁ አስር ዓመት ያህል ዕድሜ ያለው ፣ የሙዚቃ መሣርያ የያዘ ፣ የሳቨይ ተወላጅ ነበር ።» አሳቸው ።

«ልጁን አላየሁትም ።»
«ትንሹን ገርቼ.....እ አሰና ወዘዚህ አካባቢ መንደር የለም ለመሆኑ?» ሲል ጠየቃቸው ።

«አንተ እንደገለጽከው ከሆነ ልጁ ወዘዚህ አካባቢ እንግዳ መሆን አለበት ። የሱ ዓይነት ታዳጊ ልጅች በዚህ አካባቢ ሲያልፉ ብዙ ጊዜ ይታያሉ ። ግንኑታቸው ግን አይታወቅም ።»

ጎን ቫልገ እንደገና አስር ፍራንክ አውጥቶ ለቄሱ ሰጣቸው ።« ለድሆችህ ስጣቸው» አሳቸውና «እባክህን አስይዘኝ..... ሴባ ስለሆንክ አስይዘኝ» አላቸው ።

ቄሱ ደንግጠው ጎን ቫልገርን ፈርተውት ፈረሳቸውን ኮረኮሱት ። ጎን ቫልገርም ይዞት በነበረ አቅጣጫ በሩጫ ይጓዝ ጀመር ።

ዙርያ ገቡን እየተመለከተ ፣ እየተጣራ ፣ እየጮኸ ርቆ ሄደ ። በመንገድ አንድም ሰው አላገኘም ። ሁለት ወይ ሦስት ጊዜ በሩቁ ሰው ያየ መስሎት ወደዚያ ሲሮጥ ሄደ ። ጥሻ ወይም ድንጋይ እንጂ ሰው ግን አላገኘም ። በሦስት የተለያዩ አቅጣጫዎች የሚያመሩ መንገዶች ካሉበት ሥፍራ ደርሶ ቆም አለ ። ጨረቃ ወጥታለች ። ወደ ሰማዩ አድማስ እያየ አውንም

@OLDBOOKSPDF